


*From the Library of*

**ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ**


**FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES**

ደራሲው

ኮንስታንቲን፡ስታኒዩኮቪች።

# ማክሲምካ

## የመርከበኞች፡ ታሪክ።



የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡
ማዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ።
ሞስኮ ።

በሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ታተመ ።


Константин Станюкович

Максимка

МОРСКИЕ РАССКАЗЫ

*на амхарском языке*

С $\frac{70803-137}{014(01)-76}$ без объявления




## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

የመርከብ ፡ ደወል ፡ ከተደወለ ፡ አፍታም ፡ አልሆነ ፤ ጊዜው ፡ ከጧቱ ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ቀኑም ፡ የተዋበ ፡ የሞቃት ፡ አገር ፡ ቀን ፡ ነው ። ቦታው ፡ በአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ መካከል ፡ ላይ ፡ ነው ።

ከወርቅ ፡ እንደተሠራ ፡ ኳስ ፡ የምትነደውና ፡ የምታንጸባርቀው ፡ ፀሐይ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ክፍት ፡ ሰማያዊ ፡ ያለውን ፡ ሰማይ ፡ ፈጥና ፡ ሽቅብ ፡ ትወጣዋለች ። ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ለብሳ ፡ ወደ ላይ ፡ ስትጋልብም ፡ ንጹሕ ፡ ጨረሮቿ ፡ እንደሚያምር ፡ የጥልፍ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ወተት ፡ በመሰሉ ፡ ትናንሽ ፡ የደመና ፡

ንድፎች ፡ ተጋርደዋል ። ሰፊውን ፡ ውቅያኖስ ፡ በሚያብረቀርቀው ፡ ብርሃኗ ፡ አልብሳዋለች ። በርጋታ ፡ የሚንቀሳቀሰው ፡ የባሕር ፡ ሚዳም ፡ ከአንደኛው ፡ ሩቅ ፡ ሰማያዊ ፡ አድማስ ፡ እስከሌላው ፡ ጽንፍ ፡ በሰፌው ፡ ተዘርግቷል ።

በዙሪያው ፡ ያለው ፡ አየርም ፡ ጸጥ ፤ እረጭ ፡ ብሏል ።

የሚሰማው ፡ ድምጽ ፡ ክፍት ፡ ሰማያዊ ፡ የሆኑት ፡ ታላላቅ ፡ ማዕበሎች ፡ ብር ፡ የመሰለውን ፡ ጠርዛቸውን ፡ እያብለጨለጩ ፡ ተከታትለው ፡ ሲሮጡና ፡ በርጋታ ፡ ቸምቧ ፡ ብለው ፡ በመተቃቀፍም ፡ በሞቃቱ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ጥንታዊ ፡ ውቅያኖስ ፡ ጠባይ ፡ ምንጊዜም ፡ የማይለወጥ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ በሹክሹክታ ፡ ሲናገሩ ፡ ነው ።

ውቅያኖስ ፡ እንደ ፡ እሩኅሩኅና ፡ እንደ ፡ አፍቃሪ ፡ ሞግዚት ፡ ሁሉ ፡ መርከቦችን ፡ በግዙፍ ፡ ደረቶቹ ፡ ላይ ፡ ይሸከማቸዋል ፤ ኃይለኛ ፡ ዝናብና ፡ ማዕበል ፡ በማስነሳትም ፡ መርከበኞችን ፡ አያስፈራራቸውም ።

ባሕሩ ፡ ጭር ፡ ብሏል ።

አንዳችም ፡ መርከብ ፡ በየትም ፡ በኩል ፡ አይታይም ፤ አንድ ፡ የጭስ ፡ ቡልቅታ ፡ እንኳ ፡ ላመል ፡ የለም ። ከሰፊው ፡ የውቅያኖስ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ የለም ።

አልፎ ፡ አልፎ ፡ ግን ፡ ብር ፡ የመሰሉት ፡ የበራሪ ፡ ዓሣ ፡ ገላዎች ፡ በፀሐይዋ ፡ ብርሃን ፡ ሲያብረቀርቁ ፡ ይታያሉ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ተጫዋች ፡ ዓሣነባሪ ፡ ጥቁር ፡ ጀርባውን ፡ እያገላበጠ ፡ እንደ ፡ ፏፏቴ ፡ ሽቅብ ፡ ውኃውን ፡ ሲተፋው ፡ ይታያል ፤ አለዚያም ፡ ጥቁር ፡ ወይም ፡ ነጭ ፡ የባሕር ፡ አሞራ ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ሲያንዣብብ ፡ ይታያል ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ግራጫ ፡ የባሕር ፡ ወፍ ፡ ውኃውን ፡ ታካ ፡ ወደሩቁ ፡ የአፍሪቃ ፡ ወይም ፡ ያሜሪካ ፡ ጠረፍ ፡ ፈጥና ፡ ስትበር ፡ ትታያለች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባሕሩ ፡ እንደገና ፡ ጭር ፡ ይላል ። የሚያ



ጕረመርሙት ፡ ማዕበሎችና ፡ ፀሐይዋ ፡ እንዲሁም ፡ ሰማዩ ፡ እነዚህ ፡ ብቻ ፡ ብሩኅነታቸውን ፡ አስደሳችነታቸውንና ፡ ደግነታቸውን ፡ እንደያዙ ፡ ይቀራሉ ።

«ዛቢያካ ፡» የተባለችው ፡ በእንፋሎት ፡ የምትነዳ ፡ ፈጣን ፡ የሩሲያ ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ በውቅያኖሱ ፡ የሚነቃነቅ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ በርጋታ ፡ እየተወዛወዘች ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ትገሠግሣለች ፤ እያንዳንዱም ፡ ቀን ፡ ከጨካኙና ፡ ከጨለማው ፡ የሰሜን ፡ መሬት ፡ እያራቀ ፡ ይወስዳታል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይኸው ፡ ጨካኝና ፡ ጨለማ ፡ መሬት ፡ የሚናፈቅና ፡ የሚወደድ ፡ ነው ።

«ዛቢያካ ፡» የተባለችው ፡ ይህች ፡ ትንሽና ፡ ጥቁር ፡ ቅልብጭ ፡ ያለችና ፡ የጠዳች ፡ መርከብ ፡ በሦስት ፡ ምሰሶዎችዋ ፡ ላይ ፡ ሸራዎን ፡ ዘርግታ ፡ ከሰሜናዊ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚነፍሰው ፡ የማያቋርጥ ፡ ነፋስ ፡ እየገፋት ፡ በሰዓት ፡ ሰባት ፡ ወይም ፡ ስምንት ፡ ማይል ፡ ያህል ፡ ትጓዛለች ። ቀስት ፡ በመሰለው ፡ ግንባሯ ፡ ባሕሩን ፡ እየሰነጠቀች ፡ በማዕበሉና ፡ በሚደነፋው ፡ አረፋ ፡ ላይ ፡ እንዲሁም ፡ በሚረጨው ፡ ውኃ ፡ መካከል ፡ በርጋታና ፡ በኩራት ፡ ትቀዝፋለች ። ማዕበሉ ፡ ጐኗን ፡ በለዘብታ ፡ ይልሰዋል ፤ ባሕሩን ፡ ሰንጥቃው ፡ ስትሄድ ፡ ከወደኋላዋ ፡ የሚቀረው ፡ ፈለጓም ፡ የሚያንጸባርቅ ፡ ሰፊ ፡ የብር ፡ ሻሽ ፡ ይመስላል ።

የመርከቧን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ለመስቀልና ፡ የቀኑን ፡ ሥራ ፡ ለመጀመር ፡ ዘወትር ፡ ከጧቱ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ የሚደረገው ፡ መርከብ ፡ የማጽዳትና ፡ የመጠራረግ ፡ ተግባር ፡ ተጀምሯል ።

መርከበኞቹ ፡ ነጭ ፡ የሥራ ፡ ሸሚዛቸውን ፡ ለብሰው ፡ በመርከቧ ፡ ላይ ፡ ተሰማርተዋል ። ሥራ ፡ ያጠነከረው ፡ ደንደሳቸውም ፡ በሸሚዛቸው ፡ ሰፌ ፡ ሰማያዊ ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ ዘልቆ ፡ ይታያል ፤ በሌጣ ፡ እግራቸው ፡ ሁነውና ፡ ሱሪያቸውን ፡ እጉልበታቸው ፡ ድረስ ፡ ሰቅስቀው ፡ የመርከቧን ፡ መድረክና ፡ ጠርዙን ፤ መድፉንና ፡

ከነሐስ ፡ የተሠራውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሌላውን ፡ «ዛ
ቢያካ ፡» የያዘችውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይጠርጋሉ ፡ ይፈትጋሉ ፡ ይወለ
ውላሉ ። ሲሠሩም ፡ መርከበኞች ፡ መርከባቸውን ፡ ሲያጸዱ ፡ በሚ
ያሳዩት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ ማንኛውም ፡
በመርከቧ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ባሸዋም ፡ ሆነ ፡ በልዩ ፡ አ
መድ ፡ ልቡ ፡ እስቲጠፋ ፡ ተወልውሎ ፡ ፍጹም ፡ ንጹሕ ፡ ይሆናል ፡
ማለት ፡ ነው ።

መርከበኞቹ ፡ ከልባቸው ፡ ተግተው ፡ ይሠራሉ ፤ የሥራ ፡ ኃ
ላፊ ፡ የሆነው ፡ ማትቬኢች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሲጮኽባቸው ፡ ብቻ ፡
ይስቃሉ ። ይህ ፡ ሰው ፡ በመርከበኛነት ፡ ጥርሱን ፡ የነቀለ ፡ ነው ።
ዓይኖቹ ፡ ግራጫ ፡ ናቸው ፤ ፊቱም ፡ ከፀሐይ ፡ ቃጠሎና ፡ እወደብ ፡
ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ብዙ ፡ ከመጠጣት ፡ የተነሣ ፡ ቀይ ፡ ነው ። እርሱ ፡
የሚፈጥረው ፡ ስድብ ፡ እንኳንስ ፡ ሌላውንና ፡ ስድብን ፡ መስማት ፡
የለመደውን ፡ የሩሲያን ፡ መርከበኞች ፡ ጆሮ ፡ ይማርካል ። ማትቬ
ኢች ፡ ይህን ፡ የሚያደርገው ፡ መርከበኞቹን ፡ የበለጠ ፡ እንዲሠሩ ፡
ለማድረግ ፡ ሳይሆን ፡ «ለወጉ ፡ ለማረጉ ፡» ሲል ፡ ነው ።

በማትቬኢች ፡ ስድብ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አይከፋ ። ደግና ፡ ጨ
ዋ ፡ ለሁሉም ፡ ትክክለኛና ፡ ሥልጣኑን ፡ ለክፉ ፡ ተግባር ፡ የማያው
ል ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ሁሉም ፡ ያውቃሉ ። ስድብ ፡ ጣልቃ ፡ ሳያስ
ገባ ፡ ሦስት ፡ ቃላት ፡ ለመናገር ፡ እንደማይችልም ፡ ገና ፡ ዱሮ ፡ ተገ
ንዝበውት ፡ ለምደውታል ። በስድብ ፡ ረገድ ፡ ስለሚያፈልቀው ፡ ል
ዩ ፡ ልዩ ፡ ቃላት ፡ ብዙ ፡ ይደሰቱ ፡ ነበር ። እውነትም ፡ ሰውየው ፡ የ
ስድብ ፡ ፈላስፋ ፡ ኖርዋል ።

አንዳንዶቹ ፡ መርከበኞች ፡ የውኃ ፡ ገንዳና ፡ የጭስ ፡ ኩራዝ ፡
ወዳለበት ፡ ወደታችኛው ፡ ክፍል ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ይወርዱና ፡
ከሚሰነፍጠው ፡ ጭስ ፡ ትንሽ ፡ አሽትተው ፡ ከወዳጆቻቸውም ፡ ጋ
ር ፡ ላፍታ ፡ ተጫዋወተው ፡ ቶሎ ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ ይመለሱና ፡



መጥረጋቸውንና ፡ መፈተጋቸውን ፡ ይቀጥላሉ ። ከጧት ፡ ጀምሮ ፡
በየቦታው ፡ እየዞረ ፡ ሥራውን ፡ የሚቆጣጠረው ፡ ረጂሙና ፡ ቀጭ
ኑ ፡ ዋናው ፡ የመርከብ ፡ መኰንን ፡ ብቅ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ተ
ግተው ፡ መሥራታቸውን ፡ ለማሳየት ፡ ይሞክራሉ ።

ተረኛው ፡ የመርከብ ፡ መኰንን ፡ ወርቃማ ፡ ጸጉር ፡ ያለው ፡
ወጣት ፡ ልጅ ፡ ነው ። የመጠበቅ ፡ ተራው ፡ ከአስር ፡ ሰዓት ፡ እስ
ከ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ነበር ፤ በመጀመሪያው ፡ ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ የእን
ቅልፍ ፡ ስሜት ፡ ገና ፡ ዱሮ ፡ አልፎለታል ። ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሶና ፡
አንገተ ፡ ክፍት ፡ የሌሊት ፡ ሸሚዝ ፡ አጥልቆ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡
ይንጐራደዳል ። የምታቃጥለዋ ፡ ፀሐይ ፡ ገና ፡ ያላሞቀችውን ፡ ን
ጹሕና ፡ ቀዝቃዛ ፡ የጧት ፡ አየር ፡ በሳምባው ፡ ሙሉ ፡ እየሳበ ፡ ይተ
ነፍሳል ። መርከብ ፡ ነጂው ፡ ትክክለኛውን ፡ አቅጣጫ ፡ ይዞ ፡ መን
ዳቱንና ፡ የመርከቧ ፡ ሸራዎች ፡ በደንብ ፡ መዘርጋታቸውን ፡ ያያል ፤
ዝናብ ፡ የተሸከመ ፡ ደመና ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ለማረጋገ
ጥም ፡ ቆም ፡ እያለ ፡ ኰምፓሱን ፡ ሲመለከት ፡ ለስላሳ ፡ የነፋስ ፡
ሽውታ ፡ ማጅራቱን ፡ በለዘብታ ፡ ይዳብሰዋል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ በተቀደሰ ፡ ሞቃት ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ ማን
ኛውም ፡ ነገር ፡ ደህና ፡ ስለሆን ፡ ጠባቂው ፡ የመርከብ ፡ መኰ
ንን ፡ እምብዛም ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ አልነበረውም ።

በመርከቧ ፡ መሸጋገሪያ ፡ ላይ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ መንጐራ
ደዱን ፡ በመቀጠል ፡ የጥበቃ ፡ ጊዜው ፡ የሚያልቅበትን ፡ ሰዓትና ፡
ትኩስ ፡ ሻይ ፡ በኩባያ ፡ እየደጋገመ ፡ ከሚወደው ፡ ንጹሕ ፡ ዳ
ቦ ፡ ጋር ፡ የሚበላበትን ፡ ጊዜ ፡ ያስብ ፡ ነበር ። የመኰንኖች ፡ ወጥ ፡ ቤ
ት ፡ ሊጡን ፡ ለማራስ ፡ ያህል ፡ የተሰጠውን ፡ ቮድካ ፡ (አረቂ ፡) እ
ራሱ ፡ ጨልጦ ፡ ካልጠጣው ፡ በስተቀር ፡ ማለፊያ ፡ ዳቦ ፡ መሥራ
ት ፡ አሳምሮ ፡ ያውቃል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

በመርከቧ ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አስጠንቃቂ ፡ ዘበኛ ፡ በሚያስደነግጥና ፡ ባልተለመደ ፡ ከፍተኛ ፡ ድምጽ ፡ ሲጮኽ ፡ የጧቱን ፡ ጸጥታ ፡ አናጋው ።

«እባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ሰው ፡ አለ!» ሲል ፡ ጮኽ ።

መርከበኞቹ ፡ ሥራቸውን ፡ ትተው ፡ ወደመርከቧ ፡ ግንባር ፡ እሮጠው ፡ በመኝኝት ፡ ወደ ፡ ውቅያኖሱ ፡ ይመለከቱ ፡ ጀመር ።

«የት ፡ ነው?» ብለው ፡ ፊቱ ፡ በድንጋጤ ፡ አመድ ፡ የመሰለውን ፡ ባለ ፡ ወርቅማ ፡ ጸጉር ፡ ወጣት ፡ ዘበኛ ፡ በጩኸት ፡ ጠየቁት ።

«ያውና ፡ እዚያ ፡ ማዶ!» ብሎ ፡ በሚንቀጠቀጠው ፡ እጁ ፡ አመለከተ ። «አሁን ፡ ጠፋ ፤ ጐበዝ ! ካንድ ፡ ደቂቃ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ አይቸው ፡ ነበር ፤ በእንጨት ፡ ቁራጭ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ነበር ፡ ይመስለኛል ፤ እሱው ፡ ላይ ፡ የታሠረም ፡ ይመስላል ፡» ሲል ፡ እንደገና ፡ የእንጨቱን ፡ ቁራጭ ፡ ለማየት ፡ በከንቱ ፡ እየሞከረ ፡ በኃለ ፡ ስሜት ፡ ተናገረ ።

ጠባቂው ፡ መኰንንም ፡ ባስጠንቃቂው ፡ ዘበኛ ፡ ጩኸት ፡ በመደነቅ ፡ የማቅረቢያ ፡ መነጽሩን ፡ ዓይኑ ፡ ላይ ፡ ደቅነና ፡ ወዳመለከተው ፡ አቅጣጫ ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ። ምልክት ፡ ሰጭውም ፡ መነጽሩን ፡ ይዞ ፡ እንደዚሁ ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

«የሚታይህ ፡ ነገር ፡ አለን?» ሲል ፡ ወጣቱ ፡ መኰንን ፡ ጠየቀ ።

«አዎን ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፤ ጥቂት ፡ ወደግራ ፡ ይመልከቱ ።»

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መኰንኑም ፡ ሰው ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ በአንድ ፡ ቁራጭ ፡ እንጨት ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ በማዕበሉ ፡ ላይ ፡ ሲንገዋለል ፡ አየ ።



ጤናማ ፡ ሳምባው ፡ የሚፈቅድለትን ፡ ያህልም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ድምጹ ፡ እስኪሰነጠቅ ፡ ጮኸ ፤

«ሁላችሁም ፡ በመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ተሰብሰቡ! ጀልባ ፡ አዘጋጁ!»

ወደ ፡ ምልክት ፡ ሰጪው ፡ ሰውየ ፡ መለስ ፡ ብሎም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በኃለ ፡ ስሜት ፡ ተናገረ ፤

«ልብ ፡ ብለህ ፡ በዓይንህ ፡ ተከተለው!»

ትዕዛዝ ፡ ሰጪው ፡ መርከበኞቹን ፡ አሰልፎ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጮኸ ፤ «ወደላይኛው ፡ መድረክ ፡ ፈጥናችሁ ፡ ተሰብሰቡ!»

መርከበኞቹም ፡ ወደታዘዙበት ፡ ቦታ ፡ ፈጥነው ፡ ሲበታተኑ ፡ ያበዱ ፡ ሰዎች ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ። የመርከቧ ፡ አዛዥና ፡ ዋናው ፡ የመርከብ ፡ መኰንን ፡ በመሸጋገሪያው ፡ ላይ ፡ ቀድመው ፡ ተገኝተው ፡ ነበር ። ሌሎቹ ፡ መኰንኖች ፡ ግን ፡ አብዛኞቹ ፡ ገና ፡ በሙሉ ፡ ካለመንቃታቸውም ፡ በላይ ፡ ወደመድረኩ ፡ ሮጠው ፡ የመጡት ፡ እግረ ፡ መንገዳቸውን ፡ ልብሳቸውን ፡ እያጠለቁ ፡ ነበር ።

«መርከበኞች ፡ በሙሉ ፡ ተሰብሰቡ!» ሲባል ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ ትዕዛዝ ፡ ሰጪው ፡ ዋናው ፡ የመርከብ ፡ መኰንን ፡ ነበር ። መርከበኞቹም ፡ እያንዳንዱ ፡ ደቂቃ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ጥብቅ ፡ ትዕዛዙን ፡ በቅልጥፍና ፡ ተቀበሉ ።

ከሰባት ፡ ደቂቃ ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሸራዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ተጠቀለሉ ፤ «ዛቢያካም ፡» በማዕበሉ ፡ ላይ ፡ በለዘብታ ፡ መወዛወዝ ፡ ጀመረች ፤ አስራ ፡ ስድስት ፡ ቀዛፊዎችና ፡ አንድ ፡ መሪ ፡ መኰንን ፡ የያዘው ፡ ትልቅ ፡ ጀልባ ፡ ወደባሕሩ ፡ ወረደ ።

ጀልባው ፡ ከመርከቧ ፡ ተነጥሎ ፡ መሄድ ፡ ሲጀምር ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ እመርከቧ ፡ መሸጋገሪያ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፤

«እግዜር ፡ ፍጥነቱን ፡ ይስጣችሁ ፡» ሲል ፡ ተናገረ ።

መርከበኞቹም ፡ እባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ የወደቀውን ፡ ሰው ፡ ለማዳን ፡ በተቻላቸው ፡ ኃይል ፡ ሁሉ ፡ እየቀዘፉ ፡ በፍጥነት ፡ በረሩ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ «ዛቢያካ ፡» ለመዘጋጀት ፡ በወሰደባት ፡ ሰባት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ የተጓዘችው ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ያህል ፡ በመሆኑ ፡ ሰውየውንና ፡ የእንጨቱን ፡ ቁራጭ ፡ በማቅረቢያ ፡ መነጽር ፡ እንኳ ፡ ለማየት ፡ አዳገተ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ የእንጨቱ ፡ ቁራጭ ፡ የሚንሳፈፍበትን ፡ አቅጣጫ ፡ በኰምፓስ ፡ ተከትለውት ፡ ስለነበር ፡ ወደዚያው ፡ አቅጣጫ ፡ ከመርከቢቱ ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ቀዘፉ ።

ጀልባው ፡ በማዕበሉ ፡ ጠርዝ ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ብቅ ፡ እያለ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ደግሞ ፡ በማዕበሎቹ ፡ መካከል ፡ ጥልቅ ፡ እያለ ፡ ሲቀዝፍ ፡ የ«ዛቢያካ ፡» መርከበኞች ፡ በዓይናቸው ፡ ተከተሉት ፤ እያደርግም ፡ የባቄላ ፡ ፍሬ ፡ እያከለ ፡ ሄደ ።

ወዲያውኑም ፡ ጥቁር ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ አከለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

የመርከቢቱ ፡ መድረክ ፡ ጸጥ ፡ አለ ።

አልፎ ፡ አልፎ ፡ መርከበኞቹ ፡ በስተኋላ ፡ በኩልና ፡ በመድረኩ ፡ ጥግ ፡ እጅብ ፡ እያሉ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ እንዲህ ፡ በማለት ፡ ይነጋገራሉ ፤

«ምናልባት ፡ ከሰመጠ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ የወደቀ ፡ መርከበኛ ፡ ይሆናል ። »

«እዚህ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ መርከብ ፡ ልትሰምጥ ፡ አትችልም ። ጭራሹኑ ፡ የበሰበሰች ፡ መርከብ ፡ ካልሆነች ፡ በስተቀርም ፡ ልትሰበርም ፡ አትችልም ።»



«የለም ፤ ድንገት ፡ በጨለማ ፡ ከሌላ ፡ መርከብ ፡ ጋር ፡ ተጋጭታስ ፡ እንደሆን ።»

«ወይም ፡ ደግሞ ፡ ተቃጥላ ፡ ይሆናል ።»

«ታዲያ ፡ የተረፈው ፡ ሰውየ ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው!»

«ምናልባት ፡ ሌሎቹ ፡ በጀልባ ፡ ቀዝፈው ፡ ሲወጡ ፡ ይህ ፡ ሰውየ ፡ ብቻ ፡ ወደኋላ ፡ ቀርቶ ፡ ይሆናል ።»

«ለነገሩ ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ይሆን?»

«ውኃው ፡ ሞቅ ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ ምናልባት ፡ ነፍሱ ፡ ትኖር ፡ ይሆናል ።»

«ጐበዝ! ዓሣነባሪስ ፡ እንዴት ፡ ሳይበላው ፡ ቀረ ። በውኃው ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ አፈር ፡ ነው ፡ ያለው!»

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከመርከበኞቹ ፡ አንደኛው ፡ ትንፋሹን ፡ ዋጥ ፡ አድርጐ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ «ጐበዝ ፤ የመርከበኛ ፡ ሥራ ፡ አደገኛ ፡ መሆኑ ፡ ገባኝ ።» ይህን ፡ ቃል ፡ የተናገረው ፡ ሰው ፡ ጸጉረ ፡ ጥቁርና ፡ ባንደኛው ፡ ጆሮው ፡ ላይ ፡ ሎቲ ፡ ያንጠለጠለ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ነበር ። ወደ ፡ ባሕር ፡ ኃይል ፡ የገባው ፡ በዚያኑ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ በታላቅ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ጉዞ ፡ የጀመረውም ፡ ገና ፡ በጥሬነቱ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ።

በፊቱ ፡ ላይ ፡ የሐዘን ፡ ምልክት ፡ እያሳየ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ቆቡን ፡ አወለቀና ፡ አማተበ ፤ እግዜር ፡ ከባሕር ፡ ላይ ፡ አሰቃቂ ፡ ሞት ፡ እንዲጠብቀው ፡ በልቡም ፡ የሚጸልይ ፡ መሰለ ።

ለሦስት ፡ ሩብ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ የጭንቅ ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ።

በመጨረሻም ፡ የማቅረቢያ ፡ መነጽሩን ፡ ዓይኑ ፡ ላይ ፡ ደቅኖ ፡ የነበረው ፡ ምልክት ፡ ሰጪ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በደስታ ፡ ጮኸ ፤

«ጀልባው ፡ ተመልሶ ፡ መጣ!»

ጀልባው ፡ እየተቃረበ ፡ ሲመጣም ፡ ዋናው ፡ የመርከብ ፡ መኰንን ፡ ምልክት ፡ ሰጪውን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ፤

«ሰውየውን ፡ አግኝተው ፡ ይዘውታልን?»

«አይታየኝም ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡» ሲል ፡ ምልክት ፡ ሰጪው ፡ እንደመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ደስታ ፡ በሌለበት ፡ ድምጽ ፡ ተናገረ ።

ዋናው ፡ የመርከብ ፡ መኰንንም ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ አዛዡ ፡ ሄድ ፡ ብሎ ፤

«ሰውየውን ፡ ያገኙት ፡ አይመስለኝም ፡» አለ ።

«ዛቢያካ ፡» የተባለችው ፡ መርከብ ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡ አጠር ፤ ወፈር ፤ ደንደን ፤ ያለና ፡ በዕድሜውም ፡ መጠነኛ ፤ ያበጠ ፡ ጉንጩና ፡ አገጩም ፡ ሽበት ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ባደረገበት ፡ ጸጉር ፡ የተሸፈነ ፡ ዓይኑም ፡ ትንንሽና ፡ ክብ ፡ ሆኖ ፡ እንደንስር ፡ ዓይን ፡ የጮለ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሰው ፡ ትከሻውን ፡ በብስጭት ፡ እኳኳን ፡ አነቃነቀና ፡ እምብዛም ፡ ባልተደበቀ ፡ የመናደድ ፡ ስሜት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

«የተሳሳትክ ፡ ይመስለኛል ። በጀልባው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሥልጡንና ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡ መኰንን ፡ አለ ። ሰውየውን ፡ ባያገኘው ፡ ኖሮ ፡ እንዲህ ፡ ፈጥኖ ፡ ባልተመለሰም ፡ ነበር ።»

«ምልክት ፡ ሰጪው ፡ ግን ፡ ሊያየው ፡ አልቻለም ።»

«ምናልባት ፡ እጀልባው ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ይሆናል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ነገሩን ፡ አሁኑኑ ፡ ልናውቀው ፡ እንችላለን ።»

ጠቅላይ ፡ አዛዡ ፡ በመርከቧ ፡ መሽጋገሪያ ፡ ላይ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ መንጐራደደ ፡ ጀመረ ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ቆም ፡ እያለም ፡ ወደሚመለሰው ፡ ጀልባ ፡ ይመለከታል ። በመጨረሻም ፡ መነጽሩን ፡ ዓይኑ ፡ ላይ ፡ ደቀነና ፡ ተመለከተ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ የዳነውን ፡ ሰውየ ፡ ለማየት ፡ ባይችልም ፡ ቅሉ ፡ በጀልባ ፡ መሪው ፡ መኰንን ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ የደስታና ፡ የጸጥታ ፡ ምልክት ፡ ስላየ ፡ ሰውየውን ፡ ይዘው ፡ እንደተመለሱ ፡ እርግጠኛነት ፡ ተሰማው ።



በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የመርከብ ፡ አዛዡ ፡ ኩስትር ፡ ያለ ፡ ፊት ፡ በደስታ ፡ ፈገግታ ፡ አበራ ።

ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ ጀልባው ፡ ደረሰና ፡ እስከነቀዛፊዎቹ ፡ ወደመርከቧ ፡ ላይ ፡ አወጡት ።

መሪው ፡ መኰንን ፡ ቀድሞ ፡ ሲወጣ ፡ ቀዛፊዎቹ ፡ ተከተሉ ፤ ፊታቸው ፡ የሁሉም ፤ ከመቅላቱ ፡ በላይ ፡ አልቧቸዋል ፤ ደክሟቸዋልም ። ከመርከበኞቹ ፡ አንዱ ፡ የድካማቸውን ፡ ዋጋ ፡ ተሸክሟል ፤ ይሄውም ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ጥቁር ፡ ልጅ ፡ ነው ። ዕድሜው ፡ አስር ፡ ወይም ፡ አስራ ፡ አንድ ፡ ቢሆን ፡ ነው ። ሰውነቱ ፡ በውኃ ፡ እርሷል ፤ የከሳ ፡ አካላቱም ፡ በተቀዳደደ ፡ ሸሚዝ ፡ በገሚስ ፡ ተሸፍኗል ።

ትንሹ ፡ ልጅ ፡ በግሩ ፡ መቆም ፡ እንኳ ፡ አልቻለም ። ሰውነቱ ፡ በመላ ፡ ይንቀጠቀጣል ። ደስታና ፡ ጥርጣሬ ፡ በተቀላቀለበት ፡ ስሜትም ፡ መርከበኞቹን ፡ በትላላቅና ፡ በጐረጐዱት ፡ ዓይኖቹ ፡ ይመለከታቸዋል ። በእውነት ፡ ለመዳኑም ፡ ለማመን ፡ ያደገተው ፡ ይመስላል ። ከመርከበኞቹ ፡ አንዱ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ለመርከብ ፡ አዛዡ ፡ ተናገረ ፤

«ምስኪኑን ፡ ልጅ ፡ ስናወጣው ፡ እሞት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ እንደምንም ፡ አወጣነው ።»

«ወደማስታመሚያ ፡ ክፍል ፡ በፍጥነት ፡ ውሰዱት ፡» ሲል ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዡ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ።

ልጁ ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ ማስታመሚያው ፡ ክፍል ፡ ተወሰደ ፤ እዚያም ፡ ውኃውን ፡ ከሰውነቱ ፡ ላይ ፡ አድርቀው ፡ አሹትና ፡ አልጋ ፡ ውስጥ ፡ አስገብተው ፡ በብርድ ፡ ልብስ ፡ ሸፈኑት ፤ ከዚህ ፡ በ

ኋላ ፡ የመርከቧ ፡ ሐኪም ፡ በልጁ ፡ ጉሮሮ ፡ ውስጥ ፡ የአረቂ ፡ (ኮኛክ ፡) ጠብታ ፡ እያንጠባጠበ ፡ ሕክምናውን ፡ ጀመረ ።

ልጁም ፡ አረቂውን ፡ እንደውኃ ፡ ጥም ፡ እየጠጣ ፡ በሚያሳዝን ፡ ዓይን ፡ ወደአፉ ፡ ጠንቁሎ ፡ ያሳይ ፡ ጀመር ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፡ የመርከቧ ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሸራዎች ፡ እንደገና ፡ ተዘረጉና ፡ በአምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ «ዛቢያካ ፡» እንደገና ፡ ጉዞዋን ፡ ጀመረች ፤ መርከበኞቹም ፡ የተቋረጠውን ፡ ሥራቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ሁሉም ፡ ስለልጁ ፡ መዳንና ፡ ስለከሲታ ፡ ሰውነቱ ፡ ይጨዋወቱ ፡ ጀመር ።

አንዳንዶቹም ፡ ሁናቴውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደ ፡ ማስታመሚያው ፡ ክፍል ፡ ሲሄዱ ፤

«ሐኪሙ ፡ በደንብ ፡ ይጠብቀዋል ፤ ያድነዋልም!» የሚል ፡ መልስ ፡ ያገኙ ፡ ነበር ።

ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ኩርሹኖቭ ፡ የተባለው ፡ መርከበኛ ፡ ትንሹ ፡ ጥቁር ፡ ልጅ ፡ ጥቂት ፡ ማንኪያ ፡ ሾርባ ፡ ጠጥቶ ፡ እንደተኛ ፡ ወሬውን ፡ አምጥቶ ፡ ተናገረ ፤ ንግግሩንም ፡ በመቀጠል ፤

«ወጥቤቱ ፡ ሾርባውን ፡ የሠራው ፡ በተለይ ፡ ለርሱ ፡ ነበር ፤ ያውም ፡ የጠራ ፡ ሾርባ ፡ ነበር ፡» ሲል ፡ በማጋነንና ፡ በደስታ ፡ ተናገረ ። ሰውየው ፡ የታወቀ ፡ ውሸታም ፡ በመሆኑ ፡ የሚታመንበት ፡ አጋጣሚ ፡ ወሬ ፡ በማግኘቱ ፡ ደስ ፡ አለው ።

ይህን ፡ አጋጣሚ ፡ በሰፊው ፡ ሊጠቀምበት ፡ ስለፈለገም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ቀጠለ ፤

«የሐኪሙ ፡ እረዳት ፡ እንደነገረኝ ፡ ሐኪሙ ፡ ልጁን ፡ ሲመግበው ፡ ልጁ ፡ ይለፈልፍ ፡ ነበር ። ሾርባ ፡ ጨምርልኝ ፡ ማለቱ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ስኒውን ፡ ከሐኪሙ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ለመንጠቅም ፡ ሞከረ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሐኪሙ ፡ ጭማሪ ፡ ሊሰጠው ፡ አልፈ



ለገም ፡ «ቀስ ፡ በቀስ ፡ መላመድ ፡ አለበት ፤ አለበለዚያ ፡ ግን ፡ ይሞታል ፡» አለ ።

«ልጁስ ፡ ምን ፡ አደረገ?»

«ምንም ፡ አላደረገ ። ዝም ፡ አለ ።»

መርከበኞቹ ፡ በውኃ ፡ ገንዳው ፡ ዙሪያ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ ሶይኪን ፡ የተባለው ፡ የመርከብ ፡ አዛዥ ፡ አሽከር ፡ የጌታውን ፡ የሲጋራ ፡ ቁራጭ ፡ እያጨሰ ፡ መጣ ። ወዲያውኑ ፡ ሁሉም ፡ ወደርሱ ፡ ተመለከቱና ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁት ፤

«ሶይኪን ፤ ትንሹን ፡ ጥቁር ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ታውቃለህ?»

ጸጉረ ፡ ቀዩና ፡ ጠቃጠቆ ፡ ያለበት ፡ ሶይኪን ፡ ንጹሕ ፡ የመርከበኛ ፡ ሸሚዙን ፡ ለብሶና ፡ የሸራ ፡ ጫማውን ፡ አድርጎ ፡ እንዲሁም ፡ በኩራት ፡ መልክ ፡ ሲጋሩን ፡ ቡልቅ ፡ ቡልቅ ፡ እያደረገ ፡ ጉዳዩን ፡ በቅርብ ፡ እንደሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ ተናገረ ፤

«ልጁን ፡ ምን ፡ እናደርገዋለን? ወደ ፡ « ኬፕ ፡» ስንደርስ ፡ አወርደን ፡ እንተወዋለና ።»

ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብሎም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በትዕቢት ፡ ተናገረ ፤

«እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል?»

«ጥቁሮችም ፡ እንደኔና ፡ እንደ ፡ አንተው ፡ የግዜር ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡» ሲል ፡ የመርከቧ ፡ አናጢ ፡ ዛኻሪች ፡ መለሰለት ።

የቀሩትም ፡ በዛኻሪች ፡ መልስ ፡ መስማማታቸውን ፡ ባንድ ፡ ድምጽ ፡ ገለጹ ።

«ልጁ ፡ ወደ ፡ «ኬፕ ፡» ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ቤቱን ፡ እንዴት ፡ ፈልጎ ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል? መቸም ፡ እንደሌላው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ አያጣም ፡» አለ ፡ አንደኛው ፡ መርከበኛ ።

በ«ኬፕ ፡» ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጥቁሮች ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ ከየት ፡ እንደመጣ ፡ ሊያውቁ ፡ ይችላሉ ፡» አለ ፡ ሶይኪን ። የጌታውን ፡ የሲጋራ ፡ ቁራጭ ፡ ጨርሶም ፡ ሄደ ።

«እንዲህ ፡ የሚንቀባረረው ፡ ማን ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ነው? ወራዳ!» አለና ፡ አናጢው ፡ አጉረመረመ ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

በማግሥቱ ፡ ትንሹ ፡ ጥቁር ፡ ልጅ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ገና ፡ ደካማ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ ድንጋጤውና ፡ ፍርሃቱ ፡ አለፈለት ። ወፍራሙና ፡ ደጉ ፡ ሐኪምም ፡ ሰፊ ፡ ፈገግታውን ፡ እያሳየ ፡ ጉንጩን ፡ መታ ፡ መታ ፡ አደረገና ፡ አንድ ፡ ስኒ ፡ ሙሉ ፡ ሾርባ ፡ እንዲጠጣ ፡ አዘዘለት ። ልጁም ፡ ትኩሱን ፡ ሾርባ ፡ ግልብጥ ፡ አድርጎ ፡ ጠጣና ፡ በትልልቆቹ ፡ ዓይኖቹ ፡ ሐኪሙን ፡ በምሥጋና ፡ ስሜት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ተመለከተው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐኪሙ ፡ ልጁ ፡ እባሕር ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደ ወደቀና ፡ እህል ፡ ሳይበላም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ እንደቆየ ፡ ሊጠይቀው ፡ ሞከረ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ሐኪሙ ፡ ሐሳቡን ፡ ለመግለጽ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ እ ያሳየ ፡ ቢሞክርም ፡ ቅሉ ፤ ከልጁ ፡ ጋር ፡ ሊግባቡ ፡ አልቻሉም ። ልጁም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሐኪሙ ፡ ከሚያውቀው ፡ እንግሊዝኛ ፡ የበለጠ ፡ ቢናገርም ፡ ሁለቱም ፡ የሚያውቁትን ፡ ጥቂት ፡ ቃላት ፡ እርስ ፡ በእርስ ፡ በማጋጨት ፡ ጭራሹኑ ፡ የወፍ ፡ ቋንቋ ፡ አደረጉት ።

ስለዚህ ፡ ሁለቱም ፡ ለመግባባት ፡ ሳይችሉ ፡ ቀሩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐኪሙ ፡ ፔቲያ ፡ የተባለውን ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ እንዲጠራ ፡ ረዳቱን ፡ ጠየቀው ።



«ፔቲያ ፤ አንተ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ደህና ፡ አድርገህ ፡ ታውቃለህና ፡ እስቲ ፡ ይህንን ፡ ልጅ ፡ አናግረው ። እኔ ፡ እንደሆንኩ ፡ አልቻልኩም ፡» አለ ፡ ሐኪሙ ፡ እየሳቀ ። ንግግሩንም ፡ በመቀጠል ፤ «በሁለትና ፡ በሦስት ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ከሕመምተኞች ፡ ክፍል ፡ እንዲነሣ ፡ እፈቅድለታለሁ ፡ ብለህ ፡ ንገረው ፡» አለ ።

ወጣቱ ፡ እጩ ፡ መኰንንም ፡ በልጁ ፡ አልጋ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጦ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ይጠይቀው ፡ ጀመር ። ልጁ ፡ እንዲገባውም ፡ አጫጭር ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ከመምረጡ ፡ ሌላ ፡ ቃሉንም ፡ አጥርቶ ፡ ይናገር ፡ ነበር ። ልጁም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ነገሩ ፡ በሙሉ ፡ ባይገባውም ፡ አብዛኛው ፡ ስለገባው ፡ ብዙ ፡ ቃላት ፡ እያከታተለና ፡ በእጁም ፡ በፊቱም ፡ ምልክት ፡ እየሰጠ ፡ ጥያቄውን ፡ ለመመለስ ፡ ተጣደፈ ።

አስቸጋሪ ፡ ከሆነ ፡ ከብዙ ፡ ንግግር ፡ በኋላ ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ፡ ልጁ ፡ በሰጠው ፡ መልስና ፡ ምልክት ፡ መሠረት ፡ በገበታ ፡ ቤት ፡ ለመኰንኖቹ ፡ የልጁን ፡ ታሪክ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ባጭሩ ፡ ገለጸ ፤

ልጁ ፡ «ቤትሲ ፡» በምትባል ፡ ባንድ ፡ ያሜሪካ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ነበር ። የዚች ፡ መርከብ ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡ ለሆነው ፡ ሰውየም ፡ («አንድ ፡ ትልቅ ፡ አውሬ ፡ ነበር ፡» ሲል ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ፡ ጣልቃ ፡ አስገብቶ ፡ ተናገረ፡) ። ይህ ፡ ልጅ ፡ ለመርከብ ፡ አዛዥ ፡ ልብስ ፡ አጣቢ ፤ ጫማ ፡ ጠራጊና ፡ እንዲሁም ፡ አረቂና ፡ ቡና ፡ አሳላፊ ፡ ነበር ። አዛዡ ፡ «ቦይ ፡» ብሎ ፡ ይጠራው ፡ ነበር ፤ ትንሹ ፡ ጥቁር ፡ ልጅም ፡ ስሜ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አምኖ ፡ ነበር ። አባቱና ፡ እናቱ ፡ ማን ፡ እንደነበሩም ፡ ጨርሶ ፡ አያውቅም ፡ የመርከቧ ፡ አዛዡ ፡ ልጁን ፡ የገዛው ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ካንድ ፡ የሞዛምቢክ ፡ የባሪያ ፡ ገበያ ፡ ነበር ፤ ዘወትርም ፡ ይደበድበው ፡ ነበር ። «ቤትሲ ፡» የተባለችዋ ፡ መርከብ ፡ የባሪያ ፡ ጭነት ፡ ይዛ ፡ ከሴኔጋል ፡ ወደ ፡ ሪዎ ፡ ትጓዝ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ ካንድ ፡ ሌላ ፡ መርከብ ፡ ጋር ፡

ተጋጭታ ፡ ሰመጠች ። (እጬ ፡ መኰንኑ ፡ ይህን ፡ ታሪክ ፡ የገለጸው ፡ ልጁ ፤ እግም! እግም! እግም! የሚል ፡ ድምጽ ፡ በማሰማትና ፡ በቡጢ ፡ ግድግዳውን ፡ በመምታት ፡ ባሳየው ፡ ምልክት ፡ መሠረት ፡ ነው ።) ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ አንድ ፡ የሚንሳፈፍ ፡ ግንድ ፡ አግኝቶ ፡ እሱ ፡ ላይ ፡ በመጣበቅ ፡ ሁለት ፡ ቀናት ፡ ያህል ፡ ቆየ ።

ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ የሚደንቀው ፡ ልጁ ፡ በርኅራኄ ፡ በመያዙ ፡ ያሳየው ፡ መገረምና ፡ የፍርሃት ፡ መልክ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሐኪሙን ፤ እረዳቱንና ፡ እጬ ፡ መኰንኑን ፡ ሲመለከት ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ የተወራጅ ፡ ሰው ፡ የምስጋና ፡ ስሜት ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በተረፈ ፡ የሚያንጸባርቀው ፡ ገላው ፡ በግርፋት ፡ ሰንበር ፡ ከመሸፈኑም ፡ ሌላ ፡ በጣም ፡ ቀጭንና ፡ ከሲታ ፡ ነበር ። የጉድን ፡ አጥንቱም ፡ ዘልቆ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

እጬ ፡ መኰንኑ ፡ ያስተረጐመው ፡ ታሪክና ፡ ሐኪሙም ፡ የሰጠው ፡ ማስረጃ ፡ መኰንኖቹን ፡ አስደነቃቸው ። ልጁ ፡ በኬፕታውን ፡ ከተማ ፡ በሚገኘው ፡ የሩሲያ ፡ ቆንስላ ፡ ጠባቂነት ፡ እንዲቆይና ፡ መኰንኖቹም ፡ ለልጁ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያዋጡ ፡ ከመኰንኖቹ ፡ አንዱ ፡ አሳሰበ ። ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ የእጬ ፡ መኰንኑ ፡ አሽከር ፡ አርቴሚ ፡ ሙኺን ፡ (አርቱሽካ ፡ ብለው ፡ ይጠሩት ፡ ነበር ፡) ታሪኩን ፡ ለተራ ፡ መርከበኞቹ ፡ በነገራቸው ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ተደነቁ ። እሱም ፡ አሜሪካዊው ፡ የመርከብ ፡ አዛዥ ፡ ልጁን ፡ እንዴት ፡ ያሰቃየው ፡ እንደነበረ ፡ ከራሱ ፡ ፈጥሮ ፡ እየጨማመረ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ማውራት ፡ ጀመረ ፤

«ጉበዝ! በየቀኑ ፡ ልጁን ፡ ያሰቃየው ፡ ነበር ። ለትንሹ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ልጁን ፡ እስኪደማ ፡ ድረስ ፡ በቡጢ ፡ ይመታው ፡ ነበር ። ወፍራም ፡ የጠፍር ፡ አለንጋውን ፡ ከተሰቀለበት ፡ አንስቶም ፡ ይገርፈው ፡ ነበር ።» የልጁን ፡ ስቃይ ፡ አጉልቶ ፡ ለመግለጽ ፡ ሲልም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ቀጠለ ፤ «ልጁ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጥቁር ፡ ቢሆን



ም ፡ ቅሉ ፡ ምስኪን ፡ ልጅ ፡ መሆኑን ፡ ያ ፡ አሳማ ፡ ሰውየ ፡ አይገነዘብም ፡ ነበር ። የልጁ ፡ ጀርባ ፡ በግርፋት ፡ ሰንበር ፡ ተዥጐርጉሯል ። ሐኪሙ ፡ እንዳለው ፡ ሲመለከቱት ፡ በጣም ፡ ያሰቅቃል፡» አለ ፡ አርቱሽካ ፡ ወሬውን ፡ በማጣፈጥ ።

መርከበኞቹም ፡ እራሳቸው ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ገባሮች ፡ ስለነበሩ ፡ ግርፋትንና ፡ መደብደብን ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ ያወቃሉ ፤ ስለዚህ ፡ የልጁን ፡ ስቃይ ፡ ለመረዳት ፡ የአርቱሽካ ፡ ወሬ ፡ ማሳመር ፡ አላስፈለጋቸውም ፡ ነበር ። ያንን ፡ ሰይጣን ፡ ያሜሪካ ፡ የመርከብ ፡ አዛዥም ፡ ዓሣነባሪ ፡ አልበላው ፡ እንደሆን ፡ ሌላ ፡ አሰቃቂ ፡ ነገር ፡ ይደርስበት ፡ ዘንድ ፡ ተመኙ ።

«የኛ ፡ ገበሬዎች ፡ ከገባርነት ፡ ቀንበር ፡ ነፃ ፡ ወጥተዋል ፡ ባሜሪካ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ የገባርነት ፡ ቀንበር ፡ ገና ፡ እንዳለ ፡ ነው ፡ ይመስለኛል? » አለ ፡ ጠና ፡ ካሉት ፡ መርከበኞች ፡ አንደኛው ።

«አዎን ፡ ገና ፡ እንዳለ ፡ ነው ።»

«የሚያስገርም ፡ ነው! ታዲያ ፡ ነፃ ፡ ሕዝቦች ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ እንዴት ፡ ነው!»

«ለነሱ ፡ ጥቁሮቹ ፡ እንደገባሮች ፡ ናቸው ፡» ሲል ፡ አርቱሽካ ፡ ከመኰንኖቹ ፡ ከለቀመው ፡ ወሬ ፡ ለማስረዳት ፡ ቃጣ ። ንግግሩንም ፡ በመቀጠል ፤ «እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚዋጉት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ግማሾቹ ፡ አሜሪካኖች ፡ ጥቁሮቹን ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ ይፈልጋሉ ። ባሪያ ፡ ያላቸው ፡ ወገኖች ፡ ግን ፡ ባሮቻቸውን ፡ እንደያዙ ፡ ለመቆየት ፡ ይፈልጋሉ ። ስለዚህ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይተላለቃሉ ። መኰንኖቹ ፡ እንደሚሉት ፡ ድል ፡ የሚያደርጉት ፡ የነፃ ፡ አውጭዎቹ ፡ ክፍል ፡ ናቸው ። ድል ፡ ባደረጉም ፡ ጊዜ ፡ ባለባሪያዎቹን ፡ ክፍሎች ፡ ድምጥማጣቸውን ፡ ያጠፏቸዋል ፡» አለ ፡ ጨመር ፡ አድርጎ ።

«ምንም ፡ አይደለም ፤ እግዚአብሔር ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ይሆናል ። ጥቁርም ፡ ሰው ፡ እንደሌላው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ነፃነቱን ፡ ይፈልጋል ። ወፍ ፡ እንኳ ፡ በሽቦ ፡ ቤት ፡ ስትታሰር ፡ ደስ ፡ አይላትም ። የሰውም ፡ ልጅ ፡ ቢሆን ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፡» አለ ፡ አናጢው ፡ ዛኻሪች ።

የባሕር ፡ ላይ ፡ ሕይወት ፡ አደገኛ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ የተናገረው ፡ ጠየም ፡ ያለ ፡ ወጣትና ፡ አዲስ ፡ ገብ ፡ መርከበኛ ፡ ወሬውን ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ ሲያዳምጥ ፡ ቆየና ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀ ፤

«እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ያዳንነው ፡ ጥቁር ፡ ልጅ ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ነው?»

«እንዴታ ፤ ይሆናልና ። ምን ፡ ይመስልሃል ፡ ላንተ?» አለ ፡ አርቱሽካ ፡ በልበ ፡ ሙሉነት ። በሕሊናው ፡ ግን ፡ (ያሜሪካንን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ሕግ ፡ ስለማያውቅ ፡) በሙሉ ፡ እርግጠኛ ፡ አል ነበረም ።

ለእሱ ፡ እንደመሰለው ፡ ግን ፡ ልጁ ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። ያ ፡ እርጉም ፡ የመርከብ ፡ አዛዥ ፡ እንደሆን ፡ ያሣነባሪ ፡ ምሳ ፡ ሆኗል ፤ ስለዚህ ፡ ምን ፡ የሚያስፈራ ፡ ነገር ፡ አለ?

እንዲህ ፡ ሲልም ፡ ቀጠለ ፤

«ልጁ ፡ አሁን ፡ የሚያስፈልገው ፡ እ«ኬፕ ፡» ስንደርስ ፡ አዲስ ፡ ፓስፖርት ፡ ማግኘት ፡ ነው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ወደፈለገበት ፡ መሄድ ፡ ይችላል ።»

ይህ ፡ ተንኰለኛ ፡ የፓስፖርት ፡ ሐሳብ ፡ ሌላውን ፡ ሁሉ ፡ ጥርጣሬውን ፡ ስላስወገደለት ፤ ወጣቱ ፡ መርከበኛ ፤

«ይኸው ፡ ነው!» አለ ፡ በደስታ ።

«በውነት ፤ መንገዱ ፡ ይኸው ፡ ነው!»

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግነት ፡ የሚታይበት ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ ፊቱና ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ የቡችላ ፡ ዓይኖቹ ፡ በዕድለ ፡ ቢሱ ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ ታሪክ ፡ ፍጻሜ ፡ ላይ ፡ እፎይ ፡ በማለት ፡ በደስታ ፡ አበሩ ።

ብርሃን ፡ የለበሰው ፡ ምሽት ፡ ወዲያውኑ ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ወደሆነ ፡ የሞቃት ፡ አገር ፡ ሌሊት ፡ ተለወጠ ። ወይን ፡ ጠጅ ፡ የመሰለው ፡ ሰማይ ፡ በሚሊዮን ፡ በሚቆጠሩ ፡ ከዋክብት ፡ ተንቆጥቁጧል ። ራቅ ፡ ብሎ ፡ የሚታየው ፡ ውቅያኖስም ፡ ጽልመት ፡ ለብሷል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቻ ፡ በመርከቧ ፡ ጐንና ፡ ጐን ፡ ያለው ፡ ውኃ ፡ እንደ ፡ ድኝ ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ ይል ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ የጸሎት ፡ ምልክት ፡ ተሰጠ ። ኋላም ፡ ተረኛ ፡ ጠባቂ ፡ ያልሆኑት ፡ መርከበኞች ፡ የሌሊት ፡ ዕቃዎቻቸውን ፡ ወደ ፡ መድረኩ ፡ ወስደው ፡ ተኙ ።

ተረኛ ፡ ጠባቂዎቹም ፡ ተቀመጡና ፡ ሌሊቱ ፡ ቶሎ ፡ እንዲያልፍላቸው ፡ በቀስታ ፡ ይጨዋወቱ ፡ ጀመር ። ያን ፡ ዕለት ፡ ሌሊት ፡ ሁሉም ፡ ሲያወሩ ፡ የነበረው ፡ ስለ ፡ ትንሹ ፡ ጥቁር ፡ ልጅ ፡ ነበር ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሐኪሙ ፡ እንደተለመደው ፡ ከጧቱ ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ የሕመምተኞችን ፡ ክፍል ፡ ሲጐበኝ ፡ ልጁ ፡ መዳኑንና ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ መድረክ ፡ ሄዶም ፡ ከመርከበኞቹ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ለመብላት ፡ እንደሚችል ፡ አረጋገጠለት ። ሐኪሙ ፡ ለልጁ ፡ ይህን ፡ ያስታወቀው ፡ በጁ ፡ ምልክት ፡ እየሰጠ ፡ ነበር ። ልጁም ፡ ከሕመሙ ፡ ፈጽሞ ፡ በመዳኑና ፡ በደስታ ፡ በመመላቱም ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ከሞት ፡ አፋፍ ፡ መትረፉን ፡ ጨርሶ ፡ በመዘንጋቱ ፡ ሐኪሙ ፡ የሚለውን ፡ በፍጥነት ፡ ለመረዳት ፡ ቻለ ።

ከአልጋው ፡ ውስጥ ፡ ዘሎ ፡ ወጣ ፤ ልብሱን ፡ እንደለበሰም ፡ ለመሮጥና ፡ ወደ ፡ መድረኩ ፡ ላይ ፡ ሄዶ ፡ ፀሐይ ፡ ለመሞቅ ፡ ፈለገ ። ነገር ፡ ግን ፡ በከሳው ፡ ጥቁር ፡ አከላቱ ፡ እንደ ፡ ዶኒያ ፡ ያጠለቀው ፡ የመርከበኛ ፡ ሸሚዝ ፡ ሐኪሙን ፡ ከልብ ፡ አሳቀው ። የሐኪሙም ፡ ረዳት ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ ሳቀ ። ልጁም ፡ ሐኪሙ ፡ ሸሚዙን ፡ እየጐተተ ፡ በሳቅ ፡ የሚንፈቀፈቀበት ፡ ምክንያት ፡ ስላልገባው ፡ ቆሞ ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

ልጁ ፡ ከሸሚዙ ፡ ውስጥ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ወጥቶ ፡ በሕመምተኞች ፡ ክፍል ፡ በር ፡ ራቁቱን ፡ ሊወጣ ፡ ሲል ፡ የሐኪሙ ፡ ረዳት ፡ ያዘና ፡ መለሰው ። ሐኪሙም ፡ እየሳቀ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ኖ-ኖ-ኖ...»

ዶኒያ ፡ ሸሚዙን ፡ እንዲያጠልቅም ፡ በምልክት ፡ ነገረው ።

«ምን ፡ እናለብሰዋለን ፡ ፊሊፖቭ?» ሲል ፡ ሐኪሙ ፡ አንድ ፡ ጸጉረ ፡ ጥቅልና ፡ ደርጀት ፡ ያለ ፡ የሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ጠየቀ ። «ጐበዝ! በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አላሰብንበትም ፡ ነበር ፤ አዎን?»

«እርግጥ ፡ ነው ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ አላሰብንበትም ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ሸሚዙን ፡ ከወደጉልበቱ ፡ ገደማ ፡ ቆርጠን ፡ እወገቡ ፡ ላይ ፡ ቀበቶ ፡ ብናስርበት ፡ ጨዋ ፡ ያስመስለዋል ፡» ሲል ፡ መለሰ ፡ ፊሊፖቭ ። ይህ ፡ ሰው ፡ ንግግር ፡ ለማሳመር ፡ ሲል ፡ (መርከበኞች ፡ እንደሚሉት ፡ «ሊቅ ፡ ለመምሰል ፡») ያልሆነ ፡ ቃል ፡ ጣልቃ ፡ ያስገባል ።

«ጨዋ ፡ ያስመስለዋል ፡ ማለትህ ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው?» ሲል ፡ ሐኪሙ ፡ በፈገግታ ፡ ጠየቀው ።



«ጨዋ ፡ ማለቴ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፤ «ጨዋ ፡» ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆንም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ያውቃል ፡ » አለ ፡ ፊሊፖቭ ፡ በቅያሜ ፡ ድምጽ ። «ንጹሕና ፡ ጥዱ ፡ ማለት ፡ ነው ።»

«አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ጨዋ ፡ ያስመስለዋል ፡ ለማለት ፡ አልደፍርም ። ይልቁንስ ፡ መሳቂያ ፡ ያደርገዋል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዋናውን ፡ አዛዥ ፡ አስፈቅጄ ፡ በልኩ ፡ ልብስ ፡ እስኪሰፋለት ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መልበስ ፡ አለበት ። »

«በልኩ ፡ ልብስ ፡ ለማሰፋት ፡ አያደግትም ። ከመርከበኞቹ ፡ መካከል ፡ ልብስ ፡ ሰፊዎች ፡ ስላሉ ፤ ሊሰፉለት ፡ ይችላሉ ።»

«ደህና ፡ ነው ፤ እስከዚያው ፡ ድረስ ፡ ግን «የጨዋ ፡» ልብስ ፡ ያልከውን ፡ አዘጋጅለት ፡»።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሩ ፡ በቀስታና ፡ በጨዋ ፡ ደንብ ፡ ተቆረቆረ ።

«ማነው?» ሲል ፡ ሐኪሙ ፡ ጮኸ ። «ግባ!»

ፊቱ ፡ ቀላ ፡ ያለና ፡ አበጥ ፡ ያለ ፤ ጢሙ ፡ ቡናማ ፤ ዓይኑ ፡ ብስል ፡ ቀይና ፡ ቁልጭ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ደግነትንና ፡ ደስታን ፡ ያዘለ ፡ ሰው ፡ በበሩ ፡ በኩል ፡ ብቅ ፡ አለ ። ቀጥሎም ፡ አነስተኛ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የደረጀና ፡ ጡንቻማ ፡ ሰውነቱ ፡ በሙሉ ፡ ታየ ። ይህ ፡ ሰውየ ፡ መርከበኛው ፡ ኢቫን ፡ ሉችኪን ፡ ነው ።

ኢቫን ፡ ሉችኪን ፡ ዕድሜው ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ በባሕር ፡ ኃይል ፡ ውስጥ ፡ አስራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሠርቷል ። በባሕር ፡ ላይ ፡ ከጥሩዎቹ ፡ መርከበኞች ፡ አንደኛው ፡ ሲሆን ፡ በወደብ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ከሌላቸው ፡ ከዋናዎቹ ፡ ሰካራሞች ፡ አንደኛው ፡ ነው ። ለመጠጥ ፡ ሲል ፡ የለበሰውን ፡ ልብስ ፡ ሽጦ ፡ በውስጥ ፡ ልብሱ ፡ ብቻ ፡ ወደመርከቧ ፡ ይመለሳል ፤ በማግሥቱም ፡ ጧት ፡ በጥብቅ ፡ ይገረፋል ።

ሉችኪን ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ ሲገባ ፤

«እኔ ፡ ነኝ ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ!» አለ ፡ በጐረና ፡ ድምጽ ። ቀጭን ፡ ሌጣ ፡ እግሩን ፡ እየጠራረገም ፡ በጣቱ ፡ ሱሪውን ፡ ነካ ፡ ነካ ፡ ያደርግ ፡ ጀመረ ።

በሌላው ፡ እጁ ፡ አንድ ፡ ጥቅል ፡ ነገር ፡ ይዞ ፡ ነበር ።

ስካር ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መጥፎ ፡ ልማድ ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ፡ በሚሰማቸው ፡ በሃፍረትና ፡ በኃጢአት ፡ ስሜት ፡ ሐኪሙን ፡ ተመለከተው ።

«ምን ፡ ሆነሃል ፡ ሉችኪን? አሞሃልን?»

«የለም ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፤ ለጥቁሩ ፡ ልጅ ፡ ልብስ ፡ አምጥቻለሁ ። ልብስ ፡ እንደሌለው ፡ አየሁና ፡ ወርድና ፡ ቁመቱን ፡ ለክቼ ፡ ይህን ፡ ልብስ ፡ ሰፋሁለት ። እንድሰጠው ፡ ይፈቀድልኛል ፡ ጌታዬ?»

«እንዴታ ። እንዲያውም ፡ ገላገልከን ። ልጁን ፡ እንዴት ፡ እንደምናለብሰው ፡ ጨንቆን ፡ ነበር ። አንተ ፡ ከኛ ፡ ቀደም ፡ ብለህ ፡ ማሰብህ ፡ በጀ ፡ » ሲል ፡ ድንገተኛ ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ።

«የሰፋሁት ፡ በትርፍ ፡ ጊዜዬ ፡ ነው ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡» አለ ፡ ሉችኪን ፡ በይቅርታ ፡ መልክ ። ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ጥቅሉን ፡ ፈታና ፡ ከሸራ ፡ የተሠራ ፡ ትንሽ ፡ የመርከበኛ ፡ ሸሚዝ ፡ አወጣ ። ሸሚዙን ፡ አራግፎም ፡ ለሐኪሙ ፡ በተናገረው ፡ የሃፍረት ፡ ድምጽ ፡ ሳይሆን ፡ ደስታና ፡ ፍቅር ፡ በተመላበት ፡ ድምጽ ፡ ወደ ፡ ልጁ ፡ እየተመለከተ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ሸሚዙን ፡ ሰጠው ፤

«እንካ ፡ ማክሲምካ! ወዳጄ ፡ ልቤ ፡ ቬሪ ፡ ጉት ፡ ሸሚዝ ፡ ነው! በል ፡ አጥልቀውና ፡ እንዴት ፡ እንደሚያምርብህ ፡ እንየው።»

«ማክሲምካ ፡ ብለህ ፡የምትጠራው ፡ ለምንድን ፡ ነው?» ሲል ፡ ሐኪሙ ፡ በፈገግታ ፡ ጠየቀው ።

«ያዳንነው ፡ በቅዱስ ፡ ማክሲምስ ፡ ዕለት ፡ ስለሆነ ፡ ማክሲ



ምካ ፡ መባል ፡ አለበት ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ የመጠሪያ ፡ ስም ፡ ስለሌለው ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ማውጣት ፡ አለብን ።»

ትንሹ ፡ ጥቁር ፡ ልጅ ፡ አዲሱንና ፡ ንጹሑን ፡ ሸሚዝ ፡ ባጠለቀ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሉችኪን ፡ የሰፋውን ፡ ሸሚዝ ፡ በብዙ ፡ ጐን ፡ እየተመለከተና ፡ አልፎ ፡ አልፎም ፡ ሳብ ፡ ጠበቅ ፡ እያደረገ ፡ ጥሩ ፡ ልብስ ፡ ለመስፋቱ ፡ በልቡ ፡ አመነ ።

«እንግዲህ ፡ እመድረኩ ፡ ላይ ፡ ወጥተህ ፡ ፀሐይ ፡ መሞቅ ፡ ትችላለህ! ይዤው ፡ ልውጣ ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ?»

ሐኪሙም ፡ የፈቃደኛነት ፡ ፈገግታ ፡ በማሳየት ፡ ራሱን ፡ ነቀነቀ ፤ ሉችኪንም ፡ የልጁን ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ እየመራ ፡ ወደመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ወስዶ ፡ ከሌሎቹ ፡ መርከበኞች ፡ ጋር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አስተዋወቀው ፤

«እነሆ ፡ ማክሲምካ! ካሁን ፡ ወዲያ ፡ ጨካኙ ፡ አሜሪካዊ ፡ የበደለውን ፡ ሁሉ ፡ ይረሳል ። የሩሲያ ፡ መርከበኞች ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እንደማይጨክኑበትም ፡ ያውቃል ።»

ልጁን ፡ በፍቅር ፡ መልክ ፡ ትከሻውን ፡ ቸብ ፡ ቸብ ፡ እያደረገና ፡ ከርዳዳ ፡ ጸጉሩን ፡ እያሻሸም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ቆብም ፡ እንሰፋልሃለን ፡ ወዳጄ ፡ ልቤ ፤ ጫማም ፤ ሁሉንም ፡ በሰዓቱ ፡ እናደርስልሃለን!»

ልጁ ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ አልገባውም ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ በመርከበኞቹ ፡ ከርዳዳ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ከሚታየው ፡ የወዳጅነት ፡ ፈገግታ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እንደማይጨክኑበት ፡ ለመረዳት ፡ ቻለ ።

እርሱም ፡ በበኩሉ ፡ ፈገግ ፡ እያለና ፡ ወተት ፡ የመሰለ ፡ ነጭ ፡ ጥርሱን ፡ እያሳየ ፡ ያገሩን ፡ የደቡብ ፡ ፀሐይ ፡ መሞቁን ፡ ቀጠለ ።

ከዚያን ፡ ቀን ፡ ጀምሮም ፡ ስሙ ፡ ማክሲምካ ፡ ተባለ ።

## ምዕራፍ ፤ ፮ ።

ኢቫን ፤ ሉችኪን ፤ ልጁ ፤ አዲስ ፤ ልብሱን ፤ እንደለበሰ ፤ ከሌሎቹ ፤ መርከበኞች ፤ ጋር ፤ ካስተዋወቀው ፤ በኋላ ፤ ለማክሲምካ ፤ ልዩ ፤ ጥንቃቄ ፤ እንደሚያደርግለት ፤ አስታወቀ ። ይህን ፤ መብት ፤ የወሰደው ፤ ለልጁ ፤ አዲስ ፤ ልብስ ፤ ስለሰፋለትና ፤ ስም ፤ ስላወጣለት ፤ ነው ።

በአሜሪካዊው ፤ መርከበኛ ፤ አዛዥ ፤ እጅ ፤ የተሰቃየው ፤ ከሲታውና ፤ የተጐሳቆለው ፤ ጥቁር ፤ ልጅ ፤ በሉችኪን ፤ ልቦና ፤ ውስጥ ፤ የተለየ ፤ ሐዘን ፤ አሳደረበት ፤ (የራሱም ፤ ሕይወትና ፤ በተለይም ፤ የልጅነት ፤ አስተዳደጉ ፤ የሚያስደስት ፤ አልነበረም ፤)። በዚህ ፤ ምክንያት ፤ ልጁ ፤ በመርከቧ ፤ ላይ ፤ ባለበት ፤ ጊዜ ፤ ሁሉ ፤ ደስ ፤ እንዲለው ፤ ለማድረግ ፤ ወሰነ ። ዳሩ ፤ ግን ፤ ስለዚህ ፤ ሐሳቡ ፤ አንድም ፤ ቃል ፤ አልተናገረም ። እንደቀሩት ፤ ተራ ፤ መስኰባውያን ፤ ሁሉ ፤ ስሜቱን ፤ በሰው ፤ ፊት ፤ ለመግለጽ ፤ ያፍር ፤ ነበር ። የሆነ ፤ ሆኖ ፤ ፔትሮቭ ፤ ወደተባለው ፤ መርከበኛ ፤ አተኩሮ ፤ እያየ ፤ «ምስኪኑን ፤ ልጅ ፤ የሚያሳዝን ፤ አመጸኛ ፤ ሰው ፤ ቢኖር ፤ አሳየዋለሁ ፤» ሲል ፤ አስታወቀ ። ይህ ፤ ፔትሮቭ ፤ የተባለ ፤ መርከበኛ ፤ በበጥባጭነቱ ፤ የታወቀ ፤ ከመሆኑ ፤ ሌላ ፤ በአዲስ ፤ ገብና ፤ በአፋራም ፤ መርከበኞች ፤ መቀለድ ፤ ልማዱ ፤ ነው ።

ሉችኪን ፤ ንግግሩን ፤ ለማብራራት ፤ እንዲህ ፤ ሲል ፤ ቀጠለ ፤

«ኋላ ፤ እንዳትሳሳቱ ፤ ማንም ፤ ሰው ፤ ቢሆን ፤ አጠናግረዋለሁ ። በልጆች ፤ ላይ ፤ መጨከን ፤ የኃጢአት ፤ ኃጢአት ፤ ነው ። ጥቁርም ፤ ሆነ ፤ ነጭም ፤ ሆነ ፤ አንድ ፤ ነው ። ልጅ ፤ ልጅ ፤ ነው ፤ ስለዚህ ፤ እዘኑለት ።»

ሉችኪን ፤ በገዛ ፤ ፈቃዱ ፤ የማክሲምካ ፤ ጠባቂ ፤ ለመሆን ፤ በወሰደው ፤ እርምጃ ፤ ተስማሙ ። ሆኖም ፤ አብዛኞቹ ፤ ይህን ፤ አስቸጋሪ ፤ ተግባር ፤ ችሎ ፤ የሚፈጽም ፤ ለመሆኑ ፤ ጥርጣሬ ፤ ገብቷቸው ፤ ነበር ።



እንደርሱ ፤ ያለ ፤ በስካር ፤ ያረጀና ፤ ምግባር ፤ የሌለው ፤ ሰው ፤ እንዴት ፤ አድርጎ ፤ የልጁ ፤ ጠባቂ ፤ ለመሆን ፤ ይችላል?

ከሽማግሌዎቹ ፤ መርከበኞች ፤ አንደኛው ፤ በውስጠ ፤ ወይራ ፤ ንግግር ፤ እንዲህ ፤ ሲል ፤ ተናገረ ፤

«እህ! ለልጁ ፤ እንደ ፤ ሞግዚት ፤ ቢጤ ፤ ልትሆነው ፤ ነዋ!»

«አዎን ፤ ሞግዚቱ ፤ ልሆነው ፤ ነው!» አለ ፤ ሉችኪን ፤ ፈገግ ፤ እያለና ፤ የሰዎቹን ፤ የሽሙጥ ፤ ፈገግታ ፤ ናቅ ፤ እያደረገ ። ቀጥሎም ፤ እንዲህ ፤ አለ ፤ «እኔ ፤ ለዚህ ፤ ተግባር ፤ የማልበቃ ፤ የመሰላችሁ ፤ በምን ፤ ምክንያት ፤ ነው? ልጁ ፤ እንደሆን ፤ የባለጺጋ ፤ ሰው ፤ ልጅ ፤ አይደለም! እሱ ፤ የሚያስፈልገው ፤ ልብስ ፤ ነው ። ስለዚህ ፤ ሌላ ፤ ልብስና ፤ ጫማም ፤ ቆብም ፤ እሰፋለታለሁ ። ሐኪሙ ፤ ከዕቃ ፤ ቤት ፤ ውስጥ ፤ የመንግሥት ፤ ልብስ ፤ እፈልግለታለሁ ፤ ብሏል ። ማክሲምካ ፤ ከኛ ፤ ተለይቶ ፤ «ኬፕ ፤» ሲቀር ፤ ስለመስኰብ ፤ መርከበኞች ፤ ያለው ፤ ትዝታ ፤ መልካም ፤ እንዲሆን ፤ ማድረግ ፤ አለብን ። የሆነ ፤ ሆኖ ፤ እራቁቱን ፤ አይሄድም ።»

«ለነገሩ ፤ ከልጁ ፤ ጋር ፤ እንዴት ፤ ለመነጋገር ፤ ትችላለህ ፤ ሉችኪን? እሱ ፤ የሚልህ ፤ ላንተ ፤ አይገባህም ፤ አንተ ፤ የምትለው ፤ ደግሞ ፤ ለርሱ ፤ አይገባውም!»

«አይ ፤ ግድየለም ፤ እንደምንም ፤ ብለን ፤ እንነጋገራለን ፤ » አለ ፤ ሉችኪን ፤ ባልተረጋገጠ ፤ እምነት ። ንግግሩንም ፤ በመቀጠል ፤ «ልጁ ፤ ጥቁር ፤ ቢሆንም ፤ ቅሉ ፤ ብልህ ፤ ነው ። የኛን ፤ ቋንቋ ፤ በፍጥነት ፤ አስተምረዋለሁ ። ከዚያ ፤ በኋላ ፤ እንግባባለን ፤» አለና ፤ በመርከቧ ፤ ዳር ፤ ተቀምጦ ፤ አካባቢውን ፤ የሚመለከተውን ፤ ልጅ ፤ በፍቅር ፤ ዓይን ፤ ተመለከተው ።

ልጁም ፡ ሉችኪን ፡ ወዳጁ ፡ መሆኑን ፡ ያላንዳች ፡ ቃል ፡ በማስተዋል ፡ ምስጋና ፡ የተመላበት ፡ ፈገግታ ፡ አሳየ ።

አምስት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ የጧት ፡ ሥራ ፡ ተፈጸመና ፡ ቮድካ ፡ (የመስኰብ ፡ አረቂ ፡) ታደለ ። ሁለት ፡ የሥራ ፡ ኃላፊዎችና ፡ ስምንት ፡ የበታች ፡ መኰንኖች ፡ በመድረክ ፡ ላይ ፡ በዙሪያ ፡ ተቀመጡ ። የማደያው ፡ የፊሽካ ፡ ምልክትም ፡ ተሰጠ ። (መርከበኞቹ ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ «የሌሊት ፡ ወፍ ፡ ዜማ ፡» ብለው ፡ ይጠሩት ፡ ነበር ።)

ሉችኪን ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ እየጠነቀለና ፡ በደስታ ፡ ፈገግ ፡ እያለ ፡ ተመልሶ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ማክሲምካ ፡ ተቀምጦ ፡ እንዲጠብቀው ፡ ነገረውና ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ የመጠጥ ፡ ቦታ ፡ ፈጥኖ ፡ ሄደ ። ልጁ ፡ ለጊዜው ፡ ግራ ፡ ገባው ።

ሆኖም ፡ ነገሩ ፡ ወዲያው ፡ ተገለጸለት ።

የመርከቧን ፡ መድረክ ፡ ያጠነው ፡ የሚሰነፍጥ ፡ የቮድካ ፡ ሽታና ፡ ከመጠጡ ፡ ቦታ ፡ ሪዛቸውን ፡ በሻከረና ፡ ቅጥራን ፡ በነካው ፡ እጃቸው ፡ እየጠረጉ ፡ የሚመለሱት ፡ መርከበኞች ፡ የደስታ ፡ ፊት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አስታወሰው ። ይሄውም ፡ «ቤትሲ ፡» በተባለችው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ መርከበኞቹ ፡ የሳምንት ፡ የአረቂ ፡ (የራም ፡) ቀለባቸውን ፡ እንዴት ፡ ይቀበሉ ፡ እንደነበርና ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥም ፡ በየዕለቱ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ እንዴት ፡ ይጠጣ ፡ እንደነበር ፡ ነው ።

ሉችኪን ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ብርጭቆ ፡ ቮድካውን ፡ ጨልጦ ፡ በደስታ ፡ እየፈነደቀ ፡ ወደ ፡ ማክሲምካ ፡ ተመለሰና ፡ ደስታውን ፡ ለማካፈል ፡ የልጁን ፡ ጀርባ ፡ ቸብ ፡ አድርጐ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«ቦን ፡ ቮድካ! ቬሪ ፡ ጉት ፡ ሽናፕስ ፡ ማክሲምካ!»

ማክሲምካም ፡ እራሱን ፡ እየነቀነቀ ፡ ሉችኪን ፡ የሚለውን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ደገመ ፤



«ቬሪ ፡ ጉት!»

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በፍጥነት ፡ በመግባባታቸው ፡ ሉችኪን ፡ ደስ ፡ ስላለው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ጐሽ ፡ ማክሲምካ ! ሁሉ ፡ ነገር ፡ ይገባሃል! በል ፡ አሁን ፡ እንሂድና ፡ ምሳችንን ፡ እንብላ ። አልራበህም?»

ልጁ ፡ እንዲገባው ፡ ሲል ፡ መንጋጋውን ፡ አነቃነቀ ።

ልጁም ፡ ወዲያው ፡ ሊገባው ፡ ቻለ ። ምክንያቱም ፡ መርከበኞቹ ፡ ከእንጨት ፡ የተሠራ ፡ ግዙፍ ፡ ቆሪአቸውን ፡ እየያዙ ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ መድረክ ፡ ሲሄዱና ፡ ሽታው ፡ የሚጣፍጥ ፡ የጐመን ፡ ሾርባ ፡ ሲቀበሉ ፡ አየ ።

ስለዚህ ፡ ልጁ ፡ እራሱን ፡ ገባኝ ፡ በማለት ፡ ነቀነቀ ፤ ዓይኖቹም ፡ በደስታ ፡ አበሩ ።

ሉችኪንም ፤ «ይገርማል! ልጁ ፡ ብልህ ፡ ነው! ሁሉ ፡ ነገር ፡ ይገባዋል!» አለ ። በልጁና ፡ ራሱም ፡ ከልጁ ፡ ጋር ፡ ለመግባባት ፡ በመቻሉ ፡ ጥቂት ፡ ኩራት ፡ ተሰማው ። የልጁንም ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ምሳ ፡ ወሰደው ።

የመርከቧ ፡ መድረክ ፡ በሸራ ፡ ተሸፍኗል ። መርከበኞቹም ፡ እግራቸውን ፡ እሸራው ፡ ሥር ፡ አድርገውና ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ እየሆኑ ፡ ዙሪያውን ፡ ተቀምጠው ፡ በፊታቸው ፡ የቀረበውን ፡ ኰምጣጣ ፡ የጐመን ፡ የአትክልት ፡ ሾርባ ፡ የክሮንሽታድት ፡ ተራ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ሁሉ ፡ ጾጥ ፡ ብለው ፡ ይበላሉ ። ደረቅ ፡ ዳቦ ፡ እየነከሩም ፡ ገመጥ ፡ ያደርጋሉ ።

ሉችኪን ፡ ከማክሲምካ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ በሚበሉት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ በጥንቃቄ ፡ እያለፈ ፡ ወደተመደበለት ፡ ቦታ ፡ ሄደ ። እዚያም ፡ እርሱን ፡ ሲጠብቁት ፡ የነበሩትን ፡ ጓደኞቹን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤

«ታዲያስ ፡ ጐበዝ ፡ ማክሲምካ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ እንዲቀላቀል ፡ እንፈቅድለታለን?»

«ምን ፡ ዓይነት ፡ ጥያቄ ፡ ነው! ቁጭ ፡ በሉ ፡ ሁለታችሁም ፡» አለ ፡ አሮጌው ፡ የመርከብ ፡ አናጢ ፡ ዛኻሪች ።

«ምናልባት ፡ ሌሎቹ ፡ ይቃወሙ ፡ ይሆናል ። ምን ፡ ይመስላችኋል ፡ ጕበዝ?» አለና ፡ ሉችኪን ፡ እንደገና ፡ ጠየቀ ።

ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ድምጽ ፡ ልጁ ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ እንዲቀላቀል ፡ ተቀበሉትና ፡ እንዲቀመጡ ፡ ወደጐን ፡ ቦታ ፡ አሰፉላቸው ።

የመስኰብ ፡ መርከበኞች ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ዘራቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑትንና ፡ ኃይማኖታቸው ፡ የተለያዩትን ፡ ሰዎች ፡ በደግነት ፡ ዓይን ፡ በመመልከት ፡ የታወቁ ፡ ስለሆኑ ፡ ይህ ፡ አስተያየታቸው ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

መርከበኞቹ ፡ ማክሲምካን ፡ በታላቅ ፡ አክብሮት ፡ ተቀበሉት ። አንዱ ፡ መርከበኛ ፡ ከእንጨት ፡ የተሠራ ፡ ማንኪያ ፡ ሰጠው፤ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ የራሱን ፡ ዳቦ ፡ አቀረበለት ። በጠቅላላው ፡ ትንሹን ፡ ልጅ ፡ በወዳጅነትና ፡ በፍቅር ፡ ዓይን ፡ ተመለከቱት ። ይህ ፡ ልጅ ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ቆዳቸው ፡ ነጭ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ደግነት ፡ አይቶ ፡ አያውቅም ።

«በሏ ፡ እንብላ! አለበለዚያ ፡ ሾርባችን ፡ ይቀዘቅዝብናል ፡» አለ ፡ ዛኻሪች ።

መርከበኞቹ ፡ አማተቡና ፡ ምሳቸውን ፡ መብላት ፡ ጀመሩ ።

«ለምን ፡ አትበላም ፡ ማክሲምካ?» አለ ፡ ሉችኪን ፡ ወደ ፡ ልጁ ፡ ማንኪያ ፡ እየጠነቀለ ። ቀጥሎም ፤ «የሚጣፍጥ ፡ ያትክልት ፡ ሾርባ ፡ ነው! ጉት ፡ ሾርባ ፡» አለ ።

ጥቁሩ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ «ቤትሲ ፡» በተባለችው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ከነጮች ፡ ጋር ፡ ቀርቦ ፡ እንዳይበላ ፡ ክልክል ፡ ስለነበርና ፡ የሚሰጠውንም ፡ ትርፍራፊ ፡ የሚበላው ፡ በጨለማ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ተደብቆ ፡ ስለነበር ፡ ለመብላት ፡ ፈራ ። ምግቡን ፡ ግን ፡ በረሃብ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተው ፤ ምራቁንም ፡ ዋጠ ።



«ምስኪኑ ፡ ልጅ ፡ ፈርቷል ። ያ ፡ ሰይጣን ፡ አሜሪካዊ ፡ የመርከብ ፡ አዛዥ ፡ ፍጹም ፡ ተጫውቶበታል ፡ » አለ ፡ አጠገቡ ፡ የተቀመጠው ፡ ዛኻሪች ።

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ዛኻሪች ፡ የልጁን ፡ ከርዳዳ ፡ ጸጉር ፡ ዳሰሰና ፡ የራሱን ፡ ማንኪያ ፡ ወደልጁ ፡ ከንፈር ፡ አስጠጋው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ማክሲምካ ፡ ፍርሃቱ ፡ ለቀቀው ። ከጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላም ፡ የአትክልት ፡ ሾርባና ፡ ሥጋ ፤ እንዲሁም ፡ የጤፍ ፡ ገንፎ ፡ ከቅቤ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ በላ ።

አልፎ ፡ አልፎም ፡ ሉችኪን ፤

«እንዲያ ፡ ነው ፡ ማክሲምካ ፤ ቬሪ ፡ ጉት ፡ ወንድሜ ፤ ብላ ፡ ለጤናህ!» እያለ ፡ ያበረታታው ፡ ነበር ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

የመርከቧ ፡ ደወል ፡ ተደወለ ። መርከበኞቹ ፡ ግን ፡ የምሳ ፡ በኋላ ፡ እንቅልፋቸውን ፡ እየለጠጡ ፡ ያኰርፉ ፡ ነበር ። ያልተኙት ፡ ተረኛ ፡ ጠባቂዎቹና ፡ ሌሎች ፡ አንዳንድ ፡ ንቁ ፡ መርከበኞች ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። እነዚህ ፡ መርከበኞች ፡ ትርፍ ፡ ሰዓታቸውን ፡ ጫማ ፤ አዲስ ፡ ሸሚዝና ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ነገር ፡ በመስፋት ፡ ይጠቀሙበታል ።

«ዛቢያካም ፡» በማያቋርጥ ፡ ነፋስ ፡ እየተገፋች ፡ መንገዷን ፡ በለዘብታ ፡ ቀጠለች ። ተረኛው ፡ ጠባቂ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ አልነበረውም ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝናብ ፡ የተሸከመ ፡ ደመና ፡ ሲቃረብ ፡ የዝናቡ ፡ ኃይለኛ ፡ ውሽንፍር ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያውን ፡ እንዳይቀደው ፡ በማውረድ ፡ ረገድ ፡ ይረዳል ። ምክንያቱም ፡ ዝናቡ ፡ በየትም ፡ ቦታ ፡ ስለሚወርድና ፡ ለመከላከልም ፡ ስለማይቻል ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ሰዓት ፡ ግን ፡ አድማሱ ፡ ቁልጭ ፡ ብሎ ፡ ጠርቶ ፡ ነበር ። በፍጥነት ፡ ተሰብስበው ፡ ወደትልቅ ፡ የዝናብ ፡ ደመና ፡ የሚለወጡትና ፡ ፀሐይዋንም ፡ አድማሱንም ፡ የሚሸፍኑት ፡ ጥቃቅንና ፡ ግራጫ ፡ ደመናዎች ፡ አይታዩም ። ከባድ ፡ ዝናብ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ ድንገተኛና ፡ ኃይለኛ ፡ ነፋስ ፡ መርከቧን ፡ ያላጋታል ፤ የዝናብ ፡ ማዕበልም ፡ የመርከቧን ፡ መድረክ ፡ እያጥለቀለቀ ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ ከግር ፡ እስከራሱ ፡ ያርሰዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኃይለኛው ፡ ዝናብ ፡ በፍጥነት ፡ እንደመጣ ፡ በፍጥነት ፡ ተመልሶ ፡ ይሄዳል ። በድንገት ፡ የመጣው ፡ ኃይለኛ ፡ ጉርምርምታና ፡ ዝናብ ፡ ሄዶ ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ጸጥ ፡ ይላል ።

እነሆ ፡ አሁን ፡ ፀሐይዋ ፡ ከላይ ፡ ከሰማይ ፡ ታብረቀርቃለች ። የመርከቧን ፡ መድረክና ፡ ገመዶች ፤ የነፋስ ፡ መወጠሪያውንና ፡ የመርከበኞቹን ፡ ሸሚዝም ፡ በፍጥነት ፡ ታደርቃለች ። ኩል ፡ የመሰለው ፡ ሰማይም ፡ ጸጥ ፡ ያለውን ፡ ባሕር ፡ ከላይ ፡ ወደታች ፡ ይመለከታል ። መርከቧም ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያዋን ፡ ዘርግታ ፡ እንደበፊቱ ፡ በማያቋርጥ ፡ ነፋስ ፡ እየተገፋች ፡ ጉዞዋን ፡ በርጋታ ፡ ትቀጥላለች ።

እነሆ ፡ አሁን ፡ በመርከቧ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ጸጥ ፡ ብሏል ። መርከበኞቹ ፡ «እረፍት ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡» ናቸው ። ለድንገተኛ ፡ ነገር ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፡ መርከበኞቹ ፡ ሙሉ ፡ እረፍት ፡ እንዲያደርጉ ፡ የተለመደ ፡ ደንብ ፡ ነው ።

ሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ሲተኙ ፡ ሉችኪን ፡ ግን ፡ በነፋስ ፡ መወጠሪያው ፡ ምሰሶ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። ተረኛው ፡ ጠባቂ ፡ በጣም ፡ ሳይደነቀው ፡ አልቀረም ፤ ምክንያቱም ፡ ሉችኪን ፡ «በንቅልፋምነት ፡» የታወቀ ፡ ስለነበር ፡ ነው ።



ሉችኪን ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ እያጉረመረመ ፡ የሸራ ፡ ጫማ ፡ ይሰፋል ፤ ከምሳ ፡ በኋላ ፡ የወሰደው ፡ የጫማ ፡ ልክ ፡ ትክክል ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ማክሲምካን ፡ ቁልቁል ፡ ይመለከታል ። (ማክሲምካ ፡ በመርከቧ ፡ መድረኩ ፡ ላይ ፡ አጠገቡ ፡ ተዘርግቶ ፡ ተኝቷል ። ጥቁር ፡ እግሮቹም ፡ ባዲሱ ፡ ነጭ ፡ ሱሪው ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ብለዋል ።)

ጫማው ፡ ልክ ፡ መሆኑን ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ የልጁን ፡ ትናንሽ ፡ ጥቁር ፡ እግሮች ፡ ሳይመለከት ፡ ሥራውን ፡ ቀጠለ ።

ይህ ፡ ሰካራም ፡ ሰው ፡ ለምስኪኑና ፡ ቤት ፡ ለሌለው ፡ ልጅ ፡ ጫማና ፡ ሌላም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚሰፋለት ፡ መሆኑን ፡ በማሰብ ፡ ጥልቅ ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ። ሳያውቀውም ፡ የራሱን ፡ በስካርና ፡ እንዲሁም ፡ የመንግሥት ፡ ልብስ ፡ በማጥፋት ፡ በግርፋት ፡ የተመላ ፡ የዘወትር ፡ ሕይወቱን ፡ ያስብ ፡ ጀመር ።

«ፍርሃትን ፡ ጨርሶ ፡ የማላውቅ ፡ ሰው ፡ ባልሆንና ፡ ድፍረቴና ፡ ጀግንነቴም ፡ የመርከብ ፡ አዛዦችን ፡ ባያስደስታቸው ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ ዱሮ ፡ ወደ ፡ አመጸኞች ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ገብቼ ፡ ነበር ፡» ሲል ፡ እራሱ ፡ ለራሱ ፡ ተናገረ ። ይህ ፡ አስተያየቱም ፡ እውነትን ፡ የተመረኰዘ ፡ ነበር ።

«እርግጥ ፡ ነው ፡ የተውኝ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡» አለና ፡ ጮኽ ፡ ተናገረ ፤ በረዥሙም ፡ ተነፈሰና ፤ «የሚቆረቁረኝ ፡ ይህ ፡ ነው ፡» አለ ። የሚቆረቁረኝ ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ በመርከቧ ፡ ላይ ፡ የታወቀ ፡ ሰካራም ፡ በመሆኑ ፡ እንደሆን ፡ (በወደብ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ በክሮንሽታድት ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ ቀረብ ፡ ካለው ፡ የመጠጥ ፡ ቤት ፡ አልፎ ፡ ሄዶ ፡ አያውቅም ፡) ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አመጸኞች ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ያልሄደበት ፡ ምክንያት ፡ ጠንካራ ፡ መርከበኛ ፡ በመሆኑ ፡ እንደሆን ፡ አልታወቀም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በሕይወቱ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የሚቆረቁር ፡ ነገር ፡ ዘፈኑን ፡ ለጥቂ

ት ፡ ደቂቃ ፡ እንዲያቋርጥና ፡ በሐሳብ ፡ ባሕር ፡ እንዲሰምጥ ፡ አደ
ረገው ። በመጨረሻም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ማክሲምካ ፡ የመርከበኛ ፡ ሽሚዝም ፡ ያስፈልገዋል ። ሽሚዝ ፡
የሌለው ፡ መርከበኛ ፡ ምን ፡ መርከበኛ ፡ ይባላል!»

ሉችኪን ፡ በዕረፍት ፡ ሰዓቱ ፡ የማክሲምካን ፡ ጫማ ፡ ለመስ
ፋት ፡ ሶልና ፡ ሽፋን ፡ ለክቶ ፡ ቀደደ ። ሶሉ ፡ አዲስ ፡ ቆዳ ፡ ከመሆኑ ፡
ሌላ ፡ የገዛውም ፡ ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ጧት ፡ በዱቤ ፡ ካንድ ፡ መርከበ
ኛ ፡ ጓደኛው ፡ ነበር ። ይህ ፡ ቆጣቢ ፡ መርከበኛ ፡ ጫማውን ፡ የሚያ
ደርገው ፡ እራሱ ፡ ሰፍቶ ፡ ነው ።

ሉችኪን ፡ ገንዘብ ፡ የመያዝ ፡ ነገር ፡ እንደማይሆንለት ፡ ስለ
ሚያውቅ ፡ (በተለይም ፡ እወደብ ፡ ላይ ፡) የዱቤው ፡ ገንዘብ ፡ ከደመ
ወዙ ፡ ላይ ፡ እየተቆረጠ ፡ እንዲከፈል ፡ አደረገ ።

የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ የቫሲሊይ ፡ የጐሮቪች ፡ (መርከበኞቹ ፡
«የጐሪች ፡ » ብለው ፡ ይጠሩት ፡ ነበር ፡) የፉጨት ፡ ድምጽ ፡ ሲሰ
ማ ፡ ሉችኪን ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ የተኛውን ፡ ልጅ ፡ ቀሰቀሰው ። ምንም ፡
እንኳ ፡ መንገደኛ ፡ ቢሆንም ፡ እንደቀሩት ፡ መርከበኞች ፡ ሁሉ ፡
ደንቡን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፤ አለበለዚያ ፡ ግን ፡ የጐሪች ፡ ችግ
ር ፡ ይፈጥር ፡ ይሆናል ፡ ሲል ፡ ሉችኪን ፡ አሰበ ። የጐሪች ፡ ጨዋ ፡
ሰው ፡ መሆኑንና ፡ ኃይሉንም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ካላገኘ ፡ በስተ
ቀር ፡ እንደማይጠቀምበት ፡ ያውቃል ። ሆኖም ፡ የጐሪች ፡ የተቆ
ጣ ፡ እንደሆነ ፡ ልጁን ፡ ሕግ ፡ እንደጣሰ ፡ ያህል ፡ ይቆጥረዋልና ፡
የመርከቧን ፡ ሕግ ፡ ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ ለጥቁሩ ፡ ልጅ ፡ «ማስተ
ማር ፡» የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ ታየው ።

«የመነሻ ፡ ሰዓት ፡ ደረሰ ፡ ተነሣ ፡ ማክሲምካ ፡» አለ ፡ ሉችኪ
ን ፡ በርኅራኄ ፡ ድምጽ ፡ የልጁን ፡ ትከሻ ፡ እየነቀነቀ ።

ማክሲምካ ፡ ዓይኑን ፡ ገለጠ ፤ ሌሎቹ ፡ መርከበኞች ፡ ነቅተ
ው ፡ ሥራቸውን ፡ ሲቀጥሉ ፡ ባየ ፡ ጊዜም ፡ ፈጥኖ ፡ ብድግ ፡ አለ



ና ፡ እንደደነገጠ ፡ ታማኝ ፡ ውሻ ፡ ሉችኪንን ፡ ይመለከተው ፡
ጀመር ።

«አይዞህ ፡ አትፍራ ፡ ማክሲምካ ። ምን ፡ ዓይነት ፡ ቂል ፡ ል
ጅ ፡ ነህ! ሁሉን ፡ ነገር ፡ ትፈራለህ! ተመልከት ፡ ይህ ፡ ላንተ ፡ ጫ
ማ ፡ የሚሆን ፡ ነው ።»

ወደ ፡ ልጁ ፡ እግርና ፡ ወደጫማው ፡ የላይ ፡ ሽፋን ፡ ሸራ ፡ እ
የጠነቆለ ፡ አሳየው ። ልጁ ፡ ሰውየው ፡ ስለምን ፡ እንደሚናገር ፡
አልገባውም ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ ነገሩ ፡ የደግ ፡ መሆኑን ፡ በስሜት ፡ ስ
ለተረዳው ፡ ፈገግ ፡ አለ ። ሉችኪንን ፡ አምኖ ፡ በመከተልም ፡ ወደ
መርከበኞቹ ፡ ሰፈር ፡ ሄደ ። ሉችኪን ፡ ገና ፡ ያላለቀውን ፡ ጫማ ፡
ከልብሱና ፡ ካልጋ ፡ አንሶላው ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ እሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ ሲ
ያስገባው ፡ በመደነቅ ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ። ኋላም ፡ ሉችኪን ፡ ቆ
ቡን ፡ አውልቆ ፡ መጀመሪያ ፡ ወደቆቡ ፡ ቀጥሎም ፡ ወደማክሲምካ ፡
እራስ ፡ እየጠነቆለ ፡ አንተም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነጭና ፡ ዙሪያውን ፡
ጥልፍ ፡ ያለው ፡ ቆብ ፡ ይኖርሃል ፡ ብሎ ፡ ለማስረዳት ፡ ሲጣጣር ፡
ልጁ ፡ ግን ፡ ስለምን ፡ እንደሚናገር ፡ ስላልገባው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ብ
ቻ ፡ በደስታ ፡ ፈገግ ፡ እያለ ፡ ሉችኪንን ፡ ይመለከተው ፡ ነበር ። ይል
ቁንም ፡ ደግሞ ፡ እነዚህ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ ነጮች ፡ በ«ቤ
ትሲ ፡» መርከብ ፡ ላይ ፡ ከነበሩት ፡ ነጮች ፡ ይልቅ ፡ ለርሱ ፡ ደግ ፡
በመሆናቸውና ፡ በተለይም ፡ ይህ ፡ ጸጉሩ ፡ የተንጨባረረና ፡ አፍ
ንጫው ፡ እንደበርበሬ ፡ የቀላ ፡ መርከበኛ ፡ አዲስ ፡ ልብስ ፡ ስለሰ
ጠውና ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ምግብም ፡ እያበላ ፡ በደግነትና ፡ በፍቅር ፡ ስለ
ያዘው ፡ የጥቁሩ ፡ ልጅ ፡ ልብ ፡ ተነካ ። በእንዲህ ፡ ያለ ፡ የርኅራኄና ፡
የደግነት ፡ ዓይን ፡ በሕጻንነቱ ፡ አንድ ፡ ጥቁር ፡ ሴት ፡ እንደተመለ
ከተችው ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ ትዝ ፡ ይለዋል ።

እነዚህን ፡ ደግ ፡ ዓይኖችም ፡ ከትላልቅ ፡ የዘምባባ ፡ ዛፎች
ና ፡ የሙዝ ፡ ቅጠል ፡ ከለበሱ ፡ ጐጆዎች ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ያስታው

ሳቸዋል ። ይህ ፡ ነገር ፡ በሕልሙ ፡ ያየው ፡ ይሁን ፡ ወይስ ፡ የልጅ
ነቱ ፡ ትዝታ ፡ ይሆን ፡ ሊያውቅ ፡ አልቻለም ። ነገር ፡ ግን ፡ በሕል
ሙ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየመጣ ፡ ያጽናናው ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡
እነዚህን ፡ ደግነትና ፡ ፍቅር ፡ የተመላባቸው ፡ ዓይኖች ፡ በሕልም ፡
ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በእውኑ ፡ ሊያያቸው ፡ ቻለ ።

የመርከብ ፡ ላይ ፡ ሕይወቱም ፡ እንደቀድሞው ፡ ፍርሃትና ፡ ስ
ቃይ ፡ የተመላበት ፡ ሳይሆን ፡ በሕልሙ ፡ እንደሚያየው ፡ ሁሉ ፡ አ
ስደሳች ፡ ሆነለት ።

ሉችኪን ፡ ስለቆቡ ፡ ነገር ፡ ለልጁ ፡ ማስረዳቱን ፡ ተስፋ ፡ ቆ
ርጦ ፡ የሸራ ፡ ከረጢቱን ፡ ዳበሰና ፡ አንድ ፡ አንኳር ፡ ስኳር ፡ አውጥ
ቶ ፡ ለማክሲምካ ፡ ሰጠው ፤ ልጁም ፡ በጣም ፡ ተደሰተ ። የመርከበኛው
ን ፡ ሻካራና ፡ የጐበረ ፡ እጅ ፡ በቀስታና ፡ በሃፍረት ፡ ጨበጥ ፡ አድር
ጎ ፡ የተዋረደና ፡ የተሰቃየ ፡ ሰው ፡ ድንገት ፡ በርኅራኄና ፡ በደግነት ፡
ሲያዝ ፡ በሚሰማው ፡ ስሜት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ በጥልቅ ፡ ምሥጋና ፡ ዓ
ይን ፡ ተመለከተው ። ይህ ፡ ምሥጋናም ፡ በፊቱና ፡ በዓይኖቹ ፡ ላ
ይ ፡ አበራ ፤ ከደስታው ፡ ብዛት ፡ የተነሣም ፡ ስኳሩን ፡ ወደ ፡ አፉ ፡
ከመክተቱ ፡ በፊት ፡ በቀጭን ፡ ድምጹ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ቃላት ፡ በአ
ገሩ ፡ ቋንቋ ፡ ተናገረ ።

«የሚያፍቅሩህ ፡ ትንሽ ፡ ለማኝ ፡ ነህ ፡ ለማለት ፡ ያስደፍረኛ
ል ። የደግነት ፡ ቃል ፡ አለመድክም ፤ ያሳዝናል ።» አለ ፡ ሉችኪን ፡
የጐረና ፡ ድምጹ ፡ የሚፈቅድለትን ፡ ያህል ፡ በርኅራኄ ፡ መልክ ፡
እየተናገረ ። ቀጥሎም ፡ የማክሲምካን ፡ ጉንጭ ፡ ቸብ ፡ ቸብ ፡ እያ
ደረገ ፡ «በል ፡ ስኳርህን ፡ ብላ ፤ ይጣፍጣል ፡ እኮ ።» አለው ።

እነሆ ፡ በዚህ ፡ አኳኋንና ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ያገ
ለገለው ፡ መርከበኛና ፡ የቲሙ ፡ ጥቁር ፡ ልጅ ፡ በጥብቅ ፡ የወዳጅነ
ት ፡ ሰንሰለት ፡ ተሣሰሩ ። ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡
በጣም ፡ የተደሰቱ ፡ ይመስላሉ ።



«ማክሲምካ ፤ የመስኰብኛ ፡ ቋንቋ ፡ አንተን ፡ ማስተማር ፡ አ
ለብን ፤ አለበለዚያ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የምታጉመተምተው ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ ሊ
ገባን ፡ አይችልም! በል ፡ አሁን ፡ የመድፍ ፡ ተኩስ ፡ ልምምድ ፡
እናደርጋለንና ፡ ወደመርከቧ ፡ መድረክ ፡ እንሂድ! አንተም ፡ መጥ
ተህ ፡ ልታይ ፡ ትችላለህ!»

ይህን ፡ ተባብለው ፡ ወደመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ሄዱ ፤ ወዲያው
ኑም ፡ ለመድፍ ፡ ተኩስ ፡ ልምምድ ፡ የክበሮ ፡ ምልክት ፡ ተሰጠ ።
ማክሲምካም ፡ መርከበኞቹ ፡ ወደየተመደበላቸው ፡ ሥፍራ ፡ ሲሮ
ጡ ፡ ገፍተው ፡ እንዳይጥሉት ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ምሰሶውን ፡
ተደግፎ ፡ ቆመ ። መጀመሪያ ፡ ፈርቶ ፡ ነበር ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ መርከ
በኞቹ ፡ በመድፉ ፡ አፈሙዝ ፡ ውኃ ፡ መጣጭ ፡ (ስፓንጅ ፡) እየከ
ተቱ ፡ ሲያወጡና ፡ በመድፉ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ እንጨት ፡ ቀጥ ፡
ብለው ፡ ሲቆሙ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ፍርኃቱ ፡ ለቀቀውና ፡ በመደነቅ ፡ ይ
መለከት ፡ ጀመር ። ይተኩሳሉ ፡ በማለትም ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ባካባቢው ፡ መርከብ ፡ ባለመኖሩ ፡ ወዴት ፡ እንደ
ሚተኩሱ ፡ ግራ ፡ ገባው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ «ቤትሲ ፡» የተባለችው ፡ መ
ርከብ ፡ ባሪያዎች ፡ ጭና ፡ ስትሄድ ፡ ሌላ ፡ መርከብ ፡ ደርሳባት ፡
ስታባርራትና ፡ «ቤትሲም ፡» ፈጥና ፡ ስትሸሽ ፡ ለሷ ፡ የተተኰ
ሰው ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ ለጥቂት ፡ ሲስታት ፡ አይቷል ። በ«ቤት
ሲ ፡» ላይ ፡ የነበሩት ፡ መርከበኞችም ፡ በፍርኃት ፡ ፊታቸው ፡ አ
መድ ፡ ሲለብስ ፤ የመርከቧ ፡ አዛዥም ፡ አባራሪዋ ፡ መርከብ ፡ ወ
ደኋላ ፡ እስትትቀር ፡ ድረስ ፡ ሲቆጣና ፡ ሲሳደብ ፡ አይቶ ፡ ነበር ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ የተኰሰችባቸው ፡ መርከብ ፡ ባሪያ ፡ የሚነግዱን ፡ መ
ርከቦች ፡ በተለይ ፡ ለመያዝ ፡ የተላከች ፡ የእንግሊዝ ፡ አባራሪ ፡ መ
ርከብ ፡ መሆንዋን ፡ ልጁ ፡ አያውቅም ፡ ነበርና ፡ «ቤትሲ ፡» ካባ

ራሪዋ ፡ የእንግሊዝ ፡ መርከብ ፡ ሸሽታ ፡ ስታመልጥ ፡ ልጁም ፡ እንደቀሩት ፡ መርከበኞች ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አለው ። መርከቧ ፡ ብትያዝ ፡ ኖሮ ፡ ግን ፡ ጨካኙ ፡ የመርከብ ፡ አዛዥ ፡ ስለፈጸመው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የባሪያ ፡ ንግድ ፡ ይሰቀል ፡ ነበር ።

በ«ዛቢያካ ፡» መርከብ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ማክሲምካ ፡ እንዳሰበው ፡ አንድም ፡ ጥይት ፡ ሳይተኰስ ፡ ቀረ። ሆኖም ፡ ከበሮው ፡ ሲመታና ፡ ያንደኛው ፡ መድፍ ፡ አዛዥ ፡ የሆነው ፡ ሉችኪንም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ጐንበስ ፡ እያለ ፡ መድፉን ፡ ሲያነጣጥር ፡ ልጁ ፡ ፈዞ ፡ ተመለከተ ።

የመድፍ ፡ ተኩስ ፡ ልምምዱ ፡ ማክሲምካን ፡ አስደሰተው ። ከልምምዱ ፡ በኋላ ፡ ሉችኪን ፡ ሻይ ፡ ስለሰጠውም ፡ እንደዚሁ ፡ ተደሰተ ። መጀመሪያ ፡ መርከበኞቹ ፡ ላባቸውን ፡ እያንጠፈጠፉና ፡ ስኳር ፡ ቀንጠብ ፡ እያደረጉ ፡ በስኒ ፡ ፉት ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ ሙቅ ፡ ውኃ ፡ መስሎት ፡ በመደነቅ ፡ ያይ ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ ሉችኪን ፡ አንድ ፡ ስኒ ፡ ሻይ ፡ ከአንድ ፡ አንኳር ፡ ስኳር ፡ ጋር ፡ ሲሰጠው ፡ የሚጥም ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። ሁለት ፡ ስኒ ፡ ሻይም ፡ እየጣፈጠው ፡ ጠጣ ።

ስለመጀመሪያ ፡ መስኰብኛ ፡ ቋንቋ ፡ ትምህርቱ ፡ ግን ፡ ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ የቀኑ ፡ ሙቀት ፡ በረድ ፡ ሲልና ፡ ለማሰብ ፡ ሲመች ፡ ሉችኪን ፡ ሊያስተምረው ፡ ሞከረ ። በእውነቱ ፡ ግን ፡ እምብዛም ፡ አልተሳካለትም ፡ ነበር ። የልጁ ፡ ስም ፡ ማክሲምካ ፡ መሆኑንና ፡ የመምህሩም ፡ ስም ፡ ሉችኪን ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ በከንቱ ፡ ያደረገው ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሌሎቹን ፡ መርከበኞች ፡ ጥቂትም ፡ አላስደነቃቸውም ፡ ነበር ።

ሉችኪን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ መምህር ፡ ባይሆንም ፡ ቅሉ ፡ በትዕግሥትና ፡ በርጋታ ፡ ልጁን ፡ መጀመሪያ ፡ የተጻውዖ ፡ ስሞች ፡ በማስጠናት ፡ የመስኰብኛ ፡ ቋንቋ ፡ ሊያስተምረው ፡ በተቻለው ፡ ሁሉ ፡ ይደክም ፡ ነበር ። በእውነቱ ፡ ችሎታ ፡ ያለውና ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ያልገጠመው ፡ ሌላ ፡ መምህር ፡ ቢያየው ፡ ኖሮ ፡ በቀናበት ፡ ነበር ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ ብልሃትና ፡ ዘዴ ፡ እየፈጠረ ፡ ያሰበውን ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ታጥቆ ፡ ተነሣ ።

መጀመሪያ ፡ ጣቱን ፡ ወደ ፡ ልጁ ፡ ደረት ፡ እየጠነቆለ ፡ «ማክሲምካ ፡» አለ ። ኋላም ፡ ወደራሱ ፡ እየጠነቆለ ፡ «ሉችኪን ፡» አለ ። ይህን ፡ ዘዴ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቢደጋግመውም ፡ ቅሉ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ ስላላሳየ ፡ ጥቂት ፡ እራቅ ፡ ብሎ ፡ ሄደና ፡ «ማክሲምካ!» ብሎ ፡ ተጣራ ። ማክሲምካ ፡ ፈገግ ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ምሥጢሩ ፡ ሊገባው ፡ አልቻለም ። ስለዚህ ፡ ሉችኪን ፡ ሌላ ፡ ዘዴ ፡ ፈጠረ ። ከመርከበኞቹ ፡ አንዱ ፡ «ማክሲምካ ፡» ብሎ ፡ እንዲጣራ ፡ አደረገና ፤ ሰውየው ፡ ሲጣራም ፡ ሉችኪን ፡ እራሱ ፡ በርግጠኛነት ፡ ወደ ፡ ልጁ ፡ በጣቱ ፡ ጠንቁሎ ፡ አሳየ ፤ እንዲገባውም ፡ የልጁን ፡ የሸሚዝ ፡ አንገት ፡ ይዞ ፡ በለዘብታ ፡ ነቀነቀው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይሆናል! ልጁ ፡ በደስታ ፡ ብቻ ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ ሳቀ ። ሸሚዙን ፡ ይዞ ፡ የነቀነቀውም ፡ ጨፍር ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሣና ፡ የሚያስደስት ፡ ጭፈራ ፡ ጀመረ ። የሚመለከቱት ፡ መርከበኞችና ፡ ሉችኪንም ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ጭፈራውን ፡ ሲጨርስ ፡ መርከበኞቹ ፡ እንደተደሰቱ ፡ ገባው ። ምክንያቱም ፡ አብዛኞቹ ፡ ጀርባውንና ፡ ትከሻውን ፡ እንዲሁም ፡ እራሱን ፡ ቸብ ፡ ቸብ ፡ እያደረጉና ፡ ከልብ ፡ እየሳቁ ፤ እንዲህ ፡ አሉት ፤

«ብራቮ ፡ ማክሲምካ! ጉት!»

ሉችኪን ፡ ልጁን ፡ ማስተማሩን ፡ ቢቀጥል ፡ ኖሮ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ውጤት ፡ ሊያስገኝ ፡ ይችል ፡ እንደነበር ፡ ለማወቅ ፡ አስቸጋሪ ፡

ነው ። ሆኖም ፡ ማስተማሩን ፡ ሊቀጥል ፡ ሲል ፡ እንግሊዝኛ ፡ የሚናገር ፡ አንድ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ መርከበኛ ፡ መጣና ፡ ነገሩን ፡ በብዙ ፡ በማቃለል ፡ የልጁ ፡ ስም ፡ «ቦይ ፡» ሳይሆን ፡ «ማክሲምካ ፡» መሆኑንና ፡ የወዳጁም ፡ ስም ፡ ሉችኪን ፡ መሆኑን ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ለልጁ ፡ ነገረው ። ቀጥሎም ፤

«አሁን ፡ ያወጣህለትን ፡ ስም ፡ ያውቃል ፡» አለው ፡ ለሉችኪን ።

«እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡» አለ ፡ ሉችኪን ፡ በደስታ ። «በተቻለኝ ፡ ሁሉ ፡ ሞክሬ ፡ ነበር ። ልጁ ፡ ብልህ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ላስረዳው ፡ አልቻልኩም ።»

«አሁን ፡ ይገባዋል ። እስቲ ፡ ጠይቀው ።»

«ማክሲምካ ፡» አለ ፡ ሉችኪን ።

ትንሹ ፡ ልጅ ፡ ወደራሱ ፡ ጠንቁሎ ፡ አሳየ ።

«አሁን ፡ ደህና ፡ ነው ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ! ሉችኪንስ ፡ ማነው?» አለና ፡ ጠየቀው ፡ ልጁን ።

ልጁም ፡ ወደራሱ ፡ ወደ ፡ ሉችኪን ፡ በጣቱ ፡ ጠነቆለ ።

ሁለቱም ፡ ከት ፡ ብለው ፡ ሳቁ ። ሌሎቹም ፡ መርከበኞች ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፤

«ይህ ፡ ልጅህ ፡ ቀለም ፡ ሊገባው ፡ ነው!»

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ትምህርቱ ፡ በቀላሉ ፡ ይካሄድ ፡ ጀመር ። ሉችኪን ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃዎች ፡ እየጠነቆለ ፡ ስማቸውን ፡ መጥራቱን ፡ ቀጠለ ። ቃላቱም ፡ ድምጻቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቃላት ፡ ሲመስል ፡ ልጁ ፡ በቀላሉ ፡ ያስታውሳቸዋል ፡ በማለት ፡ ንባባቸውን ፡ በተቻለው ፡ ሁሉ ፡ ያጣምመው ፡ ነበር ። የእራት ፡ ደወል ፡ እስኪሰማም ፡ ድረስ ፡ ማክሲምካ ፡ አንዳንድ ፡ ቃላት ፡ መምህሩን ፡ እየተከተለ ፡ ይደጋግም ፡ ነበር ።



«ጉሽ ፡ ሉችኪን! ደህና ፡ ይዘሃል! በዚህ ፡ አኳኋን ፡ እ«ኬፕ ፡» እስክንደርስ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ የመስኰብኛ ፡ ቃላት ፡ ሊያውቅ ፡ ይችላል ፡» አሉ ፡ ሌሎቹ ፡ መርከበኞች ።

«እርግጥ ፡ ነው! እ«ኬፕ ፡» እስክንደርስ ፡ ድረስ ፡ ሃያ ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ይፈጇልና ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡ ማክሲምካ ፡ ደግሞ ፡ ብልህ ፡ ልጅ ፡ ነው!» አለ ፡ ሉችኪን ።

«ማክሲምካ ፡» የሚለውን ፡ ቃል ፡ ሲሰማ ፡ ልጁ ፡ ወደ ፡ ሉችኪን ፡ ተመለከተ ።

«ይሄዋ ፤ ስሙን ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ያውቃል! ና ፡ ውድ ፡ ወዳጄ ፤ እራታችንን ፡ ሄደን ፡ እንብላ ።»

ከእራት ፡ በኋላም ፡ ጸሎት ፡ ተደረገና ፡ አልጋ ፡ መታደል ፡ ጀመረ ። ሉችኪን ፡ ልጁን ፡ በመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ አጠገቡ ፡ አስተኛው ። ማክሲምካም ፡ አመስግኖ ፡ በደስታ ፡ እመርከበኛ ፡ ፍራሹ ፡ ላይ ፡ ተጋደመ ። ለአንገቱ ፡ ትራስና ፡ የሚለብሰውም ፡ የብርድ ፡ ልብስ ፡ ነበረው ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያልጋ ፡ ዕቃ ፡ ሉችኪን ፡ ያገኘው ፡ ከወዳጁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

«ማክሲምካ! እንግዲህ ፡ ተኛ ፡ ነገ ፡ በጧት ፡ መነሣት ፡ አለብን!» አለው ፡ ሉችኪን ።

ማክሲምካ ፡ እያንጐላጀ ፡ «ማክሲምካ ፡» «ሉቺኪ ፡» ብሎ ፡ ከደጋገመ ፡ በኋላ ፡ እንቅልፍ ፡ ተጫነው ።

ሉችኪንም ፡ በተኛው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ካማተበ ፡ በኋላ ፡ ተኝቶ ፡ በኃይል ፡ ያኰርፍ ፡ ጀመር ።

እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ ከንቅልፉ ፡ ተነሣና ፡ ሌዎንቴቭ ፡ ከተባለው ፡ መርከበኛ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ መድረኩ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ የጥበቃ ፡ ሥራውን ፡ ጀመረ ።

ማንኛውም ፡ ነገር ፡ በሥርዓት ፡ መሆኑን ፡ ካዩ ፡ በኋላ ፡ እ

ግራቸውን ፡ አጣምረው ፡ ተቀመጡና ፡ እንቅልፍ ፡ እንዳይወስዳቸው ፡ መጨዋወት ፡ ጀመሩ ። ስለክሮንሽታድትና ፡ ስለዱር ፡ የመርከብ ፡ አዛዦቻቸው ፡ ካወሩ ፡ በኋላ ፡ ዝም ፡ አሉ ።

«ሰማህ ፡ ወይ ፡ ሌዎንቴቭ ፡» አለ ፡ ሉችኪን ፡ በድንገት ። «ቮድካ ፡ አዘወትረህ ፡ ጠጥተህ ፡ አታውቅም?»

ኰስታራና ፡ ትጉህ ፡ እንዲሁም ፡ መጠጥ ፡ የማይቀምሰው ፡ ሌዎንቴቭ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሉችኪንን ፡ በመርከበኛነቱ ፡ ቢያደንቀውም ፡ ቅሉ ፡ አረቂ ፡ በመውደዱ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ስለሚያየው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በቁርጠኛ ፡ ቃል ፡ መለሰለት ፤

«ከቶ ፡ አልጠጣም!»

«ጨርሶ ፡ ቀምሼ ፡ አላውቅም ፡ ማለትህ ፡ ነው?»

«አልፎ ፡ አልፎ ፡ በዓመት ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ ብርጭቆ ፡ እጠጣለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ አልፌ ፡ አላውቅም ።»

«የቮድካ ፡ ቀለብህን ፡ በገንዘብ ፡ የምትቀበለው ፡ ለዚህ ፡ ነዋ?»

«ገንዘብ ፡ ነው ፡ ጠቃሚ ፡ ወዳጄ ። ወደ ፡ ሩሲያ ፡ ተመልሰን ፡ ከሥራ ፡ ስንሰናበት ፡ ገንዘብ ፡ ሁልጊዜ ፡ ሊያገለግለን ፡ ይችላል ።»

«እርሱስ ፡ እርግጥ ፡ ነው ።»

«ስለቮድካ ፡ የምታወራው ፡ ለምንድነው ፡ ሉችኪን?»

«አንተ ፡ ዕድለኛ ፡ መሆንህን ፡ እያሰብኩ ፡ ነው ።»

ሉችኪን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ጸጥ ፡ አለና ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ስካርን ፡ ማዳን ፡ ይቻላል ፡ የሚባለው ፡ ዕውነት ፡ ነው?»

«እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ሰምቻለሁ ። በ«ኮብቺክ ፡» መርከብ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ዝቅተኛ ፡ መኰንን ፡ በምትሐት ፡ አንዱን ፡ ሰውየ ፡ ከስካር ፡ አድኖታል ። በ«ዛቢያካም፡» መርከብ ፡ ላይ ፡ ምትሐት ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ አለ ።»



«ማነው?»

«እናጢው ፡ ዛኻሪች ፡ ነው ። ግን ፡ ምስጢር ፡ አድርጎ ፡ ይይዘዋል ። ለማንኛውም ፡ ሰው ፡ አያደርግም ። አሁን ፡ አንተ ፡ መጠጥ ፡ እተዋለሁ ፡ ማለትህ ፡ ነው ?» አለና ፡ ሌዎንቴቭ ፡ በቀልድ ፡ አኳኋን ፡ ጠየቀው ።

«መተዌን ፡ እንኳ ፡ እንጃ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልብሴን ፡ ለመጠጥ ፡ መሸጤን ፡ ማቆም ፡ እፈልጋለሁ ።»

«ለምን ፡ በልክ ፡ ለመጠጣት ፡ አትሞክርም?»

«ሞክሬ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አልሆነልኝም ፡ ወንድሜ ። መጠጥ ፡ ሳይ ፡ ቅጡ ፡ ይጠፋኛል ። ዕድሌ ፡ ነው ፡ መሰለኝ!»

«እንዲያው ፡ አእምሮ ፡ ብታጣ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የድል ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም ፡» አለ ፡ ሌዎንቴቭ ፡ ኰስተር ፡ ብሎ ። «ወንድ ፡ ልጅ ፡ እራሱን ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዛኻሪችን ፡ አማክረው ። ምናልባት ፡ ሳይረዳህ ፡ አይቀርም ፤ ግን ፡ አንተ ፡ የምትድን ፡ ሰው ፡ አትመስለኝም ፡» አለ ፡ በመቀለድ ።

«እኔም ፡ አይመስለኝም ። ምንም ፡ ነገር ፡ ሊያድነኝ ፡ አይችልም ፡» አለ ፡ ሉችኪን ። ሊድን ፡ ባለመቻሉም ፡ ኩራት ፡ የተሰማው ፡ ይመስል ፡ ፈገግ ፡ አለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ሦስት ፡ ሳምንታት ፡ አለፉ ። «ዛቢያካ ፡» ወደ ፡ ኬፕታውን ፡ ከተማ ፡ ተጠጋች ፤ ግን ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ ለመግባት ፡ አልቻለችም ።

ብርቱ ፡ አውሎ ፡ ነፋስ ፡ ቢጢ ፡ ይነፍስ ፡ ስለነበር ፡ እንዳትገባ ፡ አገዳት ። ነፋሱና ፡ ማዕበሉ ፡ ኃይለኛ ፡ ስለነበር ፡ ለመግባት ፡ መሞከር ፡ ከንቱ ፡ ድካምና ፡ ከሰል ፡ መጨረስ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ የአየሩ ፡ ሁናቴ ፡ እስኪለወጥ ፡ ድረስ ፡ «ዛቢያካ ፡» የነፋስ ፡ መወጠሪያዋን ፡ ጠቅልላ ፡ ማዕበሉ ፡ እያወዛወዛት ፡ ከወደቡ ፡ እርቃ ፡ ቆመች ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ስድስት ፡ ወይም ፡ ሰባት ፡ ቀናት ፡ አለፉ ።

በመጨረሻ ፡ የነፋሱ ፡ ኃይል ፡ ተቀነሰና ፡ መርከቧ ፡ ጭሷን ፡ ቡልቅ ፡ ቡልቅ ፡ እያደረገች ፡ ወደ ፡ ኬፕታውን ፡ ወደብ ፡ አመራች ።

መርከበኞቹ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደተደሰቱ ፡ መግለጥ ፡ አያሻም ።

ሆኖም ፡ ከመርከበኞቹ ፡ አንደኛው ፡ ወደ ፡ ኬፕታውን ፡ በመድረሳቸው ፡ ካለመደሰቱም ፡ ሌላ ፡ መርከቧ ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ ስትጠጋ ፡ ሐዘንና ፡ ሐሳብ ፡ እየተጫነው ፡ ሄደ ።

ይሄውም ፡ መርከበኛ ፡ ሉችኪን ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ ከማክሲምካ ፡ ለመለየት ፡ ስላልፈቀደ ፡ ነበር ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ለመርከበኞቹ ፡ መጀመሪያ ፡ ባይመስላቸውም ፡ ቅሉ ፡ ሉችኪን ፡ ማክሲምካን ፡ በጥንቃቄ ፡ በያዘበት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለልጁ ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ እየጠነከረ ፡ ሄዶ ፡ ነበር ። ትንሹ ፡ ጥቁር ፡ ልጅም ፡ በበኩሉ ፡ ለሉችኪን ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ እንደዚሁ ፡ የጠነከረ ፡ ነበር ። ሉችኪን ፡ ጐበዝ ፡ መምህር ፡ በመሆኑና ፡ ልጁም ፡ ብልህ ፡ ተማሪ ፡ በመሆኑ ፡ ሁለቱም ፡ ይግባቡ ፡ ነበር ። ልጁ ፡ ጥቂት ፡ የመስኰብኛ ፡ ቃል ፡ በማወቁም ፡ መናገር ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ። ይበልጥ ፡ እየተዋወቁ ፡ ሲሄዱም ፡ ይበልጥ ፡ ወዳጆች ፡ መሆን ፡ ጀመሩ ። ማክሲምካ ፡ አሁን ፡ ሁለት ፡ሙሉ ፡ ልብስና ፡ ሁለት ፡ ሙሉ ፡ ጫማ ፡ አንድ ፡ ቆብና ፡ አንድ ፡ የመርከበኛ ፡ ሰንጢ ፡ አለው ። ብሩህና ፡ ደስተኛ ፡ ልጅ ፡ በመሆኑም ፡ መላው ፡ መርከበኞች ፡ ያፈቅሩት ፡ ነበር ። ማክሲምካ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ገመድ ፡ በመጐተቱና ፡ በተቻለው ፡ ሁሉ ፡ በመርዳቱ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ መንገደኛ ፡ የማይወደው ፡ የሥራ ፡ ኃላፊ ፡ የጐሪች ፡ እንኳ ፡ ልጁን ፡ ይወደው ፡ ነበር ።

ወደ ፡ መርከቧ ፡ ጫፍ ፡ ፈጥኖ ፡ እንደጠጣ ፡ ከመውጣቱም ፡ ሌላ ፡ ማዕበል ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ ጭራሽ ፡ አይፈራም ፡ ነበር ፤ እውነተኛ ፡ የልጅ ፡ መርከበኛ ፡ ነበር ።

ጠባየ ፡ መልካምና ፡ ገር ፡ ስለነበረም ፡ ያገሩን ፡ ጭፈራ ፡ በመጨፈርና ፡ ያገሩን ፡ ዜማ ፡ በጠራ ፡ ድምጹ ፡ በማዜም ፡ መርከበኞቹን ፡ ያስደስታቸው ፡ ነበር ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደደው ፤ የእጩ ፡ መኰንኑ ፡ አሽከር ፡ አርቱሽካም ፡ ብስኩትና ፡ ከገበታ ፡ የተረፈ ፡ ፍርፋሪ ፡ ዘወትር ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ።

ማክሲምካም ፡ በጣም ፡ ይወደው ፡ ስለነበር ፡ በሄደበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ እንደትንሽ ፡ ውሻ ፡ ይከተለው ፡ ነበር ። ሉችኪን ፡ ተረኛ ፡ ጠባቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አብሮት ፡ እዘበኛው ፡ ቦታ ፡ ሄዶ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፤ ያስተማረውን ፡ የመስኰብኛ ፡ ቃላትም ፡ ለማጥናት ፡ በተቻለው ፡ ሁሉ ፡ ይደክም ፡ ነበር ።

በኬፕታውን ፡ ወደብ ፡ አጠገብ ፡ ወደሚገኘው ፡ ጥርብ ፡ ገደል ፡ ተቃረቡ ። «ዛቢያካ ፡» ፈጥና ፡ መጓዟን ፡ ቀጠለች ፤ ወደ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ገደማም ፡ እወደቡ ፡ ጋ ፡ ደርሳ ፡ ትቆማለች ።

ቀኑ ፡ ብሩህና ፡ ፀሐያማ ፡ ጧት ፡ ነበር ። ሉችኪን ፡ ግን ፡ ደስ ፡ አላለውም ፡ ነበር ። መድፉን ፡ በትጋት ፡ ሲወለውል ፤ ማክሲምካም ፡ አጠገቡ ፡ ሆኖ ፡ ሲያስፈልግ ፡ ይረዳው ፡ ነበር ።

«እንግዲህ ፡ ልንለያይ ፡ ነው ፡ ማክሲምካ ። እኬፕታውን ፡ ያወርዱሃል ። ካሁን ፡ ወዲያ ፡ ምን ፡ ታደርግልናለህ?»

ልጁ ፡ ስለወደፊቱ ፡ ጊዜ ፡ አስቦ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ፤ ሉችኪን ፡ የተናገረውም ፡ አልገባውም ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ የሉችኪንን ፡ የሐዘን ፡ ፊት ፡ በመመልከት ፡ ሉችኪን ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ የሚያሳዝን ፡ መሆኑን ፡ ተረዳ ። ስሜቱንና ፡ ሐሳቡን ፡ በፍጥነት ፡ ገልጦ ፡ የሚያሳየው ፡ አስደሳች ፡ ፊቱም ፡ በድንገት ፡ ሐዘን ፡ ለበሰ ።

«አልገባኝም ፡ ሉቺኪ ፡» አለው ።

«እዚህ ፡ አውርደው ፡ ሊተውህ ፡ ነው ፡ ወዳጄ ። እኔ ፡ መንገዴን ፡ እቀጥላለሁ ፤ ማክሲምካ ፡ ግን ፡ እዚሁ ፡ ይቀራል ፡» አለው ፡ ሉችኪን ።

ልጁ ፡ እንዲገባውም ፡ በምልክት ፡ ሊገልጥለት ፡ ሞከረ ። ልጁም ፡ ነገሩ ፡ ገባውና ፡ የሉችኪንን ፡ እጅ ፡ የሙጥኝ ፡ ብሎ ፡ ይዞ ፡ በልመና ፡ ድምጽ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ወደ ፡ ወደብ ፡ አልሄድም፡ ... እዚሁ ፡ እቀራለሁ ፡ ... ማክሲምካ ፤ ሉቺካ ፤ ሉቺካ ፤ ማክሲምካ ፡ ... እኔ ፡ የሩሲያ ፡ መርከበኛ ፡ ነኝ ፡ ...አዎን ፤ አዎን ፡ ... »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሉችኪን ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ተገለጠለት ።

«የሩሲያ ፡ መርከበኛ ፡ መሆን ፡ ትፈልጋለህ ፡ ማክሲምካ?»

«አዎን ! አዎን !» አለ ፡ ማክሲምካ ፡ እራሱን ፡ ደጋግሞ ፡ በኃይል ፡ እየነቀነቀ ።

«ደህና ፡ ነው! ለምን ፡ ቀድሞ ፡ አላሰብኩበትም ፡ ነበር! ከሌሎቹ ፡ መርከበኞች ፡ ጋር ፡ ተነጋግሬ፡ ሐሳቡን ፡ ባለቃችን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ እናቀርባለን ።»

ከጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ሉችኪን ፡ ከመርከበኞቹ ፡ ጋር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይነጋገር ፡ ጀመር ፤



«ጐበዝ! ማክሲምካ ፡ ከኛ ፡ መለየት ፡ አይፈልግም! ከኛ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ እመርከብ ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ፈቃድ ፡ እንጠይቅለት ። ምን ፡ ይመስላችኋል?»

መርከበኞቹ ፡ በነገሩ ፡ የተስማሙ ፡ መሆናቸውን ፡ በደስታ ፡ ገለጹ ።

ስለዚህ ፡ ሉችኪን ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ሹም ፡ ሄደና ፡ የመርከበኞቹን ፡ ጥያቄ ፡ ለዋናው ፡ መኰንን ፡ ያቀርብላቸው ፡ ዘንድ ፡ ጠየቀው ። ቀጥሎም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«እባክህ ፡ የጐሪች ፡ ሆይ ፤ ዋናውን ፡ መኰንን ፡ ለምንልን ። ማክሲምካ ፡ ከኛ ፡ መለየት ፡ አይፈልግም ፡ ብለህ ፡ ንገረው ። እኬፕታውን ፡ አወርደን ፡ ብንተወው ፡ እምን ፡ ይገባል? ምን ፡ እንደሚደርስበትስ ፡ ማን ፡ ያውቃል? ኃጢአት ፡ ነው ፤ የጐሪች ። ልጁ ፡ ታማኝና ፡ ደግ ፡ ልጅ ፡ ነው ። አይደለም?»

«አዎን ፡ ነው ። ጥያቄውን ፡ አቀርባለሁ ። ማክሲምካ ፡ ንጹሕ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ብቻ ፡ ግን ፡ ዋናው ፡ አዛዥ ፡ በሩሲያ ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ጥቁር ፡ ሰው ፡ እንዲገኝ ፡ የሚፈቅድ ፡ አይመስለኝም ። ችግሩ ፡ ይሄ ፡ ነው ።»

«ይህ ፡ አያስቸግርም ፡ የጐሪች ። ክርስትያን ፡ እናደርገዋለን።»

«ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው?»

«እኛ ፡ ቤተክርስትያን ፡ እናጠምቀውና ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጥቁር ፡ ሩሲያዊ ፡ ይሆናል ። አየህ!»

ሐሳቡ ፡ የጐሪችን ፡ ስለሳበው ፡ ጥያቄአቸውን ፡ ለዋናው ፡ መኰንን ፡ በቶሎ ፡ ለማቅረብ ፡ ተስፋ ፡ ሰጠ ።

መኰንኑም ፡ ጥያቄውን ፡ ሰማና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ይህን ፡ ነገር ፡ ያሰበ ፡ ሉችኪን ፡ ይመስለኛል ።»

«ሉችኪን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ። የመላው ፡ መር

ከበኞች ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። እዚህ ፡ እወደብ ፡ ላይ ፡ አውርደን ፡ ብንተወው ፡ የት ፡ ይገባል? ሰዎቹ ፡ በጣም ፡ አዝነውለታል ። ቢያስፈልግ ፡ የክፍል ፡ ጠባቂ ፡ እናደርገዋለን ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ። ደህና ፡ የልጅ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው ። ካጠመቅነው ፡ ደግሞ ፡ ነፍሱን ፡ እናድናታለን ።»

ዋናው ፡ መኰንን ፡ ጉዳዩን ፡ ለበላይ ፡ አዛዡ ፡ ለማስታወቅ ፡ ተስፋ ፡ ሰጠ ።

የበላይ ፡ አዛዡ ፡ ጧት ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ለማውጣት ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ መድረክ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ መርከበኞቹ ፡ ያቀረቡትን ፡ ጥያቄ ፡ ነገረው ።

መጀመሪያ ፡ ጠቅላዩ ፡ አዛዥ ፡ ጥያቄውን ፡ በቀጥታ ፡ እምቢ ፡ ለማለት ፡ አስቦ ፡ ነበር ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ በነገሩ ፡ አሰበበትና ፡ (ምናልባት ፡ ስለራሱ ፡ ልጆች ፡ አስቦ ፡ ይሆናል ፡) አስተያየቱን ፡ ለውጦ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ደህና ፡ ነው ፤ ሊቆይ ፡ ይችላል ። የነጂ ፡ ክፍል ፡ ጠባቂ ፡ እናደርገዋለን ። ወደ ፡ ክሮንሽታድት ፡ ስንደርስም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እናደርግለታለን ። በእውነቱ ፡ እዚህ ፡ መቆየት ፡ ከፈለገ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እናወርደዋለን! ሉችኪንም ፡ የልጁ ፡ አስተማሪ ፡ መሆኑን ፡ ይቀጥል ፡ … ይደንቃል ፤ እንደሱ ፡ ያለ ፡ ሰካራም ፡ ሰው ፡ ልጁን ፡ በንደዚህ ፡ ያለ ፡ ፍቅር ፡ ሲይዘው! ሐኪሙ ፡ እንደነገረኝ ፡ ልብስ ፡ ሁሉ ፡ ሰፍቶለታል ።»

ማክሲምካ ፡ በመርከቧ ፡ ላይ ፡ እንዲቆይ ፡ መፈቀዱን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ መርከበኞቹ ፡ በደስታ ፡ ፈነደቁ ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ይበልጥ ፡ የተደሰቱት ፡ ማክሲምካና ፡ ሉችኪን ፡ እንደሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ሰባት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ መርከቧ ፡ በኬፕታውን ፡ ወደብ ፡ መልህቋን ፡ ጣለች ። በማግሥቱ ፡ ጧትም ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ተረኛ ፡



ጠባቂዎች ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጣቸውና ፡ ወርደው ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ ሄዱ ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ማክሲምካና ፡ ሉችኪን ፡ ነበሩ ።

«አደራ ፡ ማክሲምካን ፡ ለመጠጥ ፡ እንዳትሸጠው ፡» ሲል ፡ ከመርከብ ፡ ሲወርዱ ፡ የጐሪች ፡ እየሳቀ ፡ ተናገረ ።

ነገሩ ፡ ቆረቆረውና ፡ ሉችኪን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፤

«ምን ፡ ይታወቃል ፤ ምናልባት ፡ በማክሲምካ ፡ ምክንያት ፡ ሳልሰክር ፡ እመለስ ፡ ይሆናል ።»

ምንም ፡ እንኳ ፡ ጥንብዝ ፡ ብሎ ፡ ቢሰክርም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ እንደለበሰ ፡ ተመለሰ ። በዚህም ፡ መርከበኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ተደነቁ ። ማክሲምካ ፡ ወዳጁ ፡ ሉችኪን ፡ አለቅጥ ፡ ሲጠጣ ፡ ተመልክቶት ፡ ኖሮ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ እየሮጠ ፡ ሄዶ ፡ የመስኰብ ፡ መርከበኞች ፡ ስለጠራ ፡ ተሸክመው ፡ ወደመርከቧ ፡ ላይ ፡ አወጡት ፤ ማክሲምካም ፡ ካጠገቡ ፡ አልተለየም ፡ ነበር ።

ሉችኪን ፡ ተሸክመው ፡ ሲወስዱት ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ይለፈልፍ ፡ ነበር ፤


«ማክሲምካ ፡ የት ፡ ነው? ማክሲምካን ፡ አምጡልኝ ፡ … ለመጠጥ ፡ አልሸጥኩትም ፡ … የልብ ፡ ወዳጄ ፡ ነው ፡ … ማክሲምካ ፡ የት ፡ ነው?»

ማክሲምካን ፡ አጠገቡ ፡ ቆሞ ፡ ባየ ፡ ጊዜም ፡ ጸጥ ፡ አለና ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደው ።

ካንድ ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ «ዛቢያካ ፡» ከኬፕታውን ፡ ተነስታ ፡ ሄደች ። ማክሲምካም ፡ ወዲያው ፡ ክርስትና ፡ ተነስቶና ፡ ተጠምቆ ፡ የመጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ማክሲምካ ፤ ያባት ፡ ስሙ ፡ ዛቢያኪን ፡ (ከመርከቧ ፡ ስም ፡) ተባለ ።

ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የአስራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ጐልማሳ ፡ መርከበኛ ፡ ሆኖ ፡ በ«ዛቢያካ ፡» መርከብ ፡ ላይ ፡ እንደሆነ ፡ ወደ ፡ ክሮንሽታድት ፡ ደረሰ ። በእጩ ፡ መኰንን ፡ በፔቲያ ፡ ብርታትም ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ቻለ ።

ጠቅላዩ ፡ አዛዥም ፡ የሰጠውን ፡ ተስፋ ፡ በመፈጸም ፡ በክሮንሽታድት ፡ ያስተማማሚዎች ፡ ማሰልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቦታ ፡ አገኘለት ። ሉችኪን ፡ ከባሕር ፡ ኃይል ፡ ተሰናብቶ ፡ ለማክሲምካ ፡ ሲል ፡ በክሮንሽታድት ፡ ውስጥ ፡ ለመኖር ፡ ተቀመጠ ። ማክሲምካን ፡ ለማሳደግም ፡ ከልቡ ፡ ይደክም ፡ ጀመር ። በማክሲምካ ፡ ምክንያትም ፡ ለመጠጥ ፡ ልብሱን ፡ መሸጡን ፡ እርግፍ ፡ አርጎ ፡ ትቶ ፡ በልክ ፡ መጠጣትን ፡ ተማረ ።



ምዕራፍ ፡ ፩ ።

እ. ኤ . አ . በሺ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገደማ ፡ በተዋበ ፡ የሞቃት ፡ አገር ፡ ጧት ፡ የሩሲያ ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ በሲንጋፑር ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ መልሕቃቸውን ፡ ጥለው ፡ ሳለ ፡ ባሮን ፡ ፎን ፡ ደር ፡ ቤሪንግ ፡ የተባለው ፡ ዘለግ ፡ ቀጠን ፡ ያለና ፡ ጸጉረ ፡ ነጭ ፤ ዕድሜውም ፡ ወደ ፡ ሰላሳ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የሚሆን ፡ አዲስ ፡ የተሾመ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ ጐርዴየቭ ፡ ከተባለው ፡ ዋናው ፡ የሥራ ፡ ኃላፊ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ « ሞጉቺይ ፡» የተባለችውን ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ ፊቱን ፡ ኵስተር ፡ አድርጎ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ይፈ

ትሽ ፡ ነበር ። ሲፈትሽም ፡ አንድ ፡ ባንድና ፡ በጥንቃቄ ፡ ነበር ።
ባሮኑ ፡ አድሚራሉ ፡ (የባሕር ፡ ኃይል ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡) በሰጠ
ው ፡ ትዕዛዝ ፡ መሠረት ፡ «ጐሉብ ፡» ከተባለችው ፡ ፈጥኖ ፡ ደራሽ ፡
መርከብ ፡ ወደ ፡ «ሞጉቺይ ፡» የተዛወረው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡
ሲሆን ፡ እመርከቧ ፡ ላይ ፡ የወጣውም ፡ ባለፈው ፡ ማታ ፡ ነበር ፤
እነሆ ፡ አሁን ፡ ከአዲሷ ፡ መርከብ ፡ ጋር ፡ ለመተዋወቅ ፡ ጉብኝት ፡
ያደርጋል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ የጐደለ ፡ ነገር ፡
ለማግኘት ፡ ምንጊዜም ፡ የሚጥር ፡ ሰው ፡ ቢሆንም ፡ አንድም ፡
ዓይነት ፡ እንከን ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለም ። «ሞጉቺይ ፡» ባለፉት ፡
ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ወደውጭ ፡ ጉዞ ፡ ብታደርግም ፡
በጥንቃቄና ፡ በደንብ ፡ የተያዘች ፤ ከግር ፡ እስከራሷም ፡ በንጽ
ሕና ፡ የምታበራ ፡ መርከብ ፡ ነበረች ። አሁን ፡ የሌላ ፡ ፈ
ጥኖ ፡ ደራሽ ፡ መርከብ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ የሆነው ፡ የቀድሞው ፡
የ«ሞጉቺይ ፡» መርከብ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ ስቴፓን ፡ ስቴፓኖ
ቪች ፡ በመኰንኖችና ፡ በተራ ፡ መርከበኞች ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ከ
መሆኑም ፡ ሌላ ፡ «ሞጉቺይን ፡» እንደ ፡ አዲስ ፡ ቤሳ ፡ ንጹሕ ፡ አ
ድርጌ ፡ እይዛታለሁ ፡ እያለ ፡ በሙሉ ፡ ልቡ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ። ማን
ኛውም ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ የሚወድ ፡ መርከበኛም ፡ በ«ሞጉቺይ ፡»
ይቀናባት ፡ ነበር ።

በውነትም ፡ «ሞጉቺይ ፡» ባረፈችበት ፡ ወደብ ፡ ሁሉ ፡ ትደነ
ቅ ፡ ነበር ።

ባሮኑ ፡ በመርከበኞቹ ፡ መኖሪያ ፡ ሰፈር ፡ በቀስታና ፡ በመጐ
ተት ፡ ሲራመድ ፡ ቆይቶ ፡ ድንገት ፡ ቆም ፡ አለና ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡
በረጅምና ፡ በነጭ ፡ ሌባ ፡ ጣቱ ፡ እየጠነቆለ ፡ አሳየ ። በጣቱም ፡ ላ
ይ ፡ የባሮን ፡ ፎን ፡ ደር ፡ ቤሪንግ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የሚል ፡ ቅርጽ ፡ ያ
ለበት ፡ የሚያበራ ፡ ቀለበት ፡ አድርጐ ፡ ነበር ። በጣቱ ፡ እየጠነቆ
ለ ፡ ያሳየውም ፡ ነገር ፡ በተራ ፡ መርከበኞች ፡ መኖሪያ ፡ ሰፈር ፡
እጥላ ፡ ሥር ፡ የተኛ ፡ አንድ ፡ ትልቅና ፡ ቀይ ፡ ጸጉራማ ፡ ውሻ ፡ ነ
በር ። አስቀያሚ ፡ አፉም ፡ እወለሉ ፡ ላይ ፡ ተዘርሮ ፡ ነበር ።

«ምንድን ፡ ነው ፡ ያ ፡ ደግሞ?» ሲል ፡ ባሮኑ ፡ ከጥቂት ፡ ደቂ
ቃ ፡ ጸጥታ ፡ በኋላ ፡ በቆፍጣናነት ፡ ጠየቀ ።

«ውሻ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡» አለ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ በፍጥነት ፤
ምናልባት ፡ በጥላው ፡ ምክንያት ፡ ውሻ ፡ መሆኑን ፡ ሳያይ ፡ ቀርቶ ፡
ሌላ ፡ ነገር ፡ መስሎት ፡ ይሆናል ፡ በማለት ።

«ደደብ ፡» አለ ፡ ባሮኑ ፡ በለዘበና ፡ በቀዘቀዘ ፡ ድምጽ ። «ውሻ ፡ መ
ሆኑማ ፡ ይታየኛል ፤ ኋላ ፡ የመድረክ ፡ መጥረጊያ ፡ ነው? እኔ ፡ ለማ
ወቅ ፡ የምፈልገው ፡ እዚህ ፡ ምን ፡ እንደሚሠራ ፡ ነው? ውሻ ፡ በጦ
ር ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ሲኖር ፡ ታይቶና ፡ ተሰምቶ ፡ አይታወቅም!
የማን ፡ ውሻ ፡ ነው ፡ ለነገሩ?»

«የመርከቧ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ።»

«አንተ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ስምህ ፡ ማን ፡ ነው?»

«ጐርዴየቭ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ።»

«ጐርዴየቭ ፤ እስቲ ፡ ገልጸህ ፡ አስረዳኝ ፤ የምትለው ፡ አልገ
ባኝም ። የመርከቧ ፡ ውሻ ፡ ነው ፡ ማለትህ ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ?»
አለው ፡ ባሮኑ ። ይህንንም ፡ ሲል ፡ የሩሲያ ፡ ጀርመኖች ፡ እንደ
ሚያደርጉት ፡ ሁሉ ፡ በቀስታና ፡ በርጋታ ፡ እያንዳንዱን ፡ ቃል ፡ እ
ያጋነነ ፡ ይናገር ፡ ነበር ። በትላልቅና ፡ በንጹሕ ፡ የረጉ ፡ ሰማያዊ ፡
ዓይኖቹም ፡ የሥራ ፡ ኃላፊውን ፡ አተኩሮ ፡ ያየው ፡ ነበር ።

ሽምገል ፡ ያለው ፡ የሥራ ፡ ኃላፊ ፡ በማስረዳት ፡ ረገድ ፡ (ሙ
ቅት ፡ ብሎ ፡ ሰክሮ ፡ ከወደብ ፡ ካልተመለሰ ፡ በስተቀር ፡) ካሁን ፡
በፊት ፡ ችግር ፡ አግኝቶት ፡ አያውቅም ፡ ነበርና ፡ የባሮኑን ፡ ረጅ
ምና ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ፊት ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ። የ
ባሮኑ ፡ ፊት ፡ በሥጋ ፡ የዳበረ ፡ ነው ፤ ጢሙም ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ ነው ፤

ጕንጩም ፡ ነጭና ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ያደረገበት ፡ ነው ። ባሮኑ ፡ ላቀረበው ፡ አስቸጋሪ ፡ ጥያቄ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ መልስ ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ ትንንሽና ፡ ግራጫ ፡ ዓይኖቹን ፡ በመጨነቅ ፡ ያቁለጨልጭ ፡ ጀመር ።

«የመርከቧ ፡ ውሻ ፡ የማነው ፡ እኮ?»

«የመርከበኞቹ ፡ ነው ፡…የተራ ፡ መርከበኞቹ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡» አለ ፡ ኰስተር ፡ ባለ ፡ ፊትና ፡ በቁጣ ፡ ስሜት ። «ሳይገባህ ፡ ቀርቶ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ አንተ ፡ «ቀውላላ » ?» አለ ፡ በልቡ ።

ግን ፡ «ቀውላላው ፡» የገባው ፡ አይመስልም ፤ ምክንያቱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ከንቱ ። ጌታ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ። ማንኛውም ፡ ውሻ ፡ ጌታ ፡ አለው ።»

«ይህ ፡ ግን ፡ የለውም ፡ ጌታዬ ። የቲም ፡ ነው ።»

«ምንድን ፡ ነው ፡ አልክ?» ሲል ፡ ባሮኑ ፡ ጠየቀ ። ቃሉን ፡ አያውቀውም ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

«የቲም ፡ ውሻ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በክሮንሽታድት ፡ መርከቧን ፡ ስንጭን ፡ ሳለ ፡ ቆሪጥ ፡ ከመርከበኞቹ ፡ አንዱን ፡ ተከትሎ ፡ መጣ ፤ እነሆ ፡ እስከዛሬም ፡ ድረስ ፡ አለ ። ቆሪጥ ፡ ያልነውም ፡ በጅራቱ ፡ መቆረጥ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡» አለ ፡ ጨመር ፡ አድርጎ ፡ ለማብራራት ፡ ሲል ።

«በጦር ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ውሻ ፡ እንዲኖር ፡ አይፈቀድም ። መድረክ ፡ ያቆሽሻል ።»

«ጌታዬ ፡ ሆይ ፤ ቆሪጥ ፡ አስተዋይና ፡ ጨዋ ፡ ውሻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ አስቸግሮን ፡ አያውቅም!» አለ ፡ ቆሪጥን ፡ ለመደገፍ ፡ ሲል ። «የዱሮው ፡ ዋና ፡ መኰንናችን ፡ ስቴፓን ፡ ስቴፓኖቪች ፡ እንኳ ፡ ጥሩ ፡ ውሻ ፡ መሆኑን ፡ አይቶ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ እንዲቀመጥ ፡ ፈቀደልን ፤ መርከበኞቹም ፡ ይወዱታል ።»



«እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ነፃነት ፡ ለምዳችሁ ፡ ተበላሽታችኋል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ አጥብቄ ፡ ነው ፡ የምይዛችሁ ፤ ገባህ?» አለ ፡ ባሮኑ ፡ በቁጣ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ሲያስረዳ ፡ ስለተዝናናና ፡ እምብዛም ፡ አክብሮት ፡ ስላላሳየው ።

«አዎን ፡ ጌታዬ ፡» አለ ፡ መርከበኛው ።

ባሮኑ ፡ የውሻውን ፡ ዕድል ፡ ለመወሰን ፡ ግንባሩን ፡ ሰብሰብ ፡ አድርጎ ፡ ያስብ ፡ ጀመር ። የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ውሻውን ፡ ይወደው ፡ ስለነበር ፡ ውሳኔውን ፡ በናፍቆት ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ።

በመጨረሻ ፡ ባሮኑ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«መድረኩን ፡ ሲያቆሽሽ ፡ ባገኘው ፡ አውርጄ ፡ አስጥለዋለሁ ፤ ገባህ?»

«አዎን ፡ ጌታዬ ።»

«ይህን ፡ ደግሞ ፡ እንዳትዘነጋ ፤ ትዕዛዝ ፡ ደጋግሜ ፡ መስጠት ፡ አልወድም ፡» አለ ፡ ባሮኑ ፡ በሻካራ ፡ ድምጹና ፡ በተለመደው ፡ የመንቀባረርና ፡ የበላይነት ፡ ስሜት ።

የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ጐርዴየቭ ፡ ግን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አለቃዎች ፡ ሥር ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ስለሠራና ፡ የሰዎችን ፡ ጠባይ ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ስለሚያውቅ ፡ ገና ፡ ማስጠንቀቂያው ፡ ሳይነገረው ፡ ይህ ፡ «ቀውላላ ፡» ምንም ፡ እንኳ ፡ ባነጋገሩ ፡ የረጋና ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሰው ፡ እንደሆነና ፡ ከተወዳጁ ፡ ከስቴፓን ፡ ስቴፓኖቪችም ፡ እጅግ ፡ የተለየ ፡ ፍጡር ፡ መሆኑን ፡ አውቆ ፡ ነበር ።

ቆሪጥ ፡ ስሙ ፡ ተደጋግሞ ፡ ሲነሣ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ዓይኑን ፡ ከፈት ፡ አድርጎ ፡ ተንጠራራና ፡ በዝግታ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ከጥላው ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ብርሃኑ ፡ እራመድ ፡ አለ ። የመኰንን ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ እንግዳ ፡ ባየም ፡ ጊዜ ፡ የመርከብን ፡ ሥርዓት ፡ እንደሚጠብቅ ፡ አስተዋይ ፡ ውሻ ፡ ቆራጣ ፡ ጂራቱን ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በአክብሮት ፡ መልክ ፡ አወዛወዘ ።

«ኡሀ! ምን ፡ ዓይነት ፡ አስቀያሚ ፡ ፍጡር ፡ ነው!» አለ ፡ ባሮኑ ፡ ውሻውን ፡ በመጸየፍ ፡ መልክ ፡ እያየ ። ውሻው ፡ ትልቅና ፡ ዝርክክ ፤ ጸጉሩም ፡ ቀይና ፡ ከርዳዳ ፤ ጆሮው ፡ ሹጥጥ ፡ ያለ ፡ አፉም ፡ ትልቅና ፡ ሰፊ ፡ ከመሆኑ ፡ ሌላ ፡ ብል ፡ የበላው ፡ ይመስል ፡ ጠቃጠቆ ፡ ነበረበት ።

ከቆሪጥ ፡ አስቀያሚ ፡ መልክ ፡ ደስ ፡ የሚሉት ፡ ደግነትና ፡ ብልህነት ፡ የሚታይባቸው ፡ ዓይኖቹ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ምናልባት ፡ ባሮኑ ፡ እነዚህን ፡ አተኩረው ፡ የተመለከቱትን ፡ ዓይኖች ፡ አላየም ፡ ይሆናል ።

«ይህን ፡ አስቀያሚ ፡ ውሻ ፡ ከፊቴ ፡ አጥፉልኝ!» አለ ።

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ዘወር ፡ አለና ፡ ፊቱን ፡ ከኰሰተረውና ፡ ከከፋው ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ጋር ፡ ወደላይኛው ፡ መድረክ ፡ ወጣ ።

ቆሪጥ ፡ ቆራጣ ፡ ጅራቱን ፡ በግሮቹ ፡ መካከል ፡ ሻጥ ፡ አድርጎና ፡ (አንድ ፡ የክሮንሽታድት ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ለቀልድ ፡ ሲል ፡ የቆረጠው ፡) ዱሮ ፡ በተሰበረው ፡ ባንደኛው ፡ የፊት ፡ እግሩ ፡ ወደጐን ፡ እያነከሰ ፡ ቀጭኑ ፡ ባለ ፡ ቀይ ፡ ጢም ፡ መኰንን ፡ በሱ ፡ ባለመደሰቱና ፡ ስለገላመጠውም ፡ በድሉ ፡ እያዘነ ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ቦታው ፡ አመራ ።

ያዲሱን ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ ንግግር ፡ ሰምቶ ፡ የነበረ ፡ ተራ ፡ መርከበኛ ፡ መጥቶ ፡ የመርከቧን ፡ ውሻ ፡ በለዘብታ ፡ ቸብ ፡ ቸብ ፡ አደረገው ፤ ቆሪጥም ፡ የሰውዬውን ፡ ሻካራ ፡ እጅ ፡ በምስጋና ፡ ላስ ፡ ላስ ፡ አደረገ ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

አንድ ፡ ተራ ፡ ሩሲያዊ ፡ የበላዩ ፡ ሲጨቀጭቀውና ፡ ንግግር ፡ ሲያበዛበት ፡ አለቅጥ ፡ እንደሚሰለቸውና ፡ እንደሚቸከው ፡ ሁሉ ፡



ምስኪኑ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊም ፡ በባሮኑ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ መርከቧ ፡ ወደፊት ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ እንደምትካሄድና ፡ የሥራ ፡ ኃላፊዎችና ፡ የበታች ፡ መኰንኖችም ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፤ ሥርዓትስ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፤ በሰካራሞችስ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡ እንደሚጥልባቸው ፡ ባሮኑ ፡ በረጅሙና ፡ በሚሰለች ፡ ሐታታ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ሲሰጠው ፡ ትዕግሥቱ ፡ አልቆ ፡ ቆቡን ፡ እያፍተለተለ ፡ ይሰማው ፡ ነበር ።

በመጨረሻም ፤ «የነገርኩህን ፡ ሁሉ ፡ አስታውስ ፤ ለሌሎቹም ፡ ንገራቸው ፡» በሚል ፡ ቃል ፡ ሲለያይ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ እፎይ ፡ ተገላገልኩ ፡ ብሎ ፡ በደስታ ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ ። ፊቱም ፡ ገላውን ፡ እንደታጠበ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቀልቶ ፡ ነበር ፤ ወዲያውም ፡ ሲጋራ ፡ ለማጨስ ፡ ወደላይ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ ግንባር ፡ ሄደ ።

እዚያም ፡ እንደደረሰ ፡ ሌሎቹ ፡ አውራ ፡ መርከበኞች ፤ የሐኪሙ ፡ ረዳት ፤ አስተዳዳሪው ፤ ምክትል ፡ ሹሙ ፤ ሞተር ፡ ጠባቂው ፤ ሁለቱ ፡ ጸሐፊዎችና ፡ ሌሎችም ፡ የበታች ፡ መኰንኖች ፡ ከበቡት ።

«እህስ ፡ አኪም ፡ ዛኻሪች ፤ ዋናው ፡ መኰንን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው? ምን ፡ ይመስልሃል?» ሲሉ ፡ ሁሉም ፡ ጠየቁት ።

የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ግን ፡ መልስ ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ በቀዩ ፤ በጸጉራማውና ፡ በጅማታም ፡ እጁ ፡ ተስፋ ፡ የመቁረጥ ፡ ምልክት ፡ አሳይቶ ፡ በጥላቻ ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ገንዳው ፡ ውስጥ ፡ ምራቁን ፡ ተፋ ።

በጁ ፡ ያሳየው ፡ ምልክትና ፡ በኃይል ፡ አተፋፉም ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ፀሐይ ፡ አቃጥሎት ፡ ጡብ ፡ በመሰለው ፡ ፊቱ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ የመናደድ ፡ መልክ ፤ ሽበት ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ያደረገበት ፡ ጥቁር ፡ ጢሙና ፡ ድንች ፡ የመሰለው ፡ ቀይ ፡ አፍንጫው ፤ እንዲ

ሁም ፡ ኰስታራ ፡ ግንባሩ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ «የሱ ፡ ነገር ፡ ባይወራ ፡ ይሻላል ፡» የሚል ፡ ስሜት ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ።

«ቁጡ ፡ ነው?» አለና ፡ ጠየቀ ፡ አንደኛው ።

የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ መጀመሪያ ፡ ጥያቄውን ፡ ሳይመልስ ፡ ዝም ፡ አለ ። ኋላ ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ ሲጋራውን ፡ በኃይል ፡ ሳብ ፡ ሳብ ፡ አደረገና ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ምራቁን ፡ ተፋ ። ቀጥሎም ፡ እንደርሱ ፡ ያለ ፡ ብልህ ፡ ሰው ፡ የሚናገረውን ፡ ለመስማት ፡ አሰፍስፈው ፡ ይጠብቁት ፡ የነበሩትን ፡ አድማጮቹን ፡ ዙሪያውን ፡ ተመለከታቸውና ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተነፈሰ ፤ (ቀጠን ፡ ያለ ፡ ድምጹን ፡ ዝቅ ፡ ስለሚያደርግ ፡ የጭጋግ ፡ ጥሩምባ ፡ ብለው ፡ ይጠሩት ፡ ነው ።)

«ያለጥርጥር ፡ «ጩቅጫቃው ፡ ሰይጣን ፡» ነው!»

ይህን ፡ ቃል ፡ የተናገረውም ፡ በጥላቻና ፡ ከልቡ ፡ ስለነበር ፡ ሌሎቹንም ፡ ሊያሳምናቸው ፡ ቻለ ። ምክንያቱም ፡ በቂ ፡ ነበር ። ባለፉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ መርከበኞቹ ፡ እራሳቸው ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ብለው ፡ በሚጠሩት ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ ሥር ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ። የጥንቱ ፡ ዋና ፡ መኰንናቸው ፡ ለመርከበኞቹ ፡ ከመጠንቀቁም ፡ ሌላ ፡ በመርከብ ፡ ሥራና ፡ በሰልፍ ፡ ልምምድ ፡ አያደክማቸውም ፡ ነበር ። ደግሞም ፡ እምብዛም ፡ አይማታም ፡ ነበር ። (ቢማታም ፡ ለዱላ ፡ ብሎ ፡ ሳይሆን ፡ ሲናደድ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።) መርከበኞች ፡ ወደወደብ ፡ ሄደው ፡ ሲሰክሩም ፡ ችላ ፡ ይላቸው ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ በ«ሰይጣን ፡» ሥር ፡ ሆኖ ፡ የመሥራቱ ፡ ነገር ፡ አላስደሰታቸውም ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ የሁሉም ፡ ፊት ፡ በድንገት ፡ ኰሶ ፡ መሰለ ።

ለአንድ ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ ጸጥ ፡ እረጭ ፡ አሉ ።

«በምን ፡ ረገድ ፡ ነው ፡ «ሰይጣንነቱ ፡» ሲል ፡ ወጣቱና ፡ ጸጉረ ፡ ጥቅሉ ፡ የሐኪም ፡ ረዳት ፡ ጠየቀ ። ይህ ፡ ሰው ፡ ሥራው ፡



ከሌሎቹ ፡ የተለየ ፡ በመሆኑ ፡ ከዋናው ፡ መኰንን ፡ ጋር ፡ እምብዛም ፡ የሚያገናኘው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ነበር ። ከሐኪሙ ፡ ጋርና ፡ በሕመምተኞች ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እስከሠራ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይደርስበት ።

«በሁሉ ፡ ረገድ ፡ ነዋ ፡ ወዳጄ! ዋና ፡ ጩቅጫቃ ፡ ነው ፡… ያውልህ! በንግግር ፡ ብቻ ፡ የሰው ፡ እራስ ፡ ያዞራል ፤ ይሄ ፡ የጀርመን ፡ ተውሰክ! አሁን ፡ ቅድም ፡ እኔን ፡ እክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ወስዶ ፡ ሲጨቀጭቀኝ ፡ ባየህ! ያሣ ፡ መሳይ ፡ ዓይኖቹን ፡ እኔ ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ ሳያቋርጥ ፡ እኝ-ኝ-ኝ ፡ ይል ፡ ነበር ፡» አለ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ የባሮኑን ፡ ድምጽ ፡ እየቀዳ ። «እንግዲህ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ አጥብቄ ፡ ነው ፡ የምይዘው ። በኔ ፡ ሥር ፡ ይህች ፡ መርከብ ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ነው ፡ የምትስተዳደረው ። በወደብ ፡ ላይ ፡ የሚሰክሩንም ፡ አጥብቄ ፡ እቀጣለሁ ፡» እያለ ፡ ለፈለፈ ፡ … እስኪያቅለሸልሸኝ ፡ ድረስ ።»

«ትላንትና ፡ በ«ጐሉብ ፡» መርከብ ፡ ይዞት ፡ የመጣው ፡ የበታች ፡ መኰንንም ፡ ስለርሱ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ደህና ፡ ነገር ፡ አልተናገረም ። እርሱ ፡ እንዳለው ፡ ይህ ፡ ሰውዬ ፡ ችኰና ፡ ሰውን ፡ ጩቅጭቆ ፡ መድረሻ ፡ የሚያሳጣ ፡ ነው ፡» አንደኛው ፡ የበታች ፡ መኰንን ፡ ነገሩን ፡ በመቀጠልም ፤ የ«ጐሉብ ፡» መርከበኞች ፡ እርሱ ፡ ስለሄደላቸው ፡ ደስ ፡ ብሏቸዋል ። አስቸጋሪ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። ባይማታና ፡ ባይገርፍም ፡ ቅሉ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ይቀጣል ፡ አሉ ፤ ማለት ፡ በባዶ ፡ እግር ፡ እገመድ ፡ ላይ ፡ ያቆማል ፡ ወይም ፡ በሚቆረቁር ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ እንዲቀመጥ ፡ ያደርጋል ፤ ስህተት ፡ ፈልጐ ፡ ከማግኘትም ፡ አይቦዝንም ፡ ስለራሱም ፡ ከፍ ፡ አድርጐ ፡ ያስባል ፡ አሉ ። ስሙ ፡ ማን ፡ ነበር ?»

«ቤርኒኰቭ ፤ አይደለም?» አለ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ የጀርመኑን ፡ ስም ፡ ወደ ፡ መስኰብኛ ፡ ዘወር ፡ አድርጐ ። «ከጀርመን ፡

ባሮኖች ፡ አንዱ ፡ ነው ፡ … የሚኰራበት ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ አይገባኝም ። በውነቱ ፡ ምንም ፡ እኮ ፡ አይደለም ፡» አለ ፡ በሙሉ ፡ ልብ ።

«ይህን ፡ ያሰኘህ ፡ ምንድን ፡ ነው?»

«ምክንያቱም ፡ እምብዛም ፡ ብልህ ፡ ስላልሆነ ፡ ነዋ ። ባነጋገሩ ፡ እኮ ፡ ለማወቅ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ቶሎ ፡ አይገባውም ። ለምሳሌ ፡ አሁን ፡ ቅድም ፡ ቆሪጥ ፡ የመርከቧ ፡ ውሻ ፡ ነው ፡ ስለው ፡ ጭራሽ ፡ አልገባውም ፡ ነበር ። «ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው? ጌታ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ፡» አለኝ ።»

«ስለቆሪጥ ፡ በምን ፡ የተነሣ ፡ ተነጋገራችሁ?» አለና ፡ አንደኛው ፡ መርከበኛ ፡ ጠየቀው ።

«የቆሪጥን ፡ መልክ ፡ ባለመወደዱ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ይመስልሃል? ውሻ ፡ በጦር ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ የለበትም ፡ አለ ። መድረኩን ፡ ሲያበላሽ ፡ ቢገኝም ፡ አውረጄ ፡ አስጥለዋለሁ ፡ ብሎ ፡ አስጠንቅቋል ። ባይኔ ፡ እንዳላየውም ፡ ብሏል ።»

«ለምን ፡ እኮ ፤ ምን ፡ አጠፋና ፡ ነው ? ቆሪጥ ፡ እንደሆን ፡ አላስቸገረው ።»

«እሱን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ያስቸግረዋል ፤ ይዞት ፡ ይሂድና ። ዱዳ ፡ እንስሳ ፡ እንኳ ፡ አርፎ ፡ እንዲቀመጥ ፡ አይፈቅድም ። ጐበዝ ፤ እግዚአብሔር ፡ መዓት ፡ ነው ፡ ያወረደብን! እንግዲህ ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ አይሆንም ። ያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባርከው ፡ ስቴፓን ፡ ስቴፓኖቪችን ፡ ምንጊዜም ፡ የሚረሳ ፡ ሰው ፡ አይደለም!» አለና ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ የሲጋራ ፡ ማጤሻውን ፡ ወዝወዝ ፡ አድርጐ ፡ ወደኪሱ ፡ ከተተ ።

«የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ሳይቆጣጠረው ፡ የሚቀር ፡ አይመስለኝም ፡» አለ ፡ ወጣቱ ፡ የሐኪም ፡ ረዳት ። «ብዙ ፡ የበደል ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ አይፈቅድለትም ። እሱ ፡ እኮ! ዛሬ ፡ ዘመኑ ፡ ተለ



ውጧል ። ገባሮች ፡ እንኳ ፡ ነፃነት ፡ ተሰጥቷቸዋል ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ደግሞ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ መብት ፡ አለው ።»

«የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ በሁሉ ፡ ቦታ ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ። የኛ ፡ የቅርብ ፡ አዛዣችን ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ነው ፡» ሲል ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ መለሰላቸው ።

«ቢያስፈልግ ፡ ከኛ ፡ ውስጥ ፡ አንዳችን ፡ ለመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ አቤት ፡ እንላለን ፡» አለ ፡ የሐኪሙ ፡ ረዳት ፡ በድፍረት ፡ መልክ ።

«እንዴት ፡ ብልህ ! የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ለበታች ፡ መኰንን ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ብሎ ፡ የሱን ፡ ቢጤ ፡ መኰንን ፡ ያዋርደው ፡ ይመስልሃል? ጉዱ ፡ እኮ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ። የለም ፡ ወዳጄ ፡ ከኛ ፡ ውስጥ ፡ አንዳችን ፡ ብቻ ፡ አቤት ፡ ብንል ፡ አይጠቅምም ፡ ይሄማ ፡ አለቃዎችን ፡ ሁሉ ፡ ያስቆጣቸውና ፡ ጉድ ፡ ያፈሉብናል ። በዱሮ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ዘዴ ፡ ነበረን ፡» አለ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ የጥንት ፡ ልማድ ፡ አጥብቆ ፡ ተከታይ ፡ ስለነበር ።

«ምንድን ፡ ነበር ፡ አኪም ፡ ዛኻሪች?» አሉና ፡ ጠየቁት ።

«ችግር ፡ በገጠመን ፡ ጊዜና ፡ ችግሩንም ፡ የማንችለው ፡ ሆነን ፡ ተስፋ ፡ ስንቆርጥ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ አንድነት ፡ ሆነን ፡ በሥራ ፡ ኃላፊው ፡ በኩል ፡ አቤቱታችንን ፡ ለመርከብ ፡ አዛዥ ፡ እናቀርብ ፡ ነበር ።»

«ይረዳ ፡ ነበር ፡ ታዲያ?»

«ይሄ ፡ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ መርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ዓይነት ፡ ነበር ። አንዳንዶቹ ፡ አቤቱታውን ፡ በመመርመር ፡ ፊንታ ፡ ግማሾቹን ፡ መርከበኞች ፡ ይገርፏቸዋል ። ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ አቤቱታውን ፡ ተመልክተው ፡ ተገቢውን ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣሉ ። ለምሳሌ ፡ የባሕር ፡ ኃይል ፡ ባልደረባ ፡ በሆንኩበት ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ዛኖዞቭ ፡ ስለተባለ ፡ ጨካኝ ፡ አዛዥ ፡ ለአድሚራል ፡ (የባሕር ፡ ኃይል ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡) ቻፕሊጊን ፡ አቤቱታ ፡ አቅርበን ፡ ነበር ። ነገር ፡

ግን ፡ አድሚራሉ ፡ ጉዳዩን ፡ በመመርመር ፡ ፈንታ ፡ ሁላችንንም ፡
ቀጠቀጠን ። ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ስናቃስትና ፡ ስንጮህ ፡ ዋልን ። እኔ ፡
እራሴ ፡ መቶ ፡ ግርፋት ፡ ቀመስኩ ። አቤቱታችን ፡ ያስገኘው ፡ ይሄ
ው ፡ ነበር ። በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ አድሚራል ፡ ለሆነ ፡
ቹልኮቭ ፡ ለተባለ ፡ የመርከብ ፡ አዛዣችን ፡ በዋና ፡ መኰንናችን ፡
በኩል ፡ አቤቱታ ፡ አቅርበን ፡ ነገሩን ፡ ተመለከተልን ። ምንም ፡
እንኳ ፡ አቤቱታውን ፡ ሲሰማ ፡ ፊቱን ፡ ቢያኰሳትርም ፡ ጉዳዩን ፡
እንደሚመረምር ፡ ተስፋ ፡ ሰጠን ።»

«ታዲያስ ፡ መረመረው?»

«አዎን ፡ መረመረው ። ካንድ ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ዋና ፡
መኰንናችን ፡« በጤና ፡ ምክንያት ፡» ከመርከቧ ፡ ተሰናበተ ።
ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ እንደልባችን ፡ መተንፈስ ፡ ጀመርን ። ያን ፡ ጊዜ
ም ፡ አልተቀጣንም ፡ ነበር ። ይሄውላችሁ ፡ ጐበዝ ፡ እንዲህ ፡ ነ
በር ፡ የምናደርገው ። ይህን ፡ ስላችሁም ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡የ
ምናገኘው ፡ ከመቶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።»

«ቢሆንም ፡ የመርከቧ ፡ አዛዣችን ፡ መርከበኞቹ ፡ እንዲገ
ዱበት ፡ አይፈቅድም!» አለ ፡ አንደኛው ።

«እርግጥ ፡ ነው ፡ ያለን ፡ ተስፋ ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ብቻ ፡
ነው ። ሆኖም ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ በመርከቧ ፡ ላይ ፡ የሚሆነውን ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሊያውቅ ፡ አይችልምና ፡ ይህ ፡ ቀጭን ፡ ጀርመን ፡ ጩ
ቅጭቆ ፡ ሳይገድለን ፡ አይቀርም ።»

ያዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንናቸው ፡ ወሬ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡
ቀጠለ ። በመጨረሻ ፡ ታግሦ ፡ መጠበቅ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ወሰኑ ።
ምናልባት ፡ አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ የመርከቧን ፡ አዛዥ ፡ በመፍ
ራት ፡ ስቴፓን ፡ ስቴፓኖቪች ፡ ያወጣውን ፡ የተለመደ ፡ የመር
ከብ ፡ ደንብ ፡ አይለውጥ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ አሰቡ ። ይህም ፡
ሐሳብ ፡ አዕምሯቸውን ፡ አረጋው ። ቀጥሎም ፡ በትንሽ ፡ ጣቱ ፡ ላ



ይ ፡ የከበረ ፡ ድንጋይ ፡ ቀለበት ፡ ያደረገው ፡ ወጣትና ፡ ደፋር ፡ ጸ
ሐፊ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀ ፤

«የወደብ ፡ ላይ ፡ እረፍታችንስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ አኪም ፡
ዛኻሪች? ሲንጋፑርን ፡ እንድንጎበኝ ፡ ይፈቅድልናል?»

«ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አላነሣም ፡ » አለ ፡ ጐር
ዴየቭ ።

«ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ልታነጋግረው ፡ ይገባል ፡ አኪም ፡ ዛኻ
ሪች ።»

«ደህና ፡ ነው ፤ አነጋግረዋለሁ ።»

«እወደቡ ፡ ላይ ፡ ወርዶ ፡ ለመዝናናት ፡ የማይፈልግ ፡ የለም ።
ሲንጋፑር ፡ ቆንጆ ፡ ከተማ ፡ ናት ፡ ይላሉ ፤ ላይን ፡ የሚያስደስቱ ፡
ስፍራዎችና ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ የምግብ ፡ ቤቶችም ፡ አሏት ፡ ይባላል ።
ደህና ፡ ደህና ፡ ሱቆች ፡ ይገኙባታል ፡ ማለትንም ፡ ሰምቻለሁ ።
አደራ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እንድታነሣበት ፡ አኪም ፡ ዛኻሪች ። እዚህ ፡
ቦታ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ እንደምንቆይ ፡ እናውቀውምና ፡ ወደቧ
ን ፡ አናያት ፡ ይሆናል ።»

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የዋና ፡ መኰንናቸው ፡ ወጣት ፡ አሽከር ፡ አሹ
ርኰቭ ፡ ሲሮጥ ፡ መጣና ፡ የሥራ ፡ ኃላፊውን ፡ እንዲህ ፡
አለው ፤

«አኪም ፡ ዛኻሪች! ዋና ፡ መኰንናችን ፡ ይፈልጉሃል!»

«ምን ፡ ይፈልጋል ፡ ደግሞ ፡ አሁን?»

«እንጃ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ አውቃለሁ? እክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተቀም
ጦ ፡ ወረቀት ፡ ይመረምራል ።»

«እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ሊጨቀጭቀኝ ፡ ነው? ምን ፡ ይሄ ፡...»
ብሎ ፡ ክፉኛ ፡ እየተሳደበ ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ጋ ፡ሮጠ ።

«አንተ ፡ የአዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ አሽከር ፡ ሆነህ ፡ ልትቆ
ይ ፡ ነው ?» አሉና ፡ መርከበኞቹ ፡ አሹርኰቭን ፡ ጠየቁት ።

«ምን ፡ ይደረግ ፡ መቼስ ። ጥርሴን ፡ ገለጥ ፡ እያደረግኩ ፡ መቻል ፡ አለብኝ ። እግዜር ፡ በስቴፓን ፡ ስቴፓኖቪች ፡ ቦታ ፡ የላከልኝ ፡ መዓተኛ ፡ ሰው ፡ ነው ። ደንብ ፡ መጠበቅ ፡ አለብህ ፡ እያለ ፡ ሲያወርድብኝ ፡ ነበር ። ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደመኪና ፡ አስተካክየ ፡ መሥራት ፡ አለብኝ ። »

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ ቆሪጥን ፡ አለመውደዱና ፡ አውርጄ ፡ አስጥለዋለሁ ፡ እያለ ፡ ማስፈራራቱም ፡ በመርከበኞቹ ፡ ዘንድ ፡ የቁጭት ፡ ጉርምርምታ ፡ ፈጠረ ። መርከበኞቹ ፡ ውሻውን ፡ ይወዱታል ፤ የሚሰለችውን ፡ የባሕር ፡ ላይ ፡ ኑሮዋቸውንም ፡ ያቃልልላቸዋል ፤ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በክሮንሽታድት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በኖረበት ፡ ጊዜ ፡ ተሰቃይቶ ፡ ስለነበር ፡ አሁን ፡ መርከበኞቹ ፡ ለሚያደርጉለት ፡ ልግሥናና ፡ ደግነት ፡ ሁሉ ፡ ምሥጋናውን ፡ እነሱን ፡ በማፈቅር ፡ ይገልጻል ። ስለዚህ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ይህን ፡ እንስሳ ፡ ከመርከበኞቹ ፡ ለመነጠል ፡ ያለውን ፡ ፍላጐት ፡ እንደ ፡ ጭካኔ ፡ ቆጠሩት ።

ቆሪጥ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አስቀያሚ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ መርከበኞቹ ፡ የሚያስተምሩትን ፡ ሁሉ ፡ በፍጥነት ፡ የሚቀበል ፡ ብልህ ፡ ውሻ ፡ ስለነበር ፡ በሚሠራው ፡ አስገራሚ ፡ ነገርና ፡ በአስተዋይነቱ ፡ ሁሉንም ፡ ያስደንቃቸው ፡ ነበር ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨዋታውም ፡ እነዚህ ፡ ተራ ፡ መርከበኞች ፡ ከቤታቸው ፡ እርቀው ፡ በውቅያኖስ ፡ ላይ ፡ በሚጓዙበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያሳልፉትን ፡ አስቸጋሪ ፡ ሕይወት ፡ ላንድ ፡ አፍታም ፡ ቢሆን ፡ ያስረሳቸው ፡ ነበር ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብልህ ፡ ፊቱን ፡ ኰስተር ፡ አድርጐ ፡ በኋላ ፡ እግሩ ፡ ይራመዳል ፤ ዕቃ ፡ አምጣ ፡ ሲሉትም ፡ ተሸክሞ ፡ ያመጣል ።



እገመድ ፡ ላይ ፡ ወጥቶም ፡ «ውረድ!» እስኪሉት ፡ ድረስ ፡ እዚያው ፡ ላይ ፡ ይቆማል ። «ለመገረፍ ፡ ትፈልጋለህ ፡ ወይ ፡ ቆሪጥ?» ብለው ፡ ሲጠይቁትም ፡ ጥርሱን ፡ ያፋጭና ፡ በቁጣ ፡ ያጉረመርማል ። «ወደ ፡ መሬት ፡ መውረድ ፡ ትፈልጋለህ ፡ ወይ?» ሲሉትም ፡ ሳቅ ፡ እያለ ፡ ቆራጣ ፡ ጅራቱን ፡ ያወዛውዛል ። ፊሽካ ፡ ሲነፋና ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፤ «ሁላችሁም ፡ ወደላይኛው ፡ መድረክ ፡ ሂዱ ፡» ብሎ ፡ ሲጮኽ ፡ ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ መጥፎም ፡ ይሁን ፡ ደህና ፡ ከመርከበኞቹ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ወደላይኛው ፡ መድረክ ፡ ይሮጣል ። ተመልሰው ፡ ወደመኖሪያ ፡ ሰፈራቸው ፡ እንዲሄዱ ፡ ምልክት ፡ እስኪሰጥም ፡ ድረስ ፡ አብሯቸው ፡ ይቆማል ። ኃይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ተነሥቶ ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ሲገጥማቸውም ፡ እንደዚሁ ፡ አብሯቸው ፡ በመገኘት ፡ ያበረታታቸዋል ። ቮድካ ፡ (አረቂ ፡) ለማደል ፡ ፊሽካ ፡ በተነፋም ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሥነ ፡ ሥርአት ፡ ላይ ፡ አብሮ ፡ ይገኛል ። ከምሳ ፡ ሰዓትም ፡ በኋላ ፡ እግሩ ፡ እየሄደ ፡ የሚጥሉለትን ፡ ፍርፋሪ ፡ ሲቀበል ፡ በደስታ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ እየጮኸ ፡ ያመሰግናቸዋል ።

ከምሳ ፡ በኋላ ፡ መርከበኞቹ ፡ እረፍት ፡ ሲያደርጉ ፡ ቆሪጥ ፡ ኰችኔቭ ፡ ከተባለ ፡ መርከበኛ ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ ይተኛል ። ይህ ፡ ሰው ፡ ፊቱ ፡ ኰሶ ፡ የመሰለ ፡ ሽማግሌና ፡ ጥምብዝ ፡ ያለ ፡ ሰካራም ፡ መርከበኛ ፡ ነው ። ውሻው ፡ ግን ፡ ከልቡ ፡ ይወደዋል ። ቆሪጥ ፡ ዘወትር ፡ ከዚህ ፡ ሰውዬ ፡ አጠገብ ፡ አይጠፋም ፤ ኰችኔቭ ፡ በዳበሰው ፡ ወይም ፡ ቸብ ፡ ቸብ ፡ ባደረገው ፡ ቁጥር ፡ ውሻው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። ኰችኔቭ ፡ ሌሊት ፡ ተረኛ ፡ በሆነም ፡ ጊዜ ፡ አብሮት ፡ እየሄደ ፡ የወዳጁን ፡ ሥራ ፡ ይፈጽምለታል ። በመርከቧ ፡ ግንባር ፡ በኩል ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ዝናብ ፡ ሲያርሰውና ፡ ነፋስ ፡ ሲገርፈው ፡ የተቀነጣጠቡ ፡ ጆሮዎቹን ፡ ቀጥ ፡ አድርጐ ፡ አቁሞ ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ውቅያኖስ ፡ ነቅቶ ፡ ሲመለከት ፡ ኰችኔቭ ፡ ግን ፡ የዝናብ ፡ ልብሱን ፡ ተከናንቦና ፡ የውሻው ፡ ገላ ፡ እ

ያሞቀው ፡ ያንጐላጃል ። የሚያልፍ ፡ መርከብ ፡ ብርሃን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ መርከብ ፡ ሳያስጠነቅቅ ፡ ድንገት ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ ጥላውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በኃይል ፡ ይጮኽና ፡ የተኛውን ፡ ሰው ፡ ይቀሰቅሰዋል ። ወደመሬት ፡ ሲወርድም ፡ ቆሪጥ ፡ አብሮ ፡ ከኰችኔቭ ፡ ጋር ፡ ይሄዳል ። ቀረብ ፡ ወዳለው ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ ያደርሰውና ፡ ላንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ የሰፈሩን ፡ ውሾች ፡ ለመጐብኘት ፡ ይለየዋል ። አንዳንደየም ፡ ቆስሎ ፡ አንዳንደየም ፡ በደህና ፡ ወደ ፡ ወዳጁ ፡ ይመለሳል ። ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ግን ፡ አይለየውም ። መርከበኛው ፡ ጥምብዝ ፡ ብሎ ፡ ሰክሮ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ሲለፈልፍ ፡ ውሻው ፡ ቆራጣ ፡ ጅራቱን ፡ እያወዛወዘ ፡ ወይም ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ የወዳጅነት ፡ ድምጽ ፡ እያሰማ ፡ ያዳምጠዋል ። ኰችኔቭ ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ ሲመለስ ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ በተዘረረም ፡ ጊዜ ፡ ጓደኞቹ ፡ መጥተው ፡ እስኪያነሡት ፡ ድረስ ፡ ቆሪጥ ፡ ይጠብቀዋል ። ኰችኔቭ ፡ ውሻውን ፡ ቤት ፡ የሌለው ፡ ዞሮ ፡ አዳሪ ፡ ከመሆን ፡ አውጥቶና ፡ ከውሻ ፡ አጥማጆች ፡ ገመድ ፡ አድኖ ፤ ብዙ ፡ ምግብ ፡ ወደሚገኝበት ፡ መርከብና ፡ ለጋስና ፡ ቸር ፡ ከሆኑ ፡ መርከበኞች ፡ ጋር ፡ በመቀላቀል ፡ እመርከቧ ፡ ላይ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የማያውቀውን ፡ የደስታ ፡ ኑሮ ፡ ስለከፈተለት ፡ ቆሪጥ ፡ ዕውነተኛ ፡ ታማኝነቱን ፡ ገለጸ ።

ኰሶ ፡ ፊቱና ፡ ሰው ፡ የማይቀርበው ፡ ኰችኔቭም ፡ ውሻውን ፡ በብልህነቱ ፡ ወደደው ፡ (ግብረ ፡ ገብም ፡ ነበር ፡)። ኰችኔቭ ፡ በሰከረ ፡ ጊዜ ፡ አጥብቆ ፡ የሚያምነው ፡ ውሻውን ፡ ብቻ ፡ ይመስላል ። አንድ ፡ ተንኰለኛ ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ ወደመርከብ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ እንዳስገባውና ፤ ሚስቱም ፡ ዕውነተኛ ፡ «ሴት ፡ ወይዘሮ ፡» እንደነበረች ፤ ሴት ፡ ልጁም ፡ እንዴት ፡ እንደሸሸችው ፡ ለውሻው ፡ ገለጸለት ። ይህ ፡ ፊቱ ፡ የጨገገ ፡ መርከበኛ ፡ ባንድ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ጂን ፡ (አረቂ ፡) በላይ ፡ በላዩ ፡ እየገለበጠ ፡ የሚናገረው ፡ ታሪክ ፡ የሚያሳዝን ፡ መሆኑን ፡ ቆሪጥ ፡ የተረዳ ፡ መሰለ ።

ኰችኔቭ ፡ ከቆሪጥ ፡ ጋር ፡ የተገናኘው ፡ እንደ ፡ አጋጣሚ ፡ ነው ። «ሞጉቺይ ፡ » ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ረዥም ፡ ጉዞ ፡ ከማድረጓ ፡ ከሁለት ፡ ወይም ፡ ከሶስት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ዝናባምና ፡ ብርዳም ፡ በሆነ ፡ የእሁድ ፡ ቀን ፡ ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ተገናኙ ። ኰችኔቭ ፡ ካንድ ፡ የመጠጥ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሰክሮ ፡ እየተንገዳገደ ፡ በጓሮ ፡ በኩል ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ ሲሄድ ፡ አንድ ፡ የከፋው ፡ ውሻ ፡ ቧምቧ ፡ ተጠግቶ ፡ በብርድ ፡ ሲንቀጠቀጥ ፡ አየው ። የውሻው ፡ ብቸኝነትና ፡ ዝናም ፡ ያራሰው ፡ ጸጉሩ ፤ የጐድን ፡ አጥንቱ ፡ ዘልቆ ፡ መታየትና ፡ አለቅጥ ፡ መሻገቱ ፤ በጠቅላላው ፡ ውሻው ፡ ቤት ፡ የሌለው ፡ ዱርዬ ፡ መሆኑ ፡ የሰከረውን ፡ መርከበኛ ፡ ሕሊና ፡ ቀሰቀሰው ።

«የማነህ ፡ ወዳ-ጄ? ቤት ፡ የለህም ፡ እ?» አለና ፡ እውሻው ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ አጉመተመተ ።

ውሻውም ፡ በብልህ ፡ ዓይኖቹ ፡ ሰካራሙን ፡ ሰውዬ ፡ እየተመለከተ ፡ «ልሽሽ ፡ ወይስ ፡ ሰውዬው ፡ መንገዱን ፡ ይቀጥላል ፡» በማለት ፡ ያወጣ ፡ ያወርድ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰውዬው ፡ የደግነት ፡ ቃላት ፡ በወዳጅነት ፡ ድምጽ ፡ ሲናገር ፡ ውሻው ፡ ለበጐ ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዳ ፡ በሚያሳዝን ፡ ድምጽ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። መርከበኛውም ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ እራሱን ፡ በዳበሰው ፡ ጊዜ ፡ ውሻው ፡ በሰውዬው ፡ ደግነት ፡ ተነክቶ ፡ እጁን ፡ ላሰውና ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ በቀስታ ፡ ጮኸ ።

ኰችኔቭ ፡ ኪሱን ፡ መዳበስ ፡ ሲጀመር ፤ ውሻው ፡ በመጓጓት ፡ ተመለከተው ፤

«ሳይርብህ ፡ አልቀረም ፡ አንተ ፡ ምስኪን ፡ ውሻ!» አለ ፡ መርከበኛው ። «እሰቲ ፡ ቆይ ፡ ጐሽ ፡ ዕድለኛ ፡ ነህ ፤ ይሄውና ፡ አን

ድ ፡ ነገር ፡ ተገኘልህ ፡» አለና ፡ ከሱሪ ፡ ኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ሳንቲም ፡ ፈልጐ ፡ አወጣ ።

ወደ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ሱቅም ፡ ሄዶ ፡ ከስካሩ ፡ በተረፈው ፡ ሁለት ፡ ሳንቲም ፡ ዳቦና ፡ ቁርጥራጭ ፡ ጨጓራ ፡ ገዝቶ ፡ አሾምጦቶ ፡ ወዲያው ፡ ሰጠው ።

ውሻው ፡ ምግቡን ፡ ዘሎ ፡ ይዞ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ጉርሻ ፡ ዋጠና ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ መርከበኛው ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

«እንዲህ ፡ ከራበህስ ፡ ና ፡ እንሂድ ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ ጋ ። እዚያ ፡ መርከበኞቹ ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ ይሰጡሃል ። ደጎች ፡ ናቸው ። አትፍራቸው ። ካሰኘህም ፡ እዚያው ፡ ታድራለህ ። ለምን ፡ ተብሎ ፡ ዝናም ፡ ይመታሃል? ና ፡ እንሂድ ፡ ወዳጄ!»

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ሲያፏጭ ፡ ውሻው ፡ ተከትሎት ፡ ሄዶ ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ ላይ ፡ ወጣ ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደተሰበሰቡበት ፡ ቦታ ፡ በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ውሻው ፡ ጥቂት ፡ የፍርሃትና ፡ የሐፍረት ፡ ስሜት ፡ ተሰማው ፤

«አንድ ፡ ቤት ፡ የሌሽ ፡ ውሻ ፡ አምጥቻለሁ ፡ ጐበዝ!» አለ ፡ ኰችኔቭ ፡ ወደ ፡ ውሻው ፡ እየጠነቀለ ።

የውሻው ፡ አሰቃቂ ፡ መልክ ፡ መርከበኞቹን ፡ አሳዘናቸው ። እየደባበሱና ፡ እያሻሹም ፡ ምግብ ፡ ሊሰጡት ፡ ወደታች ፡ ይዘውት ፡ አወረዱ ። ወዲያው ፡ እስቲጠግብ ፡ ድረስ ፡ በላና ፡ በወጥቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ተኛ ። የገጠመውን ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ገና ፡ ስላላመነ ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ ከንቅልፉ ፡ ብንን ፡ ይል ፡ ነበር ።

በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ የላይኛው ፡ መድረክ ፡ ሲጠረግ ፡ ውሻው ፡ በፍርሃት ፡ ነቃ ። ነገር ፡ ግን ፡ ኰችኔቭ ፡ መርከበኞቹ ፡ ጧት ፡ ለቁርስ ፡ ከበሉት ፡ ሙቅ ፡ አንድ ፡ ቆሪ ፡ አቀረበለትና ፡ ያስጨነቀውን ፡ ፍርሃቱን ፡ አስወገደለት ።



ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ የጠረጋው ፡ ሥራ ፡ ሲያልቅ ፡ ውሻውን ፡ ወደ ፡ መድረኩ ፡ ይዞት ፡ ሄደና ፡ ከመርከበኞች ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ እንዲቀመጥ ፡ አሳሰበ ።

«ከኛ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ይጓዝ!» አለ ።

ሐሳቡን ፡ ሌሎቹም ፡ ተቀበሉት ። የሥራ ፡ ኃላፊውን ፡ ከዋናው ፡ መኰንናቸው ፡ እንዲያስፈቅድላቸው ፡ ጠይቀው ፡ ፈቃዱን ፡ ካገኙ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ስም ፡ ይውጣለት ፡ ተባባሉ ።

ሁሉም ፡ ዓይናቸውን ፡ ወደ ፡ አስቀያሚው ፡ እንስሳው ፡ ጥለው ፡ ሲመለከቱት ፡ ውሻውም ፡ በበኩሉ ፡ ስለወዳጅነታቸው ፡ ቆራጣ ፡ ጅራቱን ፡ እያወዛወዘና ፡ የሚዳብሱትን ፡ መርከበኞች ፡ እጅ ፡ እየላሰ ፡ ደስታውን ፡ ገለጸ ።

«እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጅራት ፡ ይዞ ፡ ቆሪጥ ፡ ከመባል ፡ በቀር ሌላ ፡ ምንም ፡ ስም ፡ አይገኝለትም ፡» አለ ፡ ከመርከበኞቹ ፡ አንዱ ።

ይህ ፡ ስም ፡ ሌሎቹንም ፡ አሰደሰታቸው ። ስለዚህ ፡ ከዚያን ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ቆሪጥ ፡ ተብሎ ፡ የ«ሞጉቺይ ፡» ባልደረባ ፡ ሆነ ።

የቆሪጥ ፡ የመጀመሪያ ፡ መምህሩ ፡ ኰችኔቭ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሰው ፡ በውነቱ ፡ አስደናቂ ፡ የማስተማር ፡ ስጦታ ፡ እንዳለው ፡ ተገለጸ ። ውሻው ፡ ከአንድ ፡ ሳምንት ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ፍንጣቂ ፡ የሌለበት ፡ ነጩ ፡ የመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ዘወትር ፡ በንጽሕና ፡ መያዝ ፡ እንዳለበት ፡ ተረድቶ ፡ ይህንኑ ፡ ንጽሕና ፡ በማክበር ፡ ረገድ ፡ ጨዋነቱን ፡ አሳየ ። በባልቲክ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ መጥፎ ፡ ያየር ፡ ሁናቴ ፡ በገጠማቸውም ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ የባሕር ፡ ላይ ፡ ጠባይ ፡ አሳየ ፤ ፍጹም ፡ ሳያጥወለውለው ፡ እንደወትሮው ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይበላ ፡ ነበር ። ኃይለኛው ፡ ማዕበል ፡ የመርከቧን ፡ ጐን ፡ ሲመታውም ፡ ጭራሽ ፡ አልፈራም ። ቆሪጥ ፡ ወዲያውኑ ፡ በመላው ፡ መርከበኞች ፡ ዘንድ ፡ ተወዳጅነትን ፡ አግኝቶ ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ ያጫውታቸው ፡ ጀመር ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ከመርከብ ፡
አውርዶ ፡ ሊጥለው ፡ ይፈልጋል ።

አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ በሰጠው ፡ የማስፈራሪያ ፡ ቃ
ል ፡ ከኰችኔቭ ፡ ይበልጥ ፡ የሥጋ ፡ ሰው ፡ የለም ። ያ ፡ «ቀጭን ፡
ሰይጣን ፡» ውሻውን ፡ እንዳያየውም ፡ በተቻለው ፡ ሁሉ ፡ ደከ
መ ። ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ቮድካ ፡ (አረቂ ፡) ለማደል ፡ ፊሽካ ፡ ሲነፋ ፡
ቆሪጥ ፡ እንደተለመደው ፡ እየፈነደቀ ፡ መጣ ። ነገር ፡ ግን ፡ ኰች
ኔቭ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ የጨለማ ፡ ቦታ ፡ ይዞት ፡ ሄደና ፤

«ቆሪጥ ፤ እዚህ ፡ ጸጥ ፡ ብለህ ፡ መቀመጥ ፡ አለብህ ፤ አለበለ
ዚያ ፡ ግን ፡ ጉድ ፡ ይፈላል ። ምሳህንም ፡ እዚሁ ፡ አመጣልሃለሁ ፡»
አለው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ካንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ መርከበኞቹ ፡ አዲሱን ፡ ዋና ፡ መኰን
ናቸውን ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ አወቁት ፤ ከፉኛ ፡ ጠሉትም ። እርግ
ጥ ፡ ነው ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ አልገረፈም ፡ ወይም ፡ አልመታም ፡
ነበር ፤ የመማታት ፡ ዝንባሌም ፡ አልነበረውም ። ሆኖም ፡ ለትን
ሹም ፡ ለትልቁም ፡ ነገር ፡ በጭቅጭቅ ፡ ልብ ፡ ስለሚያወልቅ ፡
ጠሉት ። ሰው ፡ ሲቀጣም ፡ በመጥፎ ፡ አኳኋን ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡
መርከበኞች ፡ እወደብ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ለመውረድ ፡ ያላቸውን ፡
ፈቃድ ፡ ይከለክላቸዋል ። በውነቱ ፡ ከረዥም ፡ የባሕር ፡ ላይ ፡ ጉ
ዞ ፡ በኋላ ፡ ላንድ ፡ መርከበኛ ፡ ያለችው ፡ ደስታ ፡ ይህቺው ፡ ብቻ ፡
ናት ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ መርከበኞች ፡ እምሰሶ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ወጥ
ተው ፡ እንዲቆዩ ፡ ወይም ፡ በሚቆረቁር ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጡ ፡
ያደርጋቸዋል ። ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ መርከበኞቹ ፡ በጣም ፡ ይበሳ
ጩ ፡ የነበረው ፡ የሚወዱትን ፡ የቮድካ ፡ (የአረቂ ፡) ድርሻቸውን ፡
ሲያስቀርባቸው ፡ ነበር ።



አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ በመጣሉ
ና ፡ እያንዳንዱ ፡ የመርከብ ፡ ላይ ፡ ደንብ ፡ ከሀ ፡ እስከፐ ፡ ካልተ
ፈጸመ ፡ ብሎ ፡ በመቸኩ ፡ መርከበኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ጠሉት ፤ ፈሩትም ።
ሕሊናና ፡ ነፍስ ፡ በሌለው ፡ መኪና ፡ የተደቆሱ ፡ መሰላቸው ። ከ
ዚህም ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ዋና ፡ መኰንናቸው ፡ ሁሉንም ፡ እ
ንደሚጠላቸውና ፡ ለጅ ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ የተፈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ አድ
ርጎ ፡ እንደሚቆጥራቸው ፡ ጠልቆ ፡ ተሰማቸው ። ካፉ ፡ አንድም ፡
የቀልድና ፡ የደግነት ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ አያውቁም ። ያው ፡ የተለ
መደው ፡ ንቀትና ፡ ጥላቻ ፡ የተከናነበው ፡ ኩስታራ ፡ ድምጹና ፡
በረጋው ፡ ሰማያዊ ፡ ዓይኑ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ የክፋት ፡ አስተያ
ዬት ፡ ነው ።

አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሙያውም ፡ የሚ
ከበር ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። በተራ ፡ መርከበኞች ፡ ሰፈር ፡ (የያንዳ
ንዱ ፡ መኰንን ፡ ጠባይ ፡ በሚተነተንበት ፡ ቦታ ፡) በተደረገው ፡ ው
ሳኔ ፡ መሠረት ፡ እንኳንስ ፡ እንደ ፡ «ንሥሩ ፡» እንደ ፡ ስቴፓን ፡ ስ
ቴፓኖቪች ፡ ሊሆንና ፡ መርከቧ ፡ ከሲንጋፑር ፡ ተነሥታ ፡ ስትጓ
ዝ ፡ ማዕበል ፡ በገጠማት ፡ ጊዜ ፡ ፍርሃትን ፡ ያሳየ ፡ ዶሮ ፡ ነው ፡ ተ
ባለ ። ጠና ፡ ያሉትም ፡ መርከበኞች ፡ ሲናገሩ ፡ ሰውዬው ፡ ምንም ፡
እንኳ ፡ እዚህም ፡ እዚያም ፡ ጥልቅ ፡ ቢልም ፡ የባሕር ፡ ላይ ፡ ሙያ
ው ፡ የሚያኰራው ፡ አይደለም ፡ አሉ ። በሾጣጣ ፡ ጭንቅላቱም ፡ ው
ስጥ ፡ እምብዛም ፡ አንጎል ፡ እንደሌለውና ፡ እንዲያው ፡ ችኰ ፡ መ
ንቻኰ ፡ መሆኑን ፡ ገለጹ ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ መርከበኞቹ ፡ አዲ
ሱን ፡ ዋና ፡ መኰንናቸውን ፡ ካብ ፡ አይገባ ፡ ድንጋይ ፡ ሆኖ ፡ አገ
ኙት ። ስለሱ ፡ ሲናገሩ ፡ «ጨቅጫቃው ፡ ሰይጣን ፡» ብለው ፡ ይጠ
ሩት ፡ ነበር ። እንዳይነተርካቸውም ፡ እንደ ፡ መቅሰፍት ፡ ይሸሹ
ት ፡ ነበር ።

አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ መጀመሪያ ፡ የመርከቧን ፡ ደንብ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ሞከረ ። ቀድሞ ፡ በየቀኑ ፡ የሚደረገው ፡ የወታደር ፡ ሰልፍ ፡ ልምምድ ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ ግን ፡ ሶስት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ እንዲሆን ፡ አደረገው ። መርከበኞቹ ፡ በየቀኑ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ የጥበቃ ፡ ሥራ ፡ ጊዜ ፡ ስለነበራቸው ፡ በተጨማሪው ፡ ሰዓት ፡ አዘኑ ። ነገር ፡ ግን ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ያዲሱን ፡ መኰንን ፡ ሥልጣን ፡ መቆጣጠር ፡ ጀመረ ።

እንዴት ፡ አድርጐ ፡ እንደተቆጣጠረውም ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ቀልጣፋ ፡ አሽከር ፡ የጐርካ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ለመርከበኞቹ ፡ ተረከላቸው ፤

«ጐበዝ ፤ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ «ጨቅጫቃውን ፡ ሰይጣን ፡» ጠራና ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ «ካርላ ፡ ፌርናንድች ፤ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ለውጥ ፡ ማድረግ ፡ የለብህም ፤ ሰዎቹንም ፡ በማያስፈልግ ፡ ልምምድ ፡ አታልፋቸው ። በነበረው ፡ ልማድ ፡ ይሠራ ።»

«ጨቅጫቃው ፡ ሰይጣንስ ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ መለሰ?»

«ፊቱ ፡ በርበሬ ፡ መሰለና ፡ «እሺ ፡ ጌታዬ ፡ እኔ ፡ ላገልግሎት ፡ ደህና ፡ ነገር ፡ የሠራሁ ፡ መስሎኝ ፡ ነው ፡» አለ ። የመርከቧ ፡ አዛዥም ፤ ይቅርታህንና ፡ ባሮን ፡ ያላንተ ፡ እርዳታ ፡ እኔው ፡ እራሴ ፡ ላገልግሎት ፡ ደህናው ፡ ነገር ፡ የቱ ፡ እንደሆን ፡ አውቃለሁ ። ለጥሩ ፡ አገልግሎት ፡ ከሆነ ፡ መርከበኞቹ ፡ መልፋት ፡ የለባቸውም ። የጥበቃ ፡ ሥራቸውና ፡ ሌላው ፡ ተግባር ፡ በቂ ፡ ነው ። ልጆቹ ፡ ጐበዝ ፡ ሠራተኞችና ፡ ደህና ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ አትስጋ ። ይሄው ፡ ነው ፡ የምነግርህ ፡» አለው ። «ጨቅጫቃው ፡ ሰይጣን ፡» ጆሮውን ፡ ሸምጥጠ ፡ ሄደ ፡» አላቸው ፡ የጐርካ ፡ የተደሰቱትን ፡ መርከበኞች ።



አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ ባሮን ፡ ፎን ፡ ደር ፡ ቤሪንግ ፡ ስለ ፡ መርከብ ፡ ደንብና ፡ ሥርአት ፡ ባለው ፡ አስተያየት ፡ ለ«ሞጉቺይ ፡» መርከብ ፡ የሚስማማ ፡ አልነበረም ። መኰንኖቹም ፡ ጠሉት ። በተለይም ፡ ደግሞ ፡ ወጣቶቹ ፡ መኰንኖች ፡ የዘመኑን ፡ የነፃ ፡ አስተያየት ፡ ሐሳብ ፡ የቀመሱ ፡ ስለነበሩ ፡ ከተራ ፡ መርከበኞች ፡ ጋር ፡ ያላቸው ፡ ግንኙነት ፡ ሰብአዊ ፡ እንዲሆን ፡ ይሞክሩ ፡ ነበር ። የአዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ አስተያየት ፡ ግን ፡ ዘመኑ ፡ ያለፈበት ፡ የመኳንንትና ፡ የዱሮ ፡ ሰው ፡ አስተያየት ፡ ነበር ። «የተቀደሱ ፡ መሠረታዊ ፡ ዕምነቶች ፡» የሚላቸውን ፡ ነገሮች ፡ ከልቡ ፡ በማመን ፡ ሲኰራና ፡ ሲምበጣረር ፤ በሰዓቱም ፡ ዘወትር ፡ ሲገኝ ፡ መኰንኖቹን ፡ አበሳጫቸው ። በመኳንንት ፡ ንቀትም ፡ ሌሎቹን ፡ ዝቅ ፡ አድርጐ ፡ ስለተመለከታቸውና ፡ እራሱንም ፡ እንደማይሳሳት ፡ ሰው ፡ አድርጐ ፡ ስለቆጠረ ፡ ወጣቶቹ ፡ ደስተኞች ፡ መኰንኖቹ ፡ እንደ ፡ ደደብና ፡ እንደ ፡ ደንቆሮ ፡ ሰው ፡ ቆጠሩት ። መንገድ ፡ መሪው ፡ መኰንንና ፡ ዋናው ፡ መድፈኛ ፡ እንዲሁም ፡ መሐንዲሱ ፡ አዲሱን ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ አልወደዱትም ፡ ነበር ። ዘወትር ፡ ተጠራጣሪና ፡ በቀላሉ ፡ የሚቀየሙ ፡ ሰዎች ፡ በመሆናቸው ፡ በአዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ ረቂቅ ፡ የትህትና ፡ ጠባይ ፡ ውስጥ ፡ የንቀትና ፡ የበላይነት ፡ ስሜት ፡ እንዳለበት ፡ ተገንዝበው ፡ ነበር ። የመርከቧ ፡ አዛዥም ፡ ቢሆን ፡ አዲሱን ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ አልወደደውም ፡ ነበር ። አድሚራሉ ፡ ይህን ፡ «የጀርመን ፡ ቋሊማ ፡» ስለላከለት ፡ እምብዛም ፡ ሊያመሰግነው ፡ አልቻለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ጮሌው ፡ አድሚራል ፡ ይህን ፡ ሰውዬ ፡ ወደ ፡ «ሞጉቺይ ፡» የላከው ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ እንደሚያስወግደው ፡ እያወቀና ፡ ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ከደሙ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ የተጠላውን ፡ መኰንን ፡ ወደሩሲያ ፡ መልሶ ፡ ለመላክ ፡ ሲል ፡ ነበር ። የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ምስጢር ፡ አያውቅም ፡ ነበር ።

መኰንኖቹ ፡ ለጉዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ አዲሱን ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ አያቀርቡትም ፡ ነበር ። ከ«ሞጉቺይ ፡» መኰንኖች ፡ የወንድማማችነት ፡ ማኅበር ፡ ውስጥም ፡ አርቀውት ፡ ነበር ። እጩ ፡ መኰንኖቹ ፡ ስለገባር ፡ መጥፎነትና ፡ ሥልጣኔ ፡ ስለማይገባቸው ፡ ስለዱሮ ፡ መኳንንት ፡ ዋና ፡ መኰንናቸው ፡ እንዲሰማቸው ፡ ጮኸው ፡ በመናገርና ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፤ «በስቴፓን ፡ ስቴፓኖቪች ፡ ሥር ፡ መሥራት ፡ እንዴት ፡ ጥሩ ፡ ነበር! እሱ ፡ ችሎታና ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡ መኰንንና ፡ እንከን ፡ የሌለበት ፡ ወዳጅ ፡ ነበር! ሰዎቹስ ፡ እንዴት ፡ ይወዱት ፡ ነበር! እርሱስ ፡ እንዴት ፡ ያዝንላቸው ፡ ነበር! ለርሱስ ፡ እንዴት ፡ ጠንክረው ፡ ይሠሩ ፡ ነበር!» እያሉ ፡ ያፌዙበት ፡ ነበር ።

«ቆሪጥ ፡ እንኳ ፡ ይወደው ፡ ነበር!» አለ ፡ ኰሹቲች ። ይህ ፡ ወጣት ፡ በደደቡ ፡ ጀርመን ፡ ማፌዝ ፡ የሚወድ ፡ ጸጉረ ፡ ጥቅል ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ ነው ።«ቆሪጥን ፡ ዛሬ ፡ ምነው ፡ አላየነውም? ሳይሸሽግ ፡ አይቀርም ፤ ምስኪን ፡ ውሻ! ለምን ፡ ይሆን?» አለ ፡ ጨመር ፡ አደረገና ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ውሻውን ፡ እጥለዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ማስፈራራቱን ፡ ሲያውቅ ።

ባሮኑ ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፡ ከመነፋት ፡ በስተቀር ፡ የመኰንኖቹን ፡ የማሽሚጠጥ ፡ ቃል ፡ ከቁም ፡ ነገርም ፡ አልቆጠረው ። መጠላቱንም ፡ ያላወቀ ፡ በመምሰል ፡ ሥራውን ፡ በተለመደው ፡ የትዕቢትና ፡ የደደብነት ፡ መንፈስ ፡ ቀጠለ ።

በዚያን ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ ቆሪጥን ፡ ፈጽሞ ፡ አላየውም ፡ ነበር ። ውሻው ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሩቅ ፡ አየው ፤ ወዲያው ፡ ኰችኔቭም ፡ «ተጠንቀቅ ፡ ያን ፡ ሰውዬ!» ብሎ ፡ ስላስፈራራው ፡ ውሻው ፡ ወዲያው ፡ ተንበረከከ ። ከዚያን ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ ቆሪጥ ፡ እንደልቡ ፡ መፈንጨቱ ፡ ቀረ ። ጧት ፡ ጧት ፡ አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ የተለመደውን ፡ ጉብኝቱን ፡ ሲያደርግ ፡ ውሻው ፡



ወደታችኛው ፡ መድረክ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ከሰል ፡ ቤት ፡ ሄዶ ፡ ጨለማ ፡ ቦታ ፡ ፈልጎ ፡ መደበቅ ፡ ነበረበት ። ኰችኔቭም ፡ ውሻው ፡ ድምጽ ፡ ሳያሰማ ፡ እንዴት ፡ ለመደበቅ ፡ እንደሚችል ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ አስተማረው ። በኰችኔቭ ፡ ብርታት ፡ ውሻው ፡ «ሰይጣን ፡ መጣ ፡» ሲሉት ፡ ቆራጣ ፡ ጅራቱን ፡ እግሩ ፡ መካከል ፡ ሸጉጦ ፡ ወደ ፡ መደበቂያው ፡ ቦታ ፡ ይፈተለክና ፡ ከመርከበኞቹ ፡ አንዱ ፡ በቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ የሰላም ፡ ፉጨት ፡ ሲያሰማው ፡ ብቻ ፡ ተመልሶ ፡ ይመጣል ።

መርከበኞቹ ፡ ውሻውን ፡ ወደ ፡ መድረክ ፡ ይዘውት ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ የሚሄዱት ፡ ዋና ፡ መኰንናቸው ፡ በሚበላበት ፡ ወይም ፡ በሚተኛበት ፡ ሰዓት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውሻው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨዋታ ፡ እያሳየ ፡ ያስደስታቸዋል ። «አይዞህ ፡ አትፍራ ፡ ቆሪጥ ፤ «ጨቅጫቂ ፡» እንደሆን ፡ የለም ፡» ይሉታል ። ቆሪጥ ፡ ጨዋታውን ፡ ሲያሳይ ፡ ድንገት ፡ «ጨቅጫቂ ፡» እንዳይመጣም ፡ አስቀድሞ ፡ የሚናገር ፡ ዘብ ፡ ያቆማሉ ። ቆሪጥ ፡ ቀን ፡ እንቅልፉን ፡ ይለጥጥና ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ጨረቃ ፡ በሌለችበት ፡ ሌሊት ፡ እንደልቡ ፡ እየቦረቀ ፡ ከመርከበኞቹ ፡ ጋር ፡ ይጫወታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ኰችኔቭ ፡ ተረኛ ፡ ጠባቂ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አብሮት ፡ መጠበቁንና ፡ መርከቦች ፡ ባለፉ ፡ ቁጥር ፡ ጮኾ ፡ ምልክት ፡ መስጠቱን ፡ አቆመ ። አይጠዳሽ ፡ ኰችኔቭም ፡ ያ ፡ አጥብቆ ፡ የሚጠላው ፡ «ጨቅጫቃው ፡ ሰይጣን ፡» ምናልባት ፡ ውሻውን ፡ ያገኘው ፡ እንደሆን ፡ መዓቱን ፡ ያወርድበታል ፡ ብሎ ፡ በመፍራት ፡ ተረኛ ፡ ሲሆን ፡ ብቻውን ፡ ይጠብቅ ፡ ጀመር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጥንቃቄ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ በቆሪጥ ፡ ላይ ፡ ጉድ ፡ ፈላበትና ፡ አረፈ ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

በታው ፡ በቻይና ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ የቀኑ ፡ ሙቀትም ፡ የሚያቃጥል ፡ ነው ። በጠራው ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ቅንጣት ፡ ደመና ፡ እንኳ ፡ አይታይም ፤ ባሕሩም ፡ ጸጥ ፡ እረጭ ፡ ብሏል ። ነፋሱ ፡ ከጧት ፡ ጀምሮ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ነበርና ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያዎቹም ፡ ረግበው ፡ ስለነበር ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ለሞተር ፡ ክፍል ፡ ሠራተኞቹ ፡ እንፋሎት ፡ እንዲሰጡ ፡ አዘዘ ። ወዲያውም ፡ እንፋሎቱ ፡ መቡለቅለቅ ፡ ጀመረ ፤ «ሞጉቺይም ፡» የነፋስ ፡ መወጠሪያዎቿን ፡ ሁሉ ፡ ጠቅልላ ፡ ወደ ፡ ናጋሳኪ ፡ በፍጥነት ፡ ጉዞዋን ፡ ቀጠለች ።

በተለይም ፡ አዲሱ ፡ ዋና ፡ መኰንን ፡ «ሞጉቺይ ፡» ንጹሕ ፡ ሆና ፡ ወደ ፡ ናጋሳኪ ፡ እንድትደርስ ፡ ስለፈለገ ፡ (አድሚራሉ ፡ እዚያ ፡ ስብሰባ ፡ ስለሚያደርግ ፡) መርከቧን ፡ ለሶስተኛ ፡ ጊዜ ፡ እየዞረ ፡ ይፈትሽ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ጐደለ ፡ ያ ፡ ጐደለ ፡ እያለም ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ሲነቅፍ ፡ የጨቅጫቃ ፡ ሰው ፡ መጨረሻ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። መርከቧ ፡ ከግር ፡ እስከ ፡ እራሷ ፡ ተወልውላ ፡ ንጽሕናዋ ፡ በጠራው ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ እንደጋለ ፡ የብረት ፡ አለሎ ፡ በምታንጸባርቀው ፡ ፀሐይ ፡ ሥር ፡ ቢያበራም ፡ ቅሉ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ግን ፡ ከፍቶት ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሰው ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ከመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ጋር ፡ የማያስደስት ፡ ንግግር ፡ አድርጐ ፡ ስለነበር ፡ ተበሳጭቷል ። «ደካማ ፡ ሰው ፡» ብሎ ፡ የሚጠራው ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ላገልግሎት ፡ ይጠቅማል ፡ እያለ ፡ የሚያቀርብለትን ፡ ሐሳብ ፡ ሁሉ ፡ አልተቀበለውም ። በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ያለውም ፡ ግንኙነት ፡ በየጊዜው ፡ እየደፈረሰ ፡ ሄደ ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ወጣቶቹ ፡ እጩ ፡ መ



ኰንኖች ፡ ሊከሳቸው ፡ በማይችልበት ፡ መንገድ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ያቆስሉት ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በንዴት ፡ ስለተቃጠለም ፡ በነዚህ ፡ «ዴሞክራት ፡ ነን ፡» በሚሉና ፡ ደንብና ፡ ሥርዓት ፡ ፍጹም ፡ ሳይገባቸው ፡ ሥልጣንን ፡ በሚጋፉ ፡ ደንቆሮ ፡ መስኮቦች ፡ ሥር ፡ መሥራት ፡ ለእንደርሱ ፡ ያለ ፡ ጨዋ ፡ መኰንን ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ አስቸጋሪ ፡ መሆኑን ፡ በትዕቢት ፡ መንፈስ ፡ ያስብ ፡ ጀመር ።

ይህን ፡ እያሰበ ፡ ወደታችኛው ፡ መድረክ ፡ ወርዶ ፡ ወደ ፡ ተራ ፡ መርከበኞቹ ፡ መኖሪያ ፡ ሰፈር ፡ ሲደርስ ፡ ቆሪጥ ፡ ድንገት ፡ በፊቱ ፡ በኩል ፡ ሮጦ ፡ አለፈና ፡ ወደላይኛው ፡ መድረክ ፡ ወጣ ።

«ያ ፡ ቆሻሻ ፡ ውሻ ፡ አሁንም ፡ አለ ፡ እንዴ!» አለ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ለራሱ ፡ ቆሪጥን ፡ ድንገት ፡ ስላየው ፡ በመገረም ።

ወዲያውም ፡ ዓይኑን ፡ በጥላቻ ፡ መልክ ፡ ከመድረኩ ፡ ወዳንደኛው ፡ ክፍል ፡ አተኩሮ ፡ እየተመለከተ ፤

«የሥራ ፡ ኃላፊውን ፡ ጥራልኝ!» አለ ፡ በጩኸት ።

ከጥቂት ፡ ሴኰንድ ፡ በኋላ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ጐርዴየቭም ፡ መጣ ።

«ምንድን ፡ ነው ፡ ያ?» ብሎ ፡ በቀስታና ፡ ኮስተር ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እየጠነቆለ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ጠየቀው ።

ጐርዴየቭም ፡ የሰውዬው ፡ ረጅምና ፡ ነጭ ፡ እንዲሁም ፡ ቀለበት ፡ የተሰካበት ፡ ጣት ፡ የሚያመለክትበትን ፡ አቅጣጫ ፡ ሲያይ ፡ ሐፍረት ፡ ተሰማው ።

«ምንድን ፡ ነው ፡ እኮ?»

«ይቅርታ ፡ ጌታዬ ፡ እራስዎ ፡ ይመልከቱታ ፡...» ኋላም ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ሆዱን ፡ እየከፋው ፡ ስም ፡ ሰጠው ።

ዋናው ፡ መኰንን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ አለና ፤ ቀጥሎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«የነገርኩህን ፡ ታስታውስ ፡ የለም?»

«አዎን ፡ ጌታዬ ፡» አለ ፡ ጐርዴየቭ ፡ ከበፊቱ ፡ በጣም ፡ እየከፋው ።

«ባምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ያን ፡ ቆረቆራም ፡ ውሻ ፡ አውርደህ ፡ እንድትጥል ።»

«ይቅርታ ፡ ጌታዬ ፡ ውሻው ፡ ታሟል ፡» አለ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ባክብሮት ፡ ድምጽ ። «የሐኪሙ ፡ ረዳት ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ መርምሮት ፡ ሆዱን ፡ ታሟል ፡ አለ ፤ ግን ፡ ቶሎ ፡ ይድናል ። ባይታመም ፡ ኖሮ ፡ ጌታዬ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አይሠራም ፡ ነበር ። እባክዎ ፡ ጌታዬ ፡ ይቅርታ ፡ ያድርጉለት ፡» ሲል ፡ ድምጹ ፡ በሐዘን ፡ ስሜት ፡ እየተርገበገበ ፡ ተናገረ ።

«ጐርዴየቭ! እኔ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሰጠሁትን ፡ ትዕዛዝ ፡ መደጋገም ፡ አልወድም ። የምታወራውን ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያምናል ፡ ብለህ ፡ አታስብ ። የሰጠሁት ፡ ትዕዛዝ ፡ መፈጸሙን ፡ ባምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ መጥተህ ፡ እንደታስታውቀኝ ፡ እፈልጋለሁ ! ወለሉም ፡ እንዲጠረግ!» አለ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ጨምሮ ።

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ሄደ ።

«እህ ፤ አንት ፡ ክፉ ፡ አውሬ!» ብሎ ፡ ጐርዴየቭ ፡ ክልቡ ፡ በቀስታ ፡ ተናገረ ።

ወደ ፡ መድረኩም ፡ ሄዶ ፡ ቆሪጥን ፡ ለማውረድ ፡ የሚጠብቀውን ፡ ኰችኔቭን ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ እየተበሳጨ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«ተይዘናል ፡ ወዳጄ ። ውሻው ፡ መድረኩን ፡ ሲያቆሽሽ ፡ «ጨቅጫቃው ፡ ሰይጣን ፡» አገኘው ፡ እና ፡ ...»

የጀመረውን ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ በመጨረስም ፡ ፈንታ ፡ በሐዘን ፡ እራሱን ፡ ነቀነቀ ።



ኮችኔቭም ፡ ነገሩ ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ ገባው ። ፊቱ ፡ ወዲያው ፡ ተለውጦ ፡ ጡንጫው ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ጀመር ። ለጥቂት ፡ ሴኰንድ ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ድርቅ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ።

«የፈረደበት ፡ ውሻ ፡ እንዴት ፡ ያሳዝናል!» አለና ፡ ተነፈሰ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ። «ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ መዘዘኛ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርጉታል?»

«ዛኻሪች! ዛኻሪች!» አለ ፡ ኰችኔቭ ፡ በሚያሳዝን ፡ ድምጽ ። «ቆሪጥ ፡ ታሟል ። ታዲያ ፡ ሲያመው ፡ ምን ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል? እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ በጣም ፡ ቢያመው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አለበለዚያ ፡ ብልህ ፡ ውሻ ፡ ነው ። ያውቃል ፤ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራም ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ አልሠራም ። ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ወደላይኛው ፡ መድረክ ፡ ሲመላለስ ፡ ነው ፡ የዋለው ። ዛኻሪች! እባክህ ፡ ያን ፡ ሰይጣን ፡ ውሻው ፡ አሞት ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ በልና ፡ ንገረው ።»

«ያለነገርሁት ፡ መሰለህ? እኔ ፡ ለቆሪጥ ፡ ስል ፡ አልለመንኩትምና ፡ ነው! ግን ፡ ፍንክች ፡ አላለም ። «ውሻው ፡ ከመርከብ ፡ ወርዶ ፡ መውደቅ ፡ አለበት ፡» አለ ፤ «ባምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ!»

«ዛኻሪች! እባክህ ፡ ሂድና ፡ እንደገና ፡ ጠይቀው ፡ ውሻው ፡ ታሟል ፤ ንገረው ።»

«እሞክራለሁ ፤ ግን ፡ የሚጠቅም ፡ አይመስለኝም ። ይህ ፡ አውሬ!» አለና ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ።

ቆሪጥ ፡ በመታመሙ ፡ ምክንያት ፡ እንደወትሮው ፡ መፈንደቁ ፡ ቀርቶ ፡ ፈዟል ፡ ዓይኑም ፡ ደክሟል ። በሐፍረትና ፡ በመጸጸት ፡ ስሜት ፡ ወደ ፡ ኰችኔቭ ፡ መጥቶ ፡ እጁን ፡ ላሰው ። ኰችኔቭም ፡ በፍቅር ፡ ጀርባውን ፡ ሲዳብሰው ፡ ጭግግ ፡ ያለው ፡ ፊቱ ፡ ባልተለመደ ፡ ደስታ ፡ አበራ ።

ካንድ ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ተመልሶ ፡ መጣ ። ጭግግ ፡ ካለው ፡ ፊቱ ፡ የሄደበት ፡ ጉዳይ ፡ ያልተከናወነለት ፡ ለመሆኑ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

«ማዕርግህ ፡ ይገፈፋል ፡ ብሎ ፡ አስፈራራኝ ፡» አለ ፡ በቁጣ ፡ እያጉረመረመ ።

«ጐበዝ!» አለ ፡ ወደ ፡ መርከበኞቹ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፤ «ያ ፡ መዘዘኛ ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ እንደሚፈልግ ፡ ሰምታችኋል? ፡ የመርከባችንን ፡ ውሻ ፡ እባሕር ፡ ውስጥ ፡ ለመጣል ፡ ምን ፡ መብት ፡ አለው? ማንስ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠው?»

ያዘነ ፡ ፊቱም ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ አበራ ። ዓይኖቹም ፡ በንዴት ፡ ተንቀለቀሉ ።

መርከበኞቹም፡ በንዴት ፡ እያጉረመረሙ ፤ እንዲህ ፡ አሉ ፤

«ይሄ ፡ የተረገመ ፡ «ጨቅጫቃ ፡ ሰይጣን ፡» አሁንስ ፡ አበዛው!»

«እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ለማድረግ፡ መብት ፡ የለውም ። አውሬ!»

«አንድ ፡ ምስኪን ፡ ውሻ ፡ ለምን ፡ ተብሎ ፡ ነው ፡ እባሕር ፡ ውስጥ ፡ ተጥሎ ፡ የሚሰምጠው?»

«እናድነው ፡ ጐበዝ! ወደ ፡ መርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ጋ ፡ እንሂድ ። ጨዋ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ፍርድ ፡ አይነሣንም! እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ እንዲፈጸም ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይፈቅድም!» አለ ፡ ኰችኔቭ ፡ እየጮኸና ፡ ቆሪጥ ፡ ይጠፋብኛል ፡ ብሎ ፡ የፈራ ፡ በመምሰል ፡ ውሻውን ፡ እጐኑ ፡ ይዞ ።

«ወደመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ጋ ፡ እንሂድ!» አሉ ፡ ሌሎቹም ፡ አንድነት ፡ እየጮኹ ።

«አኪም ፡ ዛኻሪች! መርከበኞቹን ፡ አሰልፍ!»



ነገሩ ፡ እየጠነከረ ፡ ሄደ ። አኪም ፡ ዛኻሪችም ፡ የኋላ ፡ እራሱን ፡ በስጋት ፡ አከክ ፡ አከክ ፡ አደረገ ።

ያነየውኑ ፡ መርከበኞቹ ፡ የሚወዱት ፡ ወጣቱ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ ኰሹቲች ፡ ወደመርከበኞቹ ፡ ሰፈር ፡ ብቅ ፡ አለ ። መኰንኑን፡ ሲያዩትም ፡ ሰዎቹ ፡ ጸጥ ፡ አሉ ። የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ወደ ፡ መኰንኑ ፡ ቀረበና ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«እንዲህ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፤ ዋናው ፡ መኰንናችን ፡ ቆሪጥን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እንድጥለው ፡ አዞኛል ፤ መርከበኞቹም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተበሳጭተዋል ። አንድ ፡ ምስኪን ፡ ውሻ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ የሚገደለው? ጌታዬም ፡ እንደሚያውቁት ፡ ውሻው ፡ ጨዋ ፡ ነው ፤ ከኛ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ሲጓዝም ፡ ይሄውና ፡ ሁለት ፡ ዓመቱ ፡ ነው ። ትንሽ ፡ ሆዱን ፡ ቢያመው ፡ ተሳሳተ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ያጠፋው ፡ ነገር ፡ የለም ።»

የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ ችግሩ ፡ እንዴት ፡ እንደተፈጠረ ፡ ከገለጸ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጨምሮ ፡ ተናገረ ፤

«ጌታዬ ፡ መልካም ፡ ፈቃድዎ ፡ ቢሆን ፡ ስለቆሪጥ ፡ አቤቱታ ፡ ያቅርቡልን ። ውሻው ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ እንዲቆይ ፡ ይጠይቁልን ።»

ቆሪጥም ፡ ስለምን ፡ እንደሚነጋገሩ ፡ የገባው ፡ በመምሰል ፡ እጩ ፡ መኰንኑን ፡ በወዳጅነት ፡ ዓይን ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ እያየ ፡ ቆራጣ ፡ ጂራቱን ፡ በለዘብታ ፡ አወዛወዘ ።

«ይመልከቱ ፡ ጌታዬ! ቆሪጥ ፡ እራሱ ፡ ይለምንዎታል!»

እጩ ፡ መኰንኑም ፡ በሰማው ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ስላዘነ ፡ ለውሻው ፡ ሲል ፡ አማላጅ ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ ሰጠ ። በመርከበኞቹ ፡ መካከል ፡ የተነሣውም ፡ ሁከት ፡ ጸጥ ፡ አለ ። የኰችኔቭ ፡ ፊትም ፡ በተስፋ ፡ አበራ ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

«ባሮን ፡ ሆይ!» አለ ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ፡ ወደ ፡ መኰንኖች ፡ ክፍል ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ ሲገባ ፤ «መላው ፡ መርከበኞች ፡ ትዕዛዝዎን ፡ እንዲሰርዙና ፡ ቆሪጥ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ይጠይቁዎታል ። መርከበኞቹ ፡ ውሻቸው ፡ የሚወሰድባቸው ፡ ለምንድን ፡ ነው? ውሻውስ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ አጠፋ ፡ ጌታዬ?»

«ይህ ፡ ያንተ ፡ ተግባር ፡ አይደለም ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ ኰሹቲች ፡» ሲል ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ መለሰለት ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ እንዳትገባ ፡ አሳስብሃለሁ ። ውሻው ፡ መውደቅ ፡ አለበት ።»

«ይመስልዎታላ?»

«ዝም ፡ በል! እባክህ ፡» አለ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ፊቱ ፡ መንጣት ፡ እየጀመረ ።

«በጭካኔ ፡ ውሳኔዎ ፡ መርከበኞቹን ፡ ለማበሳጨት ፡ አስበዋላ?» አለ ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ፡ በንዴት ፡ እየጋለ ። «እንግዲያውስ ፡ አይሆንልዎትም ። በቀጥታ ፡ ወደመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ጋ ፡ እሄዳለሁ።»

ወደመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ክፍል ፡ ሄደ ።

ሌሎቹም ፡ በመኰንኖች ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ መኰንኖች ፡ ዋናውን ፡ መኰንን ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ የጥላቻ ፡ መንፈስ ፡ ተመለከቱት ፤ እሱም ፡ በነጭ ፡ ፊቱ ፡ ላይ ፡ የጥላቻ ፡ ፈገግታ ፡ እያሳየ ፡ ጢሙን ፡ በሐፍረት ፡ ያፍተለትል ፡ ጀመር ።

ከሁለት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላም ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ አሽከር ፡ ወደ ፡ መኰንኖቹ ፡ ክፍል ፡ መጣና ፡ ዋናውን ፡ መኰንን ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ እንደሚፈልገው ፡ ነገረው ።

«ምንድነው ፡ እሱ ፡ ስለውሻው ፡ የምሰማው ፡ ነገር ፡ ባሮን?» ብሎ ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ በቀጥታ ፡ ጠየቀው ።



«ምንም ፡ አይደል ፡ ጌታዬ ። አውርደው ፡ እንዲጥሉት ፡ አዝዣለሁ ፡» አለ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ በርጋታ ።

«በምን ፡ ምክንያት?»

«ውሻው ፡ መድረክ ፡ሲያቆሽሽ ፡ ባገኘው ፡ አውርጄ ፡ እጥለዋለሁ ፡ ብዬ ፡ አስጠንቅቄያቸው ፡ ነበር ። አሁን ፡ ቅድም ፡ መድረኩን ፡ ሲያቆሽሽ ፡ አገኘሁት ፡ ስለዚህ ፡ እንዲጣል ፡ አዘዝኩ ። የመርከብ ፡ ደንብና ፡ ሥርዓት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ከተፈለገ ፡ የዋናው ፡ መኰንን ፡ ትዕዛዝ ፡ መከበር ፡ አለበት ።»

«አንት ፡ ድንጋይ ፡ እራስ ፡ ጀርመን!» በማለት ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ በቃል ፡ ሳይሆን ፡ በልቡ ፡ አሰበና ፡ ፊቱ ፡ ኰስተር ፡ አለ ።

በጩኸት ፡ ቃልም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«ባሮን ፡ ሆይ ፤ የሰጠኸውን ፡ ትዕዛዝ ፡ አሁኑኑ ፡ ሰርዝ ፤ ውሻውም ፡ በሰላም ፡ አርፎ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ተወው ። በመርከቧ ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጥ ፡ የፈቀድኩለት ፡ እኔ ፡ ነኝ ። አዝናለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ትዕዛዝህን ፡ መሰረዝ ፡ አለብህ ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትዕዛዝ ፡ በመስጠት ፡ መርከበኞቹን ፡ ያላንድ ፡ ምክንያት ፡ ማበሳጨት ፡ የለብህም ።»

«እንግዲያውስ ፡ ጌታዬ ፡ ትዕዛዙን ፡ እራስዎ ፡ መሻር ፡ አለብዎት ፤ እኔ ፡ ላደርገው ፡ አልችልም ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡...»

«ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ምን?» አለና ፡ ጠየቀ ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ ባጭሩ ።

«ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ አሞኛልና ፡ ከዋና ፡ መኰንንነት ፡ ተግባሬ ፡ እንደሰናበት ፡ እጠይቃለሁ ።»


«እንግዲያውስ ፡ የስንብት ፡ ደብዳቤ ፡ አስገባ ፡ ምናልባት ፡ የወደብ ፡ ላይ ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፡ ለጤናህ ፡ ሳይስማማህ ፡ አይቀርም ።»

ዋናው ፡ መኰንን ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ወጣ ።

በሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ መርከቧ ፡ ናጋሳኪ ፡ ስትደርስ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ወረደ ። መርከበኞቹም ፡ ሁሉ ፡ ተደሰቱ ። ሌላ ፡ ዋና ፡ መኰንንም ፡ በሱ ፡ ምትክ ፡ ተሾመ ። መርከበኞቹ ፡ እፎይ ፡ አሉ ።

ቆሪጥ ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ እንደወትሮው ፡ የደስታና ፡ የነፃነት ፡ ሕይወት ፡ ጀመረ ። የተጠላውንና ፡ «ጨቅጫቃውን ፡ ሰይጣን ፡» ለማስወገድ ፡ ምክንያት ፡ በመሆኑም ፡ መርከበኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ከዱሮው ፡ ይበልጥ ፡ ወደዱት ።

ቆሪጥ ፡ እንደወትሮው ፡ ከኰችኔቭ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ወደብ ፡ እየወረደ ፡ ይጠብቀው ፡ ነበር ። እንደወትሮውም ፡ የሚያልፉ ፡ መርከቦች ፡ መጠበቁንና ፡ መርከበኞቹንም ፡ ማጫወቱን ፡ ቀጠለ ፡ «ጨቅጫቃው ፡ ሰይጣን ፡» መጣ ፡ ሲሉትም ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ዘሎ ፡ ይሮጥና ፡ ጠላቱ ፡ በመርከቧ ፡ ላይ ፡ እንደሌለ ፡ በማወቅ ፡ ወዲያው ፡ ተመልሶ ፡ ይመጣል ።




ምዕራፍ ፡ ፩ ።

«የነሡ ፡ ጌታዬ! አሌክሳንደር ፡ ኢቫኖቪች! ይነሡ!»

ይህን ፡ ቃል ፡ የተናገረው ፡ ኪሪሎቭ ፡ የተባለው ፡ የእጩ ፡ መኰንን ፡ መርከበኛው ፡ የኦፖልየቭ ፡ አሽከር ፡ ጌታውን ፡ ሲጠራ ፡ ነው ። ኪሪሎቭ ፡ አጠር ፡ ወፈር ፡ ያለና ፡ መልከ ፡ ጠይም ፤ ባንደኛው ፡ ጆሮውም ፡ ላይ ፡ ቀለበት ፡ ያንጠለጠለ ፡ ወጣት ፡ መርከበኛ ፡ ነው ። እንዳይወድቅ ፡ እግሩን ፡ አንፈራጦ ፡ ቁሞና ፡ ባንድ ፡ እጁም ፡ የበሩን ፡ እጀታ ፡ ጨብጦ ፡ ይዞ ፡ በሌላው ፡ እጁ ፡ የእጩ ፡ መኰንኑን ፡ እግር ፡ በለዘብታ ፡

ይጐትታል ። «ሶኮል ፡» የተባለችውን ፡ መርከብ ፡ አትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ላይ ፡ እንደተጣለች ፡ ኳስ ፡ ሁሉ ፡ ኃይለኛ ፡ ማዕበል ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲያላጋት ፡ እጨ ፡ መኰንኑ ፡ ግን ፡ እትንሽ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ።

መልስም ፡ አልሰጠም ።

እጨ ፡ መኰንኑ ፡ እንቅልፍ ፡ ወዳድ ፡ ነበር ። «ቶሎ ፡ ይነሡ ፡ እንጂ ፡» ይላል ፡ አሽከሩ ።

ጌታው ፡ ፈጥኖ ፡ ካልተነሣና ፡ የጥበቃ ፡ ተግባሩን ፡ ካልጀመረ ፡ አንድ ፡ ደቂቃ ፡ እንኳ ፡ ቢዘገይ ፡ ቁጣ ፡ እንደሚደርስበት ፡ ኪሪሎቭ ፡ ስላወቀ ፡ ጥቂት ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ የጌታውን ፡ እግር ፡ መነቅነቁን ፡ ቀጠለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኃይል ፡ እየጐተተ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ይነሡ! የመጠበቂ ፡ ሰዓት ፡ ደርሷል ። ጌታዬ ፡ አሌክሳንደር ፡ ኢቫኖቪች ፡ እባክዎ ፡ ይነሡ!»

«ሰይጣን ፡ ይዞህ ፡ ይሂድ!» አለ ፡ ሰውየው ፡ በእንቅልፍ ፡ ልቡ።

«መነሣት ፡ አለብዎት ፡ ጌታዬ ፡ አሌክሳንደር ፡ ኢቫኖቪች!»

«ሞቻለሁ ፡» አለ ፡ እጨ ፡ መኰንኑ ፡ በማጉመትመት ። «ወዲያ ፡ ሂድ ።»

አሽከሩ ፡ ሲጐትተው ፡ የነበረውን ፡ እግሩን ፡ ፈርገጥ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ የብርድ ፡ ልብሱን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሳብ ፡ አድርጐ ፡ ተከናነበና ፡ በሌላ ፡ ጐኑ ፡ ተገላብጦ ፡ ሊተኛ ፡ ሲል ፡ መርከቧ ፡ በድንገት ፡ በኃይል ፡ ተላጋችና ፡ ግንባሩን ፡ ግድግዳው ፡ ሲመታው ፡ ቁልጭ ፡ ብሎ ፡ ነቃ ።

ካልጋው ፡ ውስጥ ፡ ገና ፡ እንቅልፉ ፡ ያልወጣለት ፡ የተዋበ ፡ ለስላሳና ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ የልጅ ፡ ፊት ፡ ያለውና ፤ ነጭ ፡ ሐር ፡ መሳይ ፡ ጢምም ፡ ማብቀል ፡ የጀመረ ፤ እሪዙም ፡ ያቆጠቆጠ ፤ የተጠቀለለ ፡ ጸጉሩም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ማሽላ ፡ ጸጉር ፡ ወርቅማ ፡ የሆነ ፡ ወጣት ፡ ብቅ ፡ አለ ። ትላልቅ ፡ ቡናማ ፡ ዓይኖቹን ፡ ጭፍን ፡ ጭፍን ፡ እያደረገ ፡ እንደሚያልም ፡ ሐጻን ፡ በደስታ ፡ ፈገግ ፡ አለ ። ምናልባት ፡ በሕልም ፡ ሠረገላ ፡ ወደሌላ ፡ ሩቅ ፡ ቦታ ፡ ሳይሄድ ፡ አልቀረም ።



በሕልሙ ፡ በገጠር ፡ በሚገኝ ፡ ባንድ ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። አትክልቱም ፡ በለምለም ፡ ዕጸዋትና ፡ በተዋቡ ፡ አበባዎች ፡ ያጌጠ ፡ ነበር ። መዓዛ ፡ ያላቸው ፡ ዛፎችም ፡ መልተውበት ፡ ነበር ። ከዛፎቹ ፡ ሥር ፡ ባንድ ፡ በሚወዛወዝ ፡ ትንሽ ፡ የማንቃ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ «ሌናና ፡ አሌክሳንደር ፡ » የሚል ፡ ስም ፡ ተቀርጾበታል ። አንድ ፡ የተዋበች ፡ ልጃገረድ ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ እጐኑ ፡ ተቀምጣለች ። በሐሳብ ፡ የተመሉት ፡ ጥቋቁር ፡ ዓይኖቿ ፡ ፍቅርን ፡ አዝለዋል ። በዞማው ፡ ጸጉሯ ፡ ላይ ፡ አበባ ፡ ሻጥ ፡ አድርጋለች ። ፍቅር ፡ በለበሰው ፡ ዓይኖቿ ፡ የልጁን ፡ ዓይን ፡ አተኩራ ፡ እየተመለከተች ፡ ሙሽራው ፡ የሚያፈሰውን ፡ የፍቅር ፡ ቃል ፡ ትሰማለች ። ንግግሩን ፡ በማቋረጥ ፡ ይህን ፡ የደስታ ፡ ሰዓት ፡ ለማበላሸት ፡ ስላልፈቀደችም ፡ በለስላሳው ፡ እጅዋ ፡ የሱን ፡ እጅ ፡ አጥብቃ ፡ ይዛለች ፤ በቅንድቦቿም ፡ ላይ ፡ የንባ ፡ ጤዛ ፡ ይታያል ። «ለዘላለሙ ፡ የኔ ፡ ነህ ፡» አለች ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ። «ለዘላለም ፡ ያንቺ ፡ ነኝ ፡» አለ ፡ እሱም ፡ በቀስታ ። ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያህልም ፡ እዚያው ፡ እንደተቀመጡ ፡ ቆዩ ። የተዋበውና ፡ የረጋው ፡ ምሽትም ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ ደስታ ፡ እንደለበሱ ፡ እዚያው ፡ አገኛቸው ። ያትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ጭር ፡ አለ ። ምንም ፡ ዓይነት ፡ ድምጽ ፡ አይሰማም ፡ ነበር ። የሰማይ ፡ ከዋክብትም ፡ ሁለቱን ፡ ተፋቃሪዎች ፡ የሚያደንቁና ፡ የልባቸውን ፡ በደስታ ፡ መሸበርም ፡ የሚያዳምጡ ፡ በመምሰል ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ይላሉ ።

«ሌናዬ! አሌክሳንደር ፡ ኢቫኖቪች ፡ ኑና ፡ ሻይ ፡ ጠጡ!» የሚለው ፡ የሌና ፡ እናት ፡ ድምጽ ፡ አሁንም ፡ በጆሮው ፡ ውስጥ ፡ ይሰማዋል ።

በሕልሙ ፡ ያየው ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሚያስጐመጅ ፡ ትርኢት ፡ እውነት ፡ መሰለው ። ለወጣቱ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ መርከበኛ ፡ ይህ ፡ ሕልም ፡ ገና ፡ ጉልህ ፡ ሆኖ ፡ ይታየው ፡ ስለነበር ፡ ሳይጠፋበት ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ሊያቆየው ፡ ፈለገ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ከጥቂት ፡ ሴኰንዶች ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ጭስ ፡ በኖ ፡ ጠፋ ።

የክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ብርሃን ፡ ደብዘዝ ፡ ያለ ፡ ነው ። ወደውጭ ፡ የሚያሳየው ፡ በብርጭቆ ፡ የተደፈነ ፡ ክብ ፡ መስኮት ፡ በውኃ ፡ አረፋ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይሸፈን ፡ ስለነበር ፡ ባልተሸፈነበት ፡ ጊዜ ፡ የጧት ፡ ብርሃን ፡ በደበዘዘው ፡ መስታዋቱ ፡ ውስጥ ፡ አልፎ ፡ ገባ ። ኦፖልየቭ ፡ የቀልጣፋውንና ፡ የብልሁን ፡ አሽከሩን ፡ ቅርጽ ፡ አየ ። ኪሪሎቭ ፡ እንዳይወድቅ ፡ የሚደግፈውን ፡ ነገር ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ አጥብቆ ፡ ይዞ ፡ ከክፍሉና ፡ በክፍሉም ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ እቃ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ይወዛወዝ ፡ ነበር ። ኦፖልየቭ ፡ የጦር ፡ መርከቧ ፡ በኃይል ፡ ስትላጋና ፡ ስትንቋቋ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ማዕበሉ ፡ ኃይለኛ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳና ፡ በሙሉ ፡ ነቃ ።

የደስታ ፡ ፈገግታውም ፡ ከፊቱ ፡ ላይ ፡ ጠፋ ።

«እረ ፡ በእግዚአብሔር! እንዴት ፡ ትላጋለች!» አለ ፡ ካልጋው ፡ ለመነሣትና ፡ ግድግዳውም ፡ እንዳይመታው ፡ እየሞከረ ። ፊቱም ፡ ኮስተር ፡ አለ ።

«ማዕበሉ ፡ ኃይለኛ ፡ ነው ፡ ጌታዬ!» አለ ፡ አሽከሩ ።

«ስንት ፡ ሰዓት ፡ ነው?»

«ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሊሆን ፡ ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ቀርቶታል ።»

«በመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይስ ፡ እንዴት ፡ ነው?»

«እግዚአብሔር ፡ ያውጣን ፡ እንጂ! መዓት ፡ ነው!»

«ባንድ ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ ኃይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ተነሥቶ ፡ አድሯል ፡ ማለት ፡ ነዋ?»



«አዎን ፡ ጌታዬ ፤ የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሸራዎቹን ፡ አውርደው ፡ ጠቅልለዋቸዋል ። የመርከቧ ፡ አዛዥም ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ በላይ ፡ በኩል ፡ ነቅተው ፡ ነው ፡ ያደሩት ፡» ሲል ፡ አሽከሩ ፡ አስታወቀ ።

ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ካለ ፡ በኋላም ፡ ወጣቱ ፡ መርከበኛ ፡ (ረጅም ፡ ጉዞ ፡ ሲያደርግ ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜው ፡ ነበር ፡) እንዲህ ፡ ሲል ፡ ፍርሃት ፡ በለበሰ ፡ ድምጽ ፡ ጨምሮ ፡ ተናገረ ፤

«በመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መርከበኞች ፡ ኃይለኛ ፡ ማዕበል ፡ ሳይመጣ ፡ አይቀርም ፡ ይላሉ ፡ ጌታዬ! ነፋሱ ፡ በነፋስ ፡ መወጠሪያው ፡ ገመዶች ፡ መካከል ፡ ያፏጫል ። ባሕሩም ፡ እግዜር ፡ ይሰውረን ፡ እንጂ ፡ የሚንከባለል ፡ ተራራ ፡ ይመስላል ።

«ማዕበል ፡ ትፈራለህ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ገባኝ ።»

«አዎን ፡ ጌታዬ ፤ እንዴታ ፡» አለ ፡ ወጣቱ ፡ መርከበኛ ፡ በየዋህነትና ፡ በሐፍረት ።

«ምንም ፡ የሚያስፈራ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ወዳጄ ። ከማዕበል ፡ እንደምንም ፡ ለማለፍ ፡ እንችላለን!» አለ ፡ ወጣቱ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ በልበ ፡ ሙሉነትና ፡ በግዴለሽነት ። በውነቱ ፡ ግን ፡ እሱም ፡ እራሱ ፡ ቢሆን ፡ ማዕበል ፡ ሲነሣ ፡ አይቶ ፡ አያውቅም ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ስሜቱን ፡ ለመደበቅ ፡ ቢሞክርም ፡ ቅሉ ፡ ማዕበሉ ፡ መርከቧን ፡ እባሕር ፡ ላይ ፡ እንደወደቀ ፡ ኩበት ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲያላጋት ፡ ስጋት ፡ አደረበት ።

«አዎን ፡ ጌታዬ ፡» ሲል ፡ ኪሪሎቭ ፡ ከጌታው ፡ ሐሳብ ፡ ጋር ፡ ለመስማማት ፡ ፈጠነ ። ይህን ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ ስለታዛዥነቱና ፡ የጌታውን ፡ ቃል ፡ ለመቃወም ፡ ሥርዓቱ ፡ ስለማይፈቅድለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ።

ወጣቱ ፡ መርከበኛ ፡ ምንም፡ እንኳ ፡ ፍርሃቱን ፡ ሊደብቅ ፡ ሞክርም ፡ ቅሉ ፡ አልሆነለትም ።

«በመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ይበርዳልን?»

«እንደ ፡ ስለት ፡ ነው ፡ ጌታዬ ።»

«ከላይ ፡ የምለብሰውን ፡ የዝናብ ፡ ልብስ ፡ አውጥተሃል?»

«አዎን ፡ ጌታዬ ።»

«መልካም ። እንግዲህ ፡ ልነሣ ።»

ከሞቀ ፡ አልጋው ፡ ውስጥ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ፡ መርከበኛ ፡ እንደገና ፡ የቀድሞው ፡ ትዝታ ፡ ሊያፈዘው ፡ ነበር ፤ በተለይም ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፡ ሕልሙ ፡ ዕውነት ፡ ቢሆንለት ፡ ይወድ ፡ ነበር ፤ በድንገት ፡ ትንፋሹን ፡ ሳይወድ ፡ ሳብ ፡ አድርጎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«እመሬት ፡ ላይ ፡ ብንሆን ፡ የተሻለ ፡ ነበር ፡ ኪሪሎቭ? አይመስልህም?»

«መጠርጠሩስ ፡ ጌታዬ ፡» አለ ፡ ወጣቱ ፡ መርከበኛ ፡ በደስታ ፡ ስሜትና ፡ ፊቱ ፡ በፈገግታ ፡ እያበራ ። «ሰው ፡ በደረቀ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ ይሻለዋል ። ማለት ፡ በሚርግጠው ፡ አፈር ፡ ላይ! እዚህ ፡ ግን ፡ ሲኦል ፡ ነው ። ነፃ ፡ ብሆን ፡ ኖሮ ፡ ወደ ፡ መንደሬ ፡ በቀጥታ ፡ እሄድ ፡ ነበር ።»

«ዕውነት?» አለ ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ፡ ፈገግ ፡ እያለ ።

«አዎን ፡ ጌታዬ! አዎን!»

«እኔ ፡ ደግሞ ፡ በቀጥታ ፡ ዛሲኸርየ ፡ ወደሚባለው ፡ ቦታ ፡ እሄድ ፡ ነበር ፡» አለ ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ፡ በሐሳቡ ።

በቃሉ ፡ ግን ፡ ደስታ ፡ የሌለበት ፡ ፈገግታ ፡ እያሳየ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ምን ፡ ይሆናል ፡ ብቻ ፡ ኪሪሎቭ! ከዚህ ፡ የሚወጣበት ፡ መንገድ ፡ የለም ፤ ያለ ፡ ይመስልሃል?»



«የለም ፡ ጌታዬ ፤ ሜዳው ፡ ሁሉ ፡ ውኃ ፡ ነው ።»

«ስለዚህ ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ለጊዜው ፡ ሻዬን ፡ ብታፈላልኝ ፡ ይሻላል ። ትኩስ ፡ እንዲሆን ፡ ታዲያ!»

«ጌታዬ ፤ ሻይ ፡ አዘጋጅቻለሁ ፡ እኮ ። ዋናው ፡ መኰንንም ፡ ሻያቸውን ፡ ይጠጣሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ መርከቧ ፡ እንደዚህ ፡ ስትላጋ ፡ ሻይ ፡ ለመጠጣት ፡ ያስቸግራል ፡» አለ ፡ ኪሪሎቭ ፡ በተጨማሪ ። ከዚያም ፡ ለደጉና ፡ ለሚራራለት ፤ እንዲሁም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከልብ ፡ ለሚያጫውተው ፡ ጌታው ፡ ሻይ ፡ ለማምጣት ፡ ሄደ ።

ወደ ፡ ወጥ ፡ ቤቱ ፡ አመራ ። የመርከቧ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ መላጋት ፡ እርሱንም ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ስላማታው ፡ በግሩ ፡ መቆም ፡ አቃተው ። እግረ ፡ መንገዱን ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ የሚያውቀው ፡ አሽከር ፡ ስላገኘ ፡ አንድም ፡ መንፈሱን ፡ ለማነቃቃት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ፍርሃቱን ፡ ከወዳጁና ፡ ከሌሎቹ ፡ መርከበኞች ፡ ለመደበቅ ፡ ሲል ፡ በቀልድ ፡ አስመስሎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«እንደ ፡ ኸረው ፡ ኸረው ፡ ነው! እንኳንስ ፡ ለመራመድና ፡ ለመቆምም ፡ ያዳግታል ።»

ነገሩን ፡ ለማጣፈጥ ፡ ያህልም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጨምሮ ፡ ተናገረ ፤

«ምነው ፡ ቫሲሊይ ፡ ምን ፡ ሆንክ? ፈራህ ፡ እንዴ?»

«...እንትን ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ ማሰቤ ፡ አልቀረም ፡ ... ወይ ፡ ጉድ ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ ማዕበል ፡ ነው!» አለ ፡ ያኛው ፡ አጥወልውሎት ፡ እንዲሁም ፡ ፊቱ ፡ ነጥቶና ፡ ፍርሃት ፡ ለብሶ ።

«እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አታስብ ፡ ቫሲሊይ ። ምን ፡ የሚያስፈራ ፡ ነገር ፡ አለ? ማዕበልም ፡ ከሆነ ፡ ይምጣ ። ማዕበልን ፡ ለማለፍ ፡ እንችላለን!» አለ ፡ ኪሪሎቭ ፡ በድፍረትና ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ፡ የነገረውን ፡ ቃል ፡ እየደጋገመ ።

በልቡ ፡ በፍርሃት ፡ እየራደ ፡ በጥርሱ ፡ ግን ፡ ሳቀ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ወጣቱ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ ፊቱን ፡ ሲታጠብና ፡ ልብሱን ፡ ሲለብስ ፡ እንዳይወድቅ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የአክሮባቲክ ፡ ዘዴ ፡ በመሥራት ፡ ዳነ ። ከአሥር ፡ ደቂቃ ፡ በኋላም ፡ ዝግጁ ፡ ሆኖ ፡ ወጣ ።

በታች ፡ በኩል ፡ አካባቢው ፡ እርጥብና ፡ የታፈገ ፡ ነበር ። የመርከበኞቹም ፡ ክፍል ፡ ነፋስ ፡ ስላልነፈሰበት ፡ አየሩ ፡ ከባድና ፡ የሚሰነፍጥ ፡ ነበር ። ቀዳዳው ፡ ሁሉ ፡ ስለተደፈነም ፡ ንጹሕ ፡ አየር ፡ ፈጽሞ ፡ አይገባም ፡ ነበር ። ተረኛ ፡ ያልሆኑት ፡ መርከበኞች ፡ ፊታቸውን ፡ ቋጥረው ፡ በመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ በጸጥታ ፡ ተቀምጠዋል ፤ ግማሾቹም ፡ ተጋድመዋል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ስለተረገመው ፡ የአየር ፡ ጠባይ ፡ አንዳንድ ፡ ቃል ፡ ጣል ፡ ያደርጋሉ ። አንዳንዶቹም ፡ አጥወልውሏቸዋል ። በሞተሩ ፡ ክፍል ፡ አጠገብ ሽቼርባኮቭ ፡ የተባለ ፡ ሽማግሌ ፡ መርከበኛ ፡ (የመርከቧ ፡ ታቦት ፡ ጠባቂና ፡ ቄስ ፡ ነው ፡) መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ገልጦ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ ያንጐራጉር ፡ ነበር ። በዙሪያውም ፡ ጥቂት ፡ መርከበኞች ፡ ከበው ፡ ተቀምጠው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቋንቋው ፡ ጥንታዊ ፡ ስለሆነ ፡ ባይገባቸውም ፡ ቅሉ ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ በመስማት ፡ ያንባቢውን ፡ የዜማ ፡ ድምጽና ፡ መንፈሳዊ ፡ ቃል ፡ ያደንቁ ፡ ነበር ።

በመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ለመራመድ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ድንገት ፡ ወለሉ ፡ ከሥር ፡ ስለሚሸሽ ፡ ለማቋረጥ ፡ ጊዜውን ፡ መምረጥና ፡ ብዙ ፡ ብልሃትና ፡ ዘዴም ፡ ይጠይቅ ፡ ነበር ።

በተለይም ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፡ ሻይ ፡ ይጠጣ ፡ ስለነበር ፡ የመኰንኖቹ ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ ለወትሮው ፡ ይደምቅ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ባዶ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ። መኰንኖቹ ፡ በሙሉ ፡ በየክፍላቸው ፡ ውስጥ ፡ ተጋድመዋል ። ከጠረጴዛው ፡ በላይ ፡ የተሰቀለው ፡ መብራት ፡ ከወለሉ ፡ ጋር ፡ ታስሯል ። ጣራው ፡ ሲወዛወዝም ፡ አብሮ ፡ ይወዛወዛል ። የመጻሕፍት ፡ መደርደሪያውና ፡ ፒያኖውም ፡ ከወለሉ ፡ ጋር ፡ ጠብቀው ፡ ቢታሰሩም ፡ ቅሉ ፡ ሲጢጥ ፡ ሲጢጥ ፡ ይሉ ፡ ነበር ። በጥብቅ ፡ በተደፈነው ፡ የመኰንኖች ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ የብርሃን ፡ መስጫ ፡ በኩል ፡ ከውጭ ፡ የሚነፍሰው ፡ ኃይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ይሰማል ። የጦር ፡ መርከቧ ፡ ከግር ፡ እስከራሷ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ትወዛወዝ ፡ ነበር ። በተለይም ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ውዝዋዜ ፡ በታች ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ የመርከቧ ፡ ክፍል ፡ የበረታ ፡ ነበር ። የመኰንኖቹ ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ ለወትሮው ፡ ጫጫታና ፡ ውካታ ፤ ሳቅና ፡ ስላቅ ፡ ይበዛበት ፡ የነበረው ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ጸጥ ፡ እረጭ ፡ ብሏል ።

ላይካ ፡ የተባለው ፡ ተጫዋችና ፡ ደስተኛ ፤ ጅራተ ፡ ቆራጣና ፡ ዘረ ፡ ቅልቅል ፡ ውሻ ፡ በመኰንኖቹ ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጥግ ፡ ይዞ ፡ ጥቅልል ፡ ብሏል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ዝቅ ፡ ባለና ፡ በሚያሳዝን ፡ ድምጽ ፡ እያለቀሰ ፡ በዚህ ፡ በሚያዳልጥ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ምስኪን ፡ ውሻ ፡ እንዴት ፡ ሊቆም ፡ ይችላል ፡ በሚል ፡ ጥያቄ ፡ የፈዘዙ ፡ ዓይኖቹን ፡ በዙሪያው ፡ ያንከራትታል ። ይህን ፡ ውሻ ፡ መርከቧ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ወደውጭ ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ ከክሮንሽታድት ፡ ስትነሣ ፡ አብሮ ፡ ከተሳፈረ ፡ በኋላ ፡ መርከበኞቹ ፡ ላይካ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ። ቫስካ ፡ የተባለው ፡ የላይካ ፡ ወዳጅና ፡ የመድፈኛው ፡ መኰንን ፡ ደማም ፡ ነጭ ፡ ድመትም ፡ የለም ። ቫስካም ፡ ሳያጥወለውለው ፡ አልቀረም ።

በመኰንኖቹ ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የተገኘው ፡ ሰው ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሰው ፡ የደረጀና ፡ ጠንካራ ፤ ጸጉረ ፡ ጥቁር ፡ ሲሆን ፡ ዕድሜውም ፡ ሰላሳ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ነው ። አጭርና ፡ ወፈር ፡ ያለ ፡ ኰት ፡ ለብሶ ፡ ባንድ ፡ ሶፋ ፡ ላይ ፡ ተቀምጧል ። በፀሐይ ፡ የጠቆረው ፡ ፊቱም ፡ የስጋትና ፡ የሐሳብ ፡ መልክ ፡ ይ

ታይበታል ። ባንደኛው ፡ ነሐስ ፡ በመሰለው ፡ ጡንቻማና ፡ ጸጉራም ፡ እጁ ፡ አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ሻይ ፡ እንዳይፈስበት ፡ በጥንቃቄ ፡ እያመዛዘነ ፡ በመያዝ ፡ ላይ ፡ ነው ። ሻይውን ፡ ሳያፈስ ፡ ችምችም ፡ ወዳለው ፡ ጥቁር ፡ ሪዙ ፡ ለማስጠጋት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ እስቲገጥመው ፡ ይጠብቃል ።

«እንደምን ፡ አደርክ ፡ አሌክሴይ ፡ ኒኮላዬቪች!»

«ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ አሌክሳንደር ፡ ኢቫኖቪች!»

ወጣቱ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ መርከበኛ ፡ ከጠረጴዛው ፡ አጠገብ ፡ ከወለሉ ፡ ጋር ፡ በምስማር ፡ የተያያዘውን ፡ ወንበር ፡ ጨብጦ ፡ የዋናውን ፡ መኰንን ፡ እጅ ፡ ለመጨበጥ ፡ ሄደ ። ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ ለጥቂት ፡ እላው ፡ ላይ ፡ ሊወድቅበት ፡ ነበር ።

«ነፋሱ ፡ ሌሊቱን ፡ አይሎ ፡ አድሯል ፡ አሉ ፡ አሌክሴይ ፡ ኒኮላዬቪች?» አለ ፡ ወጣቱ ፡ ልጅ ፡ በሶፋው ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ እየተቀመጠ ።

«አዎን ፡ አይሏል ፡» አለ ፡ ያኛው ፡ ባጭሩ ።

ሻይውን ፡ ጸጥታ ፡ በተመላበት ፡ ሐሳብ ፡ ፉት ፡ እያለ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

«እነዚህ ፡ እግዜር ፡ የረገማቸው ፡ ባሕሮች! ያልተጠነቀቅን ፡ እንደሆን ፡ ከጀልባዎቻችን ፡ አንዱን ፡ ጠርገው ፡ ይወስዱብን ፡ ይሆናል ፡ ወይም ፡ የመርከቧን ፡ ጐንና ፡ ጐን ፡ ይሰብሩት ፡ ይሆናል ።» ሲል ፡ በቁጣና ፡ በስጋት ፡ ጨምሮ ፡ ተናገረ ፤ ሻይውን ፡ ጨርሶም ፡ ከመኰንኖቹ ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ ወጣና ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ሄደ ።

«ሰማችሁ ፡ ወይ ፡ አሽከሮች! ሻይው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ የሚመጣው?» ሲል ፡ ጮኸ ፡ አፖልየቭ ፡ ብቻውን ፡ ቀርቶ ።

ገና ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ እንደተናገረ ፡ የኪሪሎቭ ፡ ጥቁርና ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ የመሰለው ፡ እራስ ፡ ከወደበሩ ፡ ብቅ ፡ አለ ።



መርከቧ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ስትላጋ ፡ ድንገት ፡ ወደፊት ፡ ተንገዳገደ ፤ ቢሆንም ፡ እራሱን ፡ ለመጠበቅና ፡ በአፍ ፡ ፎጣ ፡ ሸፍኖ ፡ የያዘውንም ፡ አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ሻይ ፡ እንዳይወድቅበት ፡ ለማዳን ፡ ቻለ ። ከርሱ ፡ በስተኋላም ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ አሽከር ፡ የስኳር ፡ መያዣና ፡ ደረቅ ፡ ዳቦ ፡ ያለበት ፡ አንድ ፡ ቅርጫት ፡ ይዞ ፡ ተከትሏል ። ይህ ፡ በደህና ፡ ወደርሱ ፡ ከቀረበለት ፡ በኋላ ፡ አፖልየቭ ፡ ሻዩን ፡ በመስገብገብ ፡ ጠጣና ፡ ሌላ ፡ ድጋሚ ፡ ጠየቀ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዋናው ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ መኰንን ፡ ሞቅ ፡ የሚያደርገው ፡ አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ ትኩስ ፡ ሻይ ፡ ቶሎ ፡ ለመጠጣት ፡ ወደ ፡ መኰንኖቹ ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ መጣ ። ይህ ፡ ሰው ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ሽማግሌና ፡ የነፋስ ፡ መከላከያ ፡ የለበሰ ፡ የውኃ ፡ ፍንጣቂም ፡ በልብሱ ፡ ላይ ፡ የሚያንጸባርቅበት ፤ ረጅም ፡ ያንገት ፡ ፎጣም ፡ ባንገቱ ፡ ላይ ፡ የጠመጠመ ፤ ቆቡንም ፡ እስካይኑ ፡ ድረስ ፡ ያጠለቀ ፡ ሰው ፡ ነው ። በሱ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያረጀና ፡ የነተበ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ አለባበሱ ፡ ንቁና ፡ ባለሙያ ፡ የባሕር ፡ ተኩላ ፡ ያስመስለዋል ።

የመርከቧ ፡ በኃይል ፡ መወዛወዝ ፡ ስላስቸገረው ፡ በመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ የሚራመደው ፡ በደንበኛው ፡ የመርከበኛ ፡ እግር ፡ ነው ። ምንም ፡ ነገር ፡ በጁ ፡ ሳይዝ ፡ እንዳይወድቅ ፡ ሰውነቱን ፡ እየጠበቀና ፡ እንዳንደየም ፡ በርከክ ፡ እያለ ፡ መርከቧ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ስትወዛወዝ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ ሰውነቱን ፡ ከመውደቅ ፡ ይጠብቃል ።

ይህ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ መርከቧ ፡ ባደገኛ ፡ ውኃ ፡ ላይ ፡ ትሔድ ፡ እንደሆን ፡ ለማወቅ ፡ ሰዎች ፡ በጥያቄ ፡ ሲያስቸግሩትና ፡ እሱም ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ እርግጠኛ ፡ ሳይሆን ፡ ሲቀር ፡ ይከፋዋል ። አሁን ፡ ግን ፡ ወጣቱ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ መርከበኛ ፡ የ

ዚህን ፡ ሽማግሌ ፡ ለስላሳና ፡ የተሸበሸበ ፡ ፊት ፡ ሲያይ ፡ እንዳልከፋው ፡ አወቀ ።

«እላይ ፡ ሁናቴው ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ኢቫን ፡ ኢቫኖቪች?» አለና ፡ ጠየቀው ።

«አንተው ፡ እራስህ ፡ ታየዋለህ ፡ ልጄ ። ተረኛው ፡ ጠባቂ ፡ አንተ ፡ ትመስለኛለህ ፤ ዛሬስ ፡ በማለዳ ፡ ተነሥተሃል!» አለ ፡ ሽማግሌው ፡ እየቀለደ ። ቀጥሎም ፡ «ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ያው ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ዘወትር ፡ እንደምናውቀው ፡ ነው ፡» አለ ፡ እንዲጣፍጠው ፡ ብራንዲ ፡ የጨመረበትን ፡ ሻዩን ፡ ፉት ፡ እያለ ።

«የት ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ ያለነው ፡ ኢቫን ፡ ኢቫኖቪች?»

«ከቢስካይ ፡ ሰላጤ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ማይል ፡ ያህል ፡ ከባሕር ፡ ዳር ፡ እርቀን ፡ እንገኛለን ፡ ሻይ ፡ ድገመኝ ፡» አለና ፡ ሽማግሌው ፡ ወደ ፡ አሽከሩ ፡ ጮኸ ። «ብራንዲውንም ፡ አትርሳ! ያጣፍጠዋል!» አለ ፡ ወደ ፡ ወጣቱ ፡ መኰንን ፡ ዘወር ፡ ብሎም ፡ «መሞከር ፡ አለብህ ፤ ባሕር ፡ ሲያጥወለውል ፡ ደህና ፡ ፈውስ ፡ ነው ። ባሕር ፡ አጥወልውሎህ ፡ ያውቃል?»

«የለም ፤ ፈጽሞ ፡» አለና ፡ ፎከረ ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ።

«መጀመሪያ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ እስኪለምደው ፡ ድረስ ፡ ያጥወለውለዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንዶች ፡ ሰዎች ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አይለምዱም ። አብሬው ፡ የሠራሁት ፡ አንድ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ። ወደሩሲያ ፡ መልሰው ፡ ላኩት ፤ ምስኪን ።»

«ምናልባት ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ጊዜ ፡ ረጋ ፡ ይል ፡ ይሆናል ፡» አለ ፡ አፖልየቭ ፡ ነገሩን ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡ ለማስመሰልና ፡ ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ የሆነው ፡ ቢሆን ፡ ግድ ፡ የሌለው ፡ ለመምሰል ። ኢቫን ፡ ኢቫኖቪች ፡ የውስጠ ፡ ወይራ ፡ ፈገግታ ፡ አሳየ ።

«ረጋ ፡ ይል ፡ ይሆናል ፡ ነው ፡ ያልከው?» ብሎ ፡ ጠየቀ ።



«አዎ ፡ አይሻለውም ፡ ብለው?»

«ሲመሽስ ፡ ገና ፡ ኃይለኛ ፡ የባሕር ፡ መናወጥ ፡ አለ ። የአየር ፡ ክብደት ፡ መለኪያው ፡ እንደሚያሳየው ፡ አየሩ ፡ በጣም ፡ ቀዝቅዟል ።»

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሕይወቱን ፡ ያሳለፈውና ፡ አያሌ ፡ ማዕበልም ፡ ያየው ፤ ከካምቻትካም ፡ ጥቂት ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ የመርከብ ፡ መሰበር ፡ የደረሰበት ፡ ሽማግሌው ፡ ዋና ፡ መንገደ ፡ መሪ ፡ መኰንን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሲናገር ፡ በጸጥታና ፡ እንደማንኛውም ፡ ተራ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አድርጎ ፡ ነበር ። ሻይውን ፡ ከብራንዲ ፡ ጋር ፡ ፉት ፡ ፉት ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ እንደተስማማው ፡ አጕረምርሞ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጨምሮ ፡ ተናገረ ፤

«አሁን ፡ ጉንፋኔ ፡ አያሰጋኝም ። እላይ ፡ በነበርኩ ፡ ጊዜ ፡ ያለማቋረጥ ፡ እስል ፡ ነበር ። ሰማህ ፡ ወይ ፡ ቫሲልየቭ!» አለና ፡ ተጣራ ።

አሽከሩ ፡ መጣ ።

«እስቲ ፡ ትንሽ ፡ ብራንዲ ፡ ድገመኝ ፡ በቃ! በቃ! ብራንዲ ፡ ደህና ፡ ያሞቃል ፡» አለ ፡ ጨመር ፡ አድርጎ ፡ እራሱን ፡ ለመደገፍ ፡ ሲል ። ይህ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ የራሱንና ፡ የሌሎችንም ፡ ሕመም ፡ በብራንዲ ፡ ማዳን ፡ ይወድ ፡ ነበር ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ደግሞ ፡ በሼሪና ፡ በማርሳላ ።

ሌላ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አይፈቅድም ፤ በተለይም ፡ ሻምፓኝን ፡ «የሴቶች ፡ መጉመጥመጫ ፡» ነው ፡ በማለት ፡ ይጠላው ፡ ነበር ።

«ታዲያስ ፡ ማዕበል ፡ ይነሣ ፡ ይመስልሃል ፡ ኢቫን ፡ ኢቫኖቪች?» ሲል ፡ አፖልየቭ ፡ በግዴለሽነት ፡ መልክ ፡ ጠየቀ ። ያንየውንም ፡ ምናልባት ፡ ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ ከድምጹ ፡ የፍርሃት ፡ ስሜት ፡ ያየበት ፡ ስለመሰለው ፡ ፊቱ ፡ ቀላ ።

«እንደሚነሣ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። ያውም ፡ ዕውነተኛው ፡ ነዋ ፡ ልጄ ። ይህች ፡ የቢስካይ ፡ ሰላጤ ፡ መጥፎ ፡ ቦታ ፡ ናት ። በዚህ ፡ በኩል ፡ ባለፍኩ ፡ ቁጥር ፡ ትንሽ ፡ ማዕበል ፡ ሳታቀምሰኝ ፡ ቀርታ ፡ አታውቅም ።»

ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ ብርጭቆውን ፡ በደስታ ፡ ጨለጠና ፡ ቆቡን ፡ ወደታች ፡ ሳብ ፡ አድርጐ ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ መድረክ ፡ ሄደ ።

ኦፖልየቭ ፡ ወደመኰንኖቹ ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ ሰዓት ፡ ተመለከተ ፤ ለሁለት ፡ ሰዓት ፡ አምስት ፡ ደቂቃ ፡ ጉዳይ ፡ ነበር ። ሻይውን ፡ ሲጨርስ ፡ የዝናብ ፡ ልብሱን ፡ ኪራሎቭ ፡ አለበሰውና ፡ ልክ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ወደሚወስደው ፡ መሰላል ፡ ላይ ፡ ወጣ ። በሕይወቱ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚገጥመው ፡ ማዕበል ፡ በማሰብ ፡ ልቡ ፡ ተሸበረ ። እንደገናም ፡ በአእምሮው ፡ ወደዚያ ፡ መዓዛ ፡ ወደተመላበት ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ ሄዶ ፡ ጽጌረዳ ፡ በመሰለው ፡ በሴና ፡ ጉንጭ ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ጥቁር ፡ ነጥብ ፤ ስለ ፡ ውብ ፡ ዓይኖቿም ፡ ያስብ ፡ ጀመር ።

«እንዴት ፡ ጥሩ ፡ ነበር ፡ እዚያ ፤ እዚህ ፡ ግን ፡ …» አለ ፡ ወጣቱ ፡ መኰንን ፡ በሐሳቡ ።

ወደ ፡ መድረኩ ፡ ላይ ፡ ሲወጣ ፡ አካባቢው ፡ ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ ሌላ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ።

እንደ ፡ በረዶ ፡ የሚቀዘቅዝና ፡ ስለታም ፡ ነፋስ ፡ ከውኃ ፡ ፍንጣቂ ፡ ጋር ፡ በላው ፡ ላይ ፡ ነፈሰበት ። በነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሽራዎች ፡ መካከል ፡ ነፋሱ ፡ በኃይል ፡ ሲያፏጭ ፡ ሰማው ፤ ግራጫና ፡ የሚያጕራ ፡ ውቅያኖስም ፡ አየ ፤ ሐሳቡም ፡ በፍጥነት ፡ ወደባሕር ፡ ተግባሩ ፡ ተለወጠ ።



በግዴለሽነት ፡ መልክ ፡ በመርከቧ ፡ መሽጋገሪያ ፡ ላይ ፡ በድፍረት ፡ ሲራመድ ፡ ገሃነመ ፡ እሳትን ፡ የማይፈራና ፡ ማዕበልንም ፡ ከምንም ፡ የማይቆጥር ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጽኑ ፡ ፍርሃት ፡ ቢሰማውም ፡ የሚያጕራው ፡ ውቅያኖስ ፡ ግርማና ፡ ሞገስ ፡ የወጣቱን ፡ መኰንን ፡ ልብ ፡ ማረከው ፤ የፍጥረት ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ኃይል ፡ ፊት ፡ ግን ፡ ትሁትና ፡ ደካማ ፡ መሆኑን ፡ አስገነዘበው ።

በአካባቢው ፡ ሁሉ ፡ ዓይኑ ፡ እስከቻለ ፡ ድረስ ፡ ቢመለከት ፡ ውቅያኖሱ ፡ እንደሚገነፍል ፡ ነጭ ፡ አረፋና ፡ ቁጥር ፡ ስፍር ፡ እንደሌለው ፡ የማዕበል ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ አየው ። እንደሚፈነዳ ፡ ነገርም ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ብር ፡ የመሰለ ፡ ጠርዙን ፡ እያጋጨ ፡ ሲያጕራ ፡ ተመለከተ ። እነዚያ ፡ ከሩቅ ፡ ትናንሽ ፡ ጋራዎች ፡ መስለው ፡ የታዩት ፡ ማዕበሎችም ፡ ቀረብ ፡ ሲሏቸው ፡ ታላቅ ፡ የውኃ ፡ ተራራዎች ፡ ሆኑ ። ማዕበሎቹ ፡ ዝቅ ፡ ብድግ ፡ ሲሉ ፡ ትንሿ ፡ ጥቁር ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያዋን ፡ አውርዳ ፡ የሚመጣውን ፡ ማዕበል ፡ በመጠባበቅ ፡ ጉዞዋን ፡ ትቀጥላለች ።

መርከቧ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተላጋች ፡ ከማዕበሉ ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ ወደላይ ፡ ተነሥታ ፡ ሰንጥቃው ፡ ታልፋለች ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እማዕበሉ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ ትልና ፡ የማዕበሉ ፡ ክፍል ፡ ግንባሯን ፡ ያጥበዋል ፤ የተረፈውም ፡ ውኃ ፡ እንደ ፡ አልማዝ ፡ ይረጫል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ማዕበሉ ፡ የመርከቧን ፡ መድረክ ፡ ያለብሰውና ፡ በውኃ ፡ መውረጃው ፡ በኩል ፡ ተመልሶ ፡ ይወጣል ።

ኃይለኛ ፡ ማዕበል ፡ ተቃረበ ። የባቄላ ፡ ፍሬ ፡ በምታህለ
ው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ተራራ ፡ አህሎ ፡ የሚወድቅባት ፡ ይመስላ
ል ። ቢወድቅባት ፡ እሷንም ፡ ሰዎቿንም ፡ ጨርሶ ፡ ይደመስሳቸ
ዋል ። ግን ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የመርከቧ ፡ ግንባር ፡ ከሌላ ፡ ማዕበ
ል ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ወደታች ፡ ዝቅ ፡ ይልና ፡ የመርከቧ ፡ ኋላ ፡ ቀ
ጥ ፡ ብሎ ፡ ሲወጣ ፡ ታላቅ ፡ የባሕር ፡ ግድግዳ ፡ ይመታዋል ፤ የ
መርከቧ ፡ ኋላ ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ዝቅ ፡ ይላል ።

አንድ ፡ አቅጣጫ ፡ ይዞ ፡ ፈጥኖ ፡ የሚሮጥ ፡ ጥቁር ፡ ደመ
ና ፡ ሰማዩን ፡ ሸፍኖታል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ፀሐይዋ ፡ ብቅ ፡
ትልና ፡ በግራጫው ፡ ውቅያኖስ ፡ ላይ ፡ ጨረሯን ፡ ፈንጥቃ ፡
ወዲያው ፡ ወደ ፡ ደመናው ፡ ውስጥ ፡ ትገባለች ። ነፋሱ ፡ የ
ማዕበሉን ፡ ጠርዝ ፡ እየሰነጠቀና ፡ ብር ፡ የመሰሉ ፡ የውኃ ፡
ጠብታዎች ፡ እየፈነጠቀ ፡ በኃይል ፡ ይነፍሳል ። በመንገዱ ፡
ላይ ፡ የሚያደናቅፈው ፡ ነገር ፡ በማግኘቱም ፡ የተቆጣ ፡ በመ
ምሰል ፡ የመርከቧን ፡ ጐን ፡ እየጐነጠና ፡ እያወዛወዘ ፡ ያፏ
ጫል ።

ጠባቂዎቹም ፡ በሰማያዊ ፡ ሸሚዛቸው ፡ ላይ ፡ ውኃ ፡ ተከላ
ካይ ፡ ልብስ ፡ አጥልቀውና ፡ የነፋሱን ፡ መወጠሪያ ፡ ገመድ ፡ ጨ
ብጠው ፡ ይዘው ፡ ቆመዋል ። ጸጥ ፡ ጭጭ ፡ ብለዋል ፤ ከአን
ዳቸውም ፡ ዘንድ ፡ ጨዋታና ፡ ሳቅ ፡ አይሰማም ፤ አንድ ፡ ከባድ ፡
ማዕበል ፡ አጥቧቸው ፡ ሲያልፍ ፡ ውኃውን ፡ ከላያቸው ፡ ላይ ፡
እንደ ፡ ዳክዬ ፡ አራግፈው ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ወደሚንከባለለው ፡
ውቅያኖስ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ወደመርከቧ ፡ መሽጋገሪያ ፡ ይ
መለከታሉ ።

በመሽጋገሪያው ፡ ላይ ፡ ሽምገል ፡ ያለው ፡ የመርከቧ ፡ አ
ዛዥ ፡ እግሩን ፡ አንፈራጦና ፡ በጆቹ ፡ የጅ ፡ መያዣውን ፡ ይዞ ፡
ከመሽጋገሪያው ፡ ጋር ፡ እንደታሰረ ፡ ሁሉ ፡ ቆሟል ። ፊቱ ፡ የር



ጋታና ፡ የጸጥታ ፡ መልክ ፡ እንደያዘ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አድ
ማሱ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ወደ ፡ ነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሸራው ፡
ይመለከታል ። ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ያሳለፈው ፡ እንደነቃ ፡ ነ
ው ። ነፋስ ፡ የመታውና ፡ የደከመ ፡ ፊቱም ፡ ይበልጥ ፡
ያረጀ ፡ አስመስሎታል ። ላንድ ፡ ለሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡
ለማረፍ ፡ ፈልጐ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ከማድረጉ ፡
በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሸራውን ፡ ለማው
ረድና ፡ መጭውን ፡ ማዕበል ፡ በማዕበል ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡
ሸራ ፡ ብቻ ፡ ለመቀበል ፡ ወሰነ ።

ኦፖልየቭን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በቁርጠኛና ፡ በጐረና ፡ ድም
ጽ ፡ አዘዘው ፤

«የነፋስ ፡ መወጠሪያውን ፡ አውርድና ፡ የማዕበል ፡ የነ
ፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሸራውን ፡ አውጣ!»

«እሺ ፡ ጌታዬ!» ሲል ፡ እጩ ፡ መኰንኑ ፡ መለሰና ፤ የድ
ምጽ ፡ ማጉሊያውን ፡ አፉ ፡ ላይ ፡ ለጉሞ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
ጮኸ ፤

«የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሸራ ፡ ይውረድ! የነፋስ ፡ መወጠሪ
ያ ፡ አውራጆችም ፡ ተዘጋጁ!»

አውራጆቹ ፡ ወደገመዱ ፡ በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
አዘዛቸው ፤

«በምሰሶው ፡ ዙሪያ ፡ ተሰለፉ!»

ገመዱን ፡ አጥብቀው ፡ ይዘው ፡ ወደላይ ፡ በቀስታና ፡ በጥ
ንቃቄ ፡ መወጣት ፡ ጀመሩ ። ምሰሶው ፡ በኃይል ፡ ሲወዛወዝ ፡ እ
ንደምንም ፡ ወደጫፉ ፡ እየዳሁ ፡ ደረሱ ። ወጣቱ ፡ መኰንንም ፡
እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ቅንጣት ፡ ፍሬ ፡ አህለው ፡ በሚያስ
ፈራው ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተወዛወዙ ፡ የነፋ
ስ ፡ መወጠሪያውን ፡ በፍጥነት ፡ ሲፈቱ ፡ ትንፋሹን ፡ ቋጥሮ ፡

ተመለከታቸው ። ምናልባት ፡ እንደኛውን ፡ ነፋስ ፡ ጥሎት ፡ እመርከቧ ፡ ላይ ፡ ወርዶ ፡ ይዘረራል ፡ በማለት ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ። በፍርሃት ፡ የተመሉት ፡ ዓይኖቹ ፡ ላንድ ፡ ሴኮንድ ፡ እንኳ ፡ ከምሰሶው ፡ ላይ ፡ አልተነቀሉም ፡ ነበር ። የመርከቧ ፡ አዛዥና ፡ ዋናው ፡ መኰንንም ፡ አተኩረው ፡ ይመለከቷቸው ፡ ነበር ። እነሱም ፡ እንደዚሁ ፡ ሰግተው ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

መርከበኞቹ ፡ ግን ፡ በግራቸውም ፡ በቀኛቸውም ፡ ገመዱን ፡ ጥርቅም ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ ነበር ። ባንድ ፡ እጃቸው ፡ ምሰሶውን ፡ ይዘው ፡ ባንድ ፡ እጃቸው ፡ ደግሞ ፡ ከባዱን ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሸራ ፡ ይፈቱ ፡ ነበር ። ሥራቸውን ፡ ሲፈጽሙ ፡ አፖልየቭ ፡ በደስታ ፡ ስሜት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዛቸው ፤

«የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ አውራጆች ፡ ውረዱ!»

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የማዕበል ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያ ፡ ሸራ ፡ ተዘረጋና ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥ ፡ አፖልየቭ ፡ በተለመደው ፡ የትዕዛዝ ፡ ድምጹ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

«አንድ ፡ ነገር ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ጥራኝ ። የመርከብ ፡ ነጂዎቹም ፡ ነቅተው ፡ እንዲሠሩ ፡ ተቆጣጠር ፡» ሲል ፡ የመርከብ ፡ ነጂዎቹም ፡ እንዲሰሙ ፡ ጮኾ ፡ ተናገረ ።

ኋላም ፡ እረፍት ፡ ለማድረግ ፡ ወደክፍሉ ፡ ሄደ ። ዋናው ፡ መኰንን ፡ ከአፖልየቭ ፡ ጋር ፡ በመድረኩ ፡ ላይ ፡ ቀረ ።

አፖልየቭ ፡ ጥበቃውን ፡ ሲጨርስ ፡ ከሥራው ፡ ጋር ፡ ተለማምዶ ፡ ነበር ፤ ማዕበሉም ፡ እምብዛም ፡ አላስፈራውም ፡ ነበር ። እኩለ ፡ ቀን ፡ ሲሆን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ ምትክ ፡ ገባና ፡ ሥራውን ፡ በሚገባ ፡ በመፈጸሙ ፡ ኩራት ፡ እየተሰማው ፡ ወደ ፡ መኰንኖች ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ ሄደ ። ነገር ፡ ግን ፡ ኩራቱን ፡ የተመለከተለት ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።



መጥፎው ፡ የአየር ፡ ጠባይ ፡ የምግብ ፡ ዝግጅቱን ፡ ሥራ ፡ ስላቃወሰው ፡ ለምሳ ፡ የቀረበው ፡ ምግብ ፡ አሳማና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀዝቃዛ ፡ የቆርቆሮ ፡ መብል ፡ ነበር ። ምሳ ፡ የቀረበውም ፡ ከጠረጴዛው ፡ ጋር ፡ ጠብቆ ፡ በተያያዘ ፡ የእንጨት ፡ ቆሪ ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። የቀሩትም ፡ የምግብ ፡ ዕቃዎችና ፡ ጠርሙሶች ፡ በተለየ ፡ ቦታ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። መርከቧ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ትላጋ ፡ ስለነበርም ፡ አሽከሮቹ ፡ ቆመው ፡ ምግብ ፡ ለማሳለፍ ፡ በጣም ፡ ቸግሯቸው ፡ ነበር ። ምግቡም ፡ የተበላው ፡ በፍጥነትና ፡ በጸጥታ ፡ ነበር ፤ የተለመደው ፡ የደስታ ፡ ጭውውትም ፡ አልነበረም ፤ አብዛኞቹም ፡ መኰንኖች ፡ የምግብ ፡ ፍላጎት ፡ አልነበራቸውም ። ሽማግሌው ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ መኰንን ፡ ብቻ ፡ ሳይለወጥ ፡ እንደወትሮው ፡ ለሁለት ፡ ሰው ፡ የሚበቃ ፡ ምግቡን ፡ በልቶ ፡ ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ዘወትር ፡ የሚሰጠውን ፡ የማርሳላ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጣ ።

ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ ወደየክፍላቸው ፡ ሄዱ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

ውድቅት ፡ ሲሆን ፡ ኃይለኛው ፡ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ማዕበል ፡ ተለወጠ ።

ልብሱን ፡ ሳያወልቅ ፡ ለመተኛት ፡ የሄደውን ፡ አፖልየቭን ፡ አንድ ፡ ኃይለኛ ፡ ግጭት ፡ በድንገት ፡ ቀሰቀሰው ። ዓይኑን ፡ ሲገልጥም ፡ ክፍሉ ፡ በሙሉ ፡ በመብረቅ ፡ ብርሃን ፡ በርቶ ፡ አየው ። ኋላም ፡ እንደገና ፡ ጨለማ ፡ ሆነና ፡ ነጐድጓዱ ፡ አስተጋባ ።

በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ በሩን ፡ እንደምንም ፡ ፈልጐ ፡ አገኘና ፡ ወደ ፡ መርከበኞች ፡ መኖሪያ ፡ ሰፈር ፡ እየተንገዳገደ ፡ ሄደ ። መርከቧ ፡ ወደግራም ፡ ወደቀኝም ፤ ወደኋላም ፡ ወደፊትም ፡

ትላጋ ፡ ነበር ። አንድም ፡ መርከበኛ ፡ አልተኛም ፡ ነበር ።
የሚንጠለጠል ፡ አልጋቸውም ፡ ባዶውን ፡ ይወዛወዝ ፡ ነበር ።
ተረኛ ፡ ያልሆኑት ፡ መርከበኞች ፡ ፊታቸው ፡ በፍርሃት ፡ ገር
ጥቶ ፡ እዚህም ፡ እዚያም ፡ ሰብሰብ ፡ ብለው ፡ ነበር ። አብ
ዛኞቹ ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ ይተነፍሱ ፡ ነበር ፡ ወይም ፡ ደግም ፡ በቀስ
ታ ፡ ጸሎት ፡ እያደረሱ ፡ በጃቸው ፡ ያማትቡ ፡ ነበር ። ድብዝዝ ፡
ባለው ፡ የሚወዛወዝ ፡ መብራት ፡ ሥር ፡ እነዚህን ፡ በፍርሃት ፡
የተዋጡ ፡ ሰዎች ፡ ማየት ፡ የሚያሳዝን ፡ ትርኢት ፡ ነበር ።
ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ በጎረና ፡ ድምጽ ፡ ጮኾ ፡ እንዲህ ፡
አለ ፤

«ጎበዝ ፡ ንጹሕ ፡ ሸሚዛችንን ፡ እናጥልቅ ፤ ማለቃችን ፡
ነው!»

የሥራ ፡ ኃላፊው ፡ በዚህ ፡ ንግግር ፡ አለቅጥ ፡ ተቆጥቶ ፡
በሻካራ ፡ ድምጹ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

«አፍህን ፡ ዝጋ ፡ አንተ! ሰዎቹን ፡ ልታስፈራራ ፡ ነው?
አሁን ፡ አንተም ፡ መርከበኛ ፡ ነኝ ፡ ትል ፡ ይሆናል!»

ከዚህም ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ ሰዎቹን ፡ የሚያስደስት ፡ የስ
ድብ ፡ ማዕበል ፡ አወረደበት ።

ሽማግሌው ፡ ታቦት ፡ ጠባቂ ፡ ሽቸርባኰቭ ፡ ጧት ፡ ጧት ፡
እንደሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡ በሞተሩ ፡ ክፍል ፡ አጠገብ ፡ ጥቂቶች ፡
መርከበኞች ፡ ሰብስቦ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያነብላቸው ፡ ነበር ።

የሚሰለች ፡ የዜማ ፡ ድምጹም ፡ ነጎድጓዱ ፡ አስተጋብቶ ፡
ዝም ፡ ባለ ፡ ቁጥር ፡ ጎልቶና ፡ ጠርቶ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

«በዚያኑ ፡ ቀን ፡ ክርስቶስ ፡ ከቤቱ ፡ ወጥቶ ፡ ሄደና ፡ በባ
ሕር ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጠ ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ወደርሱ ፡ መጥተ
ው ፡ ተሰበሰቡ ። እሱም ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀመጠ ፤
የተሰበሰቡትም ፡ ሰዎች ፡ በባሕሩ ፡ ዳር ፡ ቆሙ ፡» አለ ።



ኪሪሎቭ ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ መሰላሉን ፡ ጨብጦ ፡ ይዞ ፡ በዝ
ምታ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ።

«ኪሪሎቭ ፤ አንተ ፡ ነህ ?» ብሎ ፡ አፓልየቭ ፡ ጠራው ።

«አዎን ፡ ጌታዬ ።»

«ምነዋ! ታለቅሳለህ ፡ እንዴ?»

«ምን ፡ ላድርግ ፤ ፈራሁ ፡ ጌታዬ ፤ ሽቸርባኰቭ ፡ የሚያነበ
ውም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ነው ።»

«አታፍርም! መርከበኛ ፡ አይደለህም?»

«አዎን ፡ ጌታዬ ፡» አለ ፡ ወጣቱ ፡ መርከበኛ ፡ እንባውን ፡
ለማገድ ፡ እየሞከረ ።

«በላ ፡ ታዲያ ፡ እንደመርከበኛ ፡ ሁን ፡» አለው ፡ ወጣቱ ፡
እጩ ፡ መኰንን ፡ በማስተዛዘን ፡ ድምጽ ። «አይዞህ ፡ ምንም ፡ ክ
ፉ ፡ አደጋ ፡ አይደርስብንም ።» እሱም ፡ እራሱ ፡ ስጋት ፡ አድ
ሮበት ፡ ስለነበር ፡ የአሽከሩን ፡ ትከሻ ፡ ቸብ ፡ ቸብ ፡ አደረገና ፡
መወጣጫውን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ መርከቧ ፡ መድረክ ፡ አመራ ።

የመርከቧን ፡ መድፍ ፡ ጨብጦ ፡ ይዞም ፡ በመርከቧ ፡ መ
ሽጋገሪያ ፡ ሥር ፡ ወደመርከቧ ፡ ግንባር ፡ ሄደ ። እመድረኩ ፡ ጋ ፡
ሲደርስም ፡ ዙሪያውን ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ በፍርሃት ፡ በድን ፡
ሆነ ።

የጦር ፡ መርከቧ ፡ እባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ እያለች ፡ ት
ወጣ ፡ ነበር ፤ ውኃውም ፡ ግንባሯን ፡ ያጥበው ፡ ነበር ። ነጎድጓ
ዱ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ሲያስተጋባና ፡ መብረቁም ፡ የዝናሙን ፡ ደመ
ና ፡ ሲወጋው ፡ የሚታየው ፡ ጠመዝማዛ ፡ ብልጭታ ፡ የሚደነ
ፋውን ፡ ውቅያኖስና ፡ ጋራ ፡ የሚያህለውን ፡ ማዕበል ፤ እንዲ
ሁም ፡ የተላላጠውን ፡ የመርከቧን ፡ የላይ ፡ ልባድ ፡ አብርቶ ፡
ያሳይ ፡ ነበር ። ከጀልባዎቹ ፡ አንዱንም ፡ ውኃ ፡ ይዞት ፡ ሄዷል ።
ማዕበሉ ፡ በሙሉ ፡ ኃይሉ ፡ የተነሣና ፡ መርከቧንም ፡ ከወዲያ ፡

ወዲህ ፡ እያመታ ፡ ሊያጠፋት ፡ የተቃረበ ፡ ይመስላል ። መርከቧ ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እማዕበሉ ፡ ላይ ፡ እየነጠረች ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እየተደፈቀች ፤ ሕመሙ ፡ ስለጐዳትም ፡ እየተንቋቋችና ፡ እያቃሰተች ፡ አደገኛ ፡ መንገዷን ፡ ቀጠለች ። መርከበኞቹ ፡ በየቦታው ፡ ተሰብስበው ፡ የሕይወት ፡ መጠበቂያውን ፡ ገመድ ፡ ይዘዋል ። መብረቁ ፡ ዓይን ፡ የሚያጠፋውን ፡ ብርሃኑን ፡ ብልጭ ፡ ባደረገ ፡ ቁጥር ፡ መርከበኞቹ ፡ ያማትባሉ ። ዋናው ፡ የመርከቧ ፡ አዛዥም ፡ እመርከቧ ፡ መንጃ ፡ አጠገብ ፡ ሆኖ ፡ ለስድስቱ ፡ ነጂዎች ፡ አጭር ፡ ትዕዛዝ ፡ በመስጠት ፡ መርከቧ ፡ በየት ፡ በኩል ፡ መሄድ ፡ እንዳለባት ፡ ይመራል ። የደከመው ፤ የገረጣውና ፡ በጣም ፡ የተኰሳተረው ፡ ፊቱ ፡ በመርከቧ ፡ የፋኖስ ፡ ብርሃን ፡ ቁልጭ ፡ ብሎ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። ባጠገቡም ፡ ዋናው ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ መኰንንና ፡ ዋናው ፡ መኰንን ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

በመጀመሪያዎቹ ፡ ጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ወጣቱን ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ የፍርሃት ፡ ሞት ፡ አንቆት ፡ ነበር ። ቀስ ፡ በቀስ ፡ ግን ፡ ፍርሃቱ ፡ ወደ ፡ በድንነት ፡ ተለወጠ ።

«መርከቧ ፡ የሰመጠች ፡ እንደሆን ፡ ሁላችንም ፡ ማለቃችን ፡ ነው ፡» የሚል ፡ ሐሳብ ፡ በአዕምሮው ፡ ላይ ፡ ብልጭ ፡ አለበት ።

አንድ ፡ ነገር ፡ ጨብጦም ፡ እዚያው ፡ አለበት ፡ ቦታ ፡ ድርቅ ፡ ብሎ ፡ ቀረ ።

«አምላክ ፡ ሆይ ፡ ማረን!» ሲል ፡ ምልክት ፡ ሰጭው ፡ ከርሱ ፡ ጥቂት ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ቁሞ ፡ ሲናገር ፡ ሰማው ። «ወዲያ ፡ ማዶ ፡ ይመልከቱ ፡ ጌታዬ!» አለ ።

አፖልየቭ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ አስቀድሞ ፡ አይቶ ፡ ነበር ። አንዲት ፡ መርከብ ፡ ጥቂት ፡ እራቅ ፡ ብላ ፡ ስትሰምጥ ፡ የመብረቁ ፡



ብርሃን ፡ ወለል ፡ አድርጐ ፡ አሳየ ። መርከበኞቹም ፡ በመጨነቅ ፡ እጃቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሳይወድ ፡ በግድ ፡ ዓይኑን ፡ ከደነ ።

ሌላ ፡ መብረቅ ፡ ደግም ፡ ውቅያኖሱን ፡ እንደገና ፡ አበራው ፤ መርከቧ ፡ ግን ፡ የለችም ፡ ነበር ።

አፖልየቭ ፡ አማተበ ፤ ባጠገቡ ፡ የነበሩትም ፡ መርከበኞች ፡ ትንፋሻቸውን ፡ በረዥሙ ፡ ሳቡ ።

«ሁሉም ፡ ሰመጡ!» አለ ፡ አንደኛው ።

* * *

ወጣቱ ፡ እጩ ፡ መኰንን ፡ የውቅያኖሱን ፡ ድንፋታ ፡ እየተመለከተ ፡ ላንድ ፡ ወይም ፡ ለሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ በመርከቧ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ቆየ ። ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ እንደቆየ ፡ ግን ፡ እሱም ፡ እራሱ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ።

በመጨረሻ ፡ ማዕበሉ ፡ ትንሽ ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ስለመሰለው ፡ አፖልየቭ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ወረደ ።

በመርከበኞቹ ፡ መኖሪያ ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ የፍርሃት ፡ ስሜት ፡ እንዳለ ፡ ነበር ። ሽቸርባኰቭም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ማንበቡን ፡ ይቀጥል ፡ ነበር ።

ወጣቱ ፡ መኰንን ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ተዘረጋ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ያየው ፡ ነገር ፡ አዕምሮውን ፡ ስላናወጸው ፡ እንቅልፍ ፡ እስኪወስደው ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈጀበት ። በመጨረሻ ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ ያዘውና ፡ ተኛ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

በነቃም ፡ ጊዜ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ የቀን ፡ ብርሃን ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ አየ ። ካልጋው ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ሲቀመጥም ፡ መርከቧ ፡ በርጋታ ፡ ስትጓዝ ፡ አገኛት ፤ ደስታ ፡ የተመላበት ፡ የመደነቅ ፡ ስሜትም ፡ አደረበት ። በክፍሉ ፡ በር ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ በተመለከተም ፡ ጊዜ ፡ መርከበኞቹ ፡ በደስታ ፡ ሲጨዋወቱ ፡ አየ ። ቀዳዳውም ፡ ሁሉ ፡ ተከፍቶ ፡ መጥፎው ፡ ሽታ ፡ ለቆ ፡ ነበር ።

«ኪሪሎቭን ፡ ላኩልኝ ፡» አለና ፡ ጮኸ ።

ኪሪሎቭ ፡ የደስታ ፡ መልክ ፡ ይዞ ፡ መጣ ።

«እንዴት ፡ አደርክ ። ማዕበሉ ፡ ጸጥ ፡ ብሏላ?»

«አዎን ፡ ጌታዬ ።»

«ይሄውልሃ ፤ ማዕበሉን ፡ እንደምንም ፡ እናልፈዋለን ፡ አላልኩሁም ፡ ነበር?»

«አዎን ፡ ጌታዬ ።»

የመኰንኖቹ ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ አምሮና ፡ ደምቆ ፡ ነበር ። መኰንኖቹም ፡ ሁሉ ፡ እዚያ ፡ ተሰብስበው ፡ የሚያወሩት ፡ ስለ ፡ ማዕበሉና ፡ «ሶኮል ፡» ምንም ፡ እንኳ ፡ ትንሽ ፡ ብትጐዳና ፡ አንድ ፡ ጀልባም ፡ ቢጠፋባትም ፡ ቅሉ ፡ መከራውን ፡ እንዴት ፡ እንዳለፈችው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምክንያቱን ፡ እንጃ ፡ ስትሰምጥ ፡ ያይዋትን ፡ መርከብ ፡ አንዳቸውም ፡ አላነሡም ፡ ነበር ።

«ደንበኛው ፡ ማዕበል ፡ ነበር ። ደህና ፡ አድርጐ ፡ አንቀጠቀጠን ፡» አለ ፡ ሽማግሌው ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ መኰንን ። «አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ገና ፡ አለቀቀም! ሆኖም ፡ ግድ ፡ የለም ፡... የአየር ፡ ክብደት ፡ መለኪያው ፡ እንደሚያሳየው ፡ አየሩ ፡ ሞቅ ፡ እያለ ፡ ነው ፡ የሚሄደው ፡» አለ ፡ ጨመር ፡ አድርጐ ። ሁለት ፡



ብርጭቆ ፡ ሻዩን ፡ ከብራንዲ ፡ ጋር ፡ ከጠጣ ፡ በኋላም ፡ ፀሐይ ፡ ለመሞቅ ፡ ወደመድረኩ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ማዕበሉ ፡ ገና ፡ በሙሉ ፡ ጸጥ ፡ ባይልም ፡ ቅሉ ፡ ስኒ ፡ ይዞ ፡ ሻይ ፡ ለመጠጣት ፡ ያህል ፡ ደህና ፡ ነበር ። ኦፖልየቭ ፡ ባለፉት ፡ ቀናት ፡ ያልበላውን ፡ ለመካስ ፡ ሲል ፡ ከሻዩ ፡ ጋር ፡ ግማሽ ፡ ቆርቆሮ ፡ ያህል ፡ የእንግሊዝ ፡ ብስኩት ፡ በላ ። ተጫዋቹንና ፡ ተወዳጁን ፡ ውሻ ፡ ላይካን ፡ እንዲሁም ፡ ዱብየውን ፡ ድመት ፡ ቫስካን ፡ ሳይረሳ ፡ መገባቸው ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ውቅያኖሱን ፡ ለመመልከት ፡ ወደ ፡ መድረኩ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

ውቅያኖሱ ፡ ጸጥ ፡ እያለ ፡ ይሄዳል ። ከባዱ ፡ ማዕበልም ፡ እንደ ፡ በፊቱ ፡ በኃይል ፡ አይደነፋም ፤ መርከቧም ፡ ዋናውን ፡ የነፋስ ፡ መወጠሪያዋን ፡ ዘርግታ ፡ አዲስና ፡ የማይቋርጥ ፡ ነፋስ ፡ እየገፋት ፡ በርጋታ ፡ ትጓዛለች ።

አናጢዎቹም ፡ በመርከቧ ፡ ጐንና ፡ ጐን ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ ይጠግናሉ ፤ ሲሠሩም ፡ ያንጐራጉራሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

ከሁለት ፡ ቀናት ፡ በኋላ ፡ ኪሪሎቭ ፡ ጌታውን ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ቀሰቀሰው ።

«ጌታዬ ፡ አሌክሳንደር ፡ ኢቫኖቪች! ይነሡ ፡ ጌታዬ! ወደ ፡ ማዴይራ ፡ ልንደርስ ፡ ነው!»

ወጣቱ ፡ መኰንን ፡ ብዙ ፡ ከተነቀነቀ ፡ በኋላ ፡ ተነሣ ።

«አሁን ፡ ቶሎ ፡ ደርሰን ፡ መርከቧ ፡ መልሕቋን ፡ ትጥላለች ። ቀኑም ፡ የተዋበ ፡ ነው!» አለ ፡ አሽከሩ ፡ በደስታ ፡ ስሜት ።

አፖልየሽም ፡ ቶሎ ፡ ለበሰና ፡ ወደ ፡ መድረኩ ፡ ሮጦ ፡ ሄደ ።

መርከቧም ፡ ጭሷን ፡ ቡልቅ ፡ ቡልቅ ፡ እያደረገች ፡ ጭጋግ ፡ ወደ ፡ ሸፈነው ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ተራራማ ፡ ደሴት ፡ ተቃረበች ። ማዕበሉ ፡ ያደረሰባት ፡ ጉዳት ፡ በደንብ ፡ ስለተጠገነ ፡ የ«ሶኮል ፡» ገላ ፡ በጠራው ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ በዝግታ ፡ በምትሽከረከረው ፡ አብረቅራቂ ፡ ፀሐይ ፡ ሥር ፡ በንጽሕና ፡ አበራ ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ በኃይል ፡ ሲደነፋባቸው ፡ የነበረውም ፡ ውቅያኖስ ፡ አሁን ፡ በርጋታ ፡ ይወዛወዛል ፤ አታላይ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለሙም ፡ የመርከቧን ፡ ጐን ፡ በለዘብታ ፡ ላስ ፡ ላስ ፡ ያደርገዋል ።

ማውጫ ።


| | ገጽ ። |
|---|---|
| ማክሲምካ ። | ፫ |
| ቆሪጥ ። | ፶፩ |
| ማዕበል ፡ ሲነሣ ። | ፹፭ |

## አንባብያን ፡ ሆይ!

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ፡ ስለዚች ፡ መጽሐፍ ፡ ትርጉም ፤ ዝግጅትና ፡ እትም ፡ ያላችሁን ፡ አስተያየትና ፡ አሳባችሁን ፡ ብትገልጹለት ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል ።

አድራሻው ፤
21, Zubovsky Boulevard, Moscow, U. S. S. R.